

BL Or. 534, f. 1a.

እስካሁን ከተገኙት የዜናሁ ለጋላ ቅጅዎች አንዱ።

(ገጽ 63-66 ላይ ተቀድቷል።)

# ምዕራፍ ፫


## ጋላ/ኦሮሞ


*ዱሜሳ ታኢ፥ ዋቃ ኡዊሳ፤*
*ጨቆርሳ ታኢ፥ ለፊ ኡዊሳ።*


❖

ደመና ሁን፥ ሰማዩን አልብሰው፤
ሰርዶ ሁን፥ መሬቱን አላብሰው።

**የኦሮሞ ሽማግሌዎች ምርቃት**



የደቡብ ኢትዮጵያ ኦሮሞዎችን ያጠና አይኬ ሃበርላንድ።

(ፎቶግራፉ አንሺ፡ Karl Heinz Striedter, Frobenius-Institut)

*"ዜናሁ ለጋላ"ን እና ስለኦሮሞዎች የሚባለውን በይበልጥ ለመረዳት መነጋገሪያ ሊሆኑ የሚችሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች እንዳስፈላጊነቱ በዚህ ምዕራፍ ባጭሩም በረጂሙም እየተቸሁ አቀርባቸዋለሁ።*

## (1) ጋላ ወይስ ኦሮሞ

ኦሮምኛ ተናጋሪዎች "ጋላ" የሚለውን ስም ከመጥላታቸው በፊት ጀምሮ የነገድ ስማቸው "ኦሮሞ" እንደሆነ ይናገራሉ። ሌሎችም ኦሮሞ እንዲሏቸው ዛሬ ገፋበት እንጂ ስሙ ከጥንት የኖረ ለመሆኑ ባዔ ምኒልክ ዘመን የነበሩ አቶ ዐፅሜና አለቃ ታየ ይመሰክራሉ። የታሪክ ምንጮቹ ግን፥ በዚያውም ተያይዞ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሌሎችም፥ የሚጠሯቸው "ጋላ" እያሉ ነው። በዚህ ድርሰቴ ውስጥ ሁለቱ ስሞች እየተፈራረቁ ቢመጡ "ጋላ" የምንጮቹ "ኦሮሞ" የኔ አጠራር ሆነው ነው።

## (2) የጋላ ትርጉም

"ጋላ" ማለት ትርጉሙ ምን እንደሆነ አይታወቅም፤ የማይታወቀውን ለማወቅ ብዙዎች (ዘመናዊ ጸሐፊዎች ሳይቀሩ) ሲሞክሩ ይታያሉ። አንደኛ፥ ቀደም ብለው የወጡ የሕዝብና የቦታ ስሞች ትርጉማቸው በጊዜው ሳይመዘገብ ከቀረ ወይም በቋንቋችን ውስጥ ሕያው ካልሆነ የተጸውዖ ስም ቢሆኑም እንደ "ዛፍ"፥ "ጠላ"፥ "ፈረስ" የዘመን ርዝመት ትርጉማቸውን ደብቆባቸዋል። ግን እንደሰው ስም እንደ "አስፋ"፥ "መሐመድ"፥ "ገለታ"፤ እንደቦታ ስም እንደ "አህያ ፈጅ"፥ "ነጭ ሣር"፥ "ዶሮ ማነቂያ"፥ "አሐዱ ዕዕ" የተጸውዖ ስሞች ስለሆኑ ትርጉማቸው ያልጠፉ እየመሰለን ለማወቅ እንፈልጋለን። ስንፈልግ ሰዉ ዝም ብሎ የፈጠረውን ትርጉም እናገኝና እውነት አድርገን እንይዘዋለን[1]። "ጋላ"፥ "አማራ"፥ "ሸዋ"፥ "ጐጃም"፥ ወዘተ በሚሉት ስሞች ላይ የደረሰው ይኸው

---

1. የኔ ብጤው መምህርም "ይኸንን የፈጠራውን ታሪክ ለዕውቀቱ ያህል ዕወቁት፤ እንደ እውነተኛ ታሪክ መተረካችሁን ግን ተው" ቢለን እሺ አንለውም። ለምሳሌ፥ "ጠመንጃ" ማለት "ጠብ መንጃ" ከሚለው የመጣ ነው የሚለውን ማስጣል አልተቻለም። ዘመኑ የመምህር ቃል የማይከበርበት ዘመን በመሆኑ፡ "ጠመንጃ"/"ጠበንጃ" የቱርክ ቃል ሆኖ ከኛ የደረሰው በዓረብኛ በኩል ነው፥ የዚህን የቱርክ ቃል ትርጉም "ጠብ መንጃ" ለማድረግ መጀመሪያ ቱርኮችን አማርኛ ተናጋሪዎች ማድረግ ያስፈልጋል" ቢባልም ብዙ ሰሚ አልተገኘም።



የደቡብ ኢትዮጵያ ኦሮሞዎችን ያጠና አይኬ ሃበርላንድ፡፡

(ፎቶግራፍ አንሺ፡ Karl Heinz Striedter, Frobenius-Institut)

ነው፡ እውነተኛ ትርጉማቸው እስካሁን አልተገኘም:: "ዛፍ" ለምን "ዛፍ" እንደተባለ ምክንያት ቢኖረውም፥ ያንን ምክንያት አሁን እንደማናውቅ፡ ለእነዚህ ነገዶችና ቦታዎች ለምን ይኸ ዓይነት ስም እንደተሰጣቸው የሚታመን ዕውቀት የለንም::

"ጋላት" የሚል የግዕዝ ቃል አለ፤ ግን "ጋላ" ከግዕዙ "ጋላት" ጋራ ግንኙነት ይኑረው አይኑረው እርግጠኛ አይደለሁም:: በግዕዝ "ጋላት" ብዙ ቍጥር ሆኖ ትርጉሙ "ጭፍሮች" ማለት ነው:: ወደኋላ ዘመን የተጻፉት ካልሆኑ በቀር ቀደም ያሉት ምንጮች አሮሞዎችን ባንድም በብዙም "ጋላ" ይሏቸዋል፤ ብዙዎቹን "ጋላት" ("ጭፍሮች") ወይም "ጋሎች" የሚሏቸው ሁሌም ባይሆን አብዛኛውን ጊዜ የቅርቡ ዘመን ምንጮች ናቸው፤ ስለዚህ "ጋላ" የ"ጋላት" ነጠላ ቍጥር ነው ለማለት አያስደፍርም:: አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም "ጋላ"ን እና "ጋላት"ን ሳያያይዙ ለየብቻቸው የመዘገቧቸው ስለዚህ ነው[2]::

ይህም ሆኖ፥ "ጋላት" የ"ጋላ" ብዙ ቢሆን ተስማሚው ነው፤ ምክንያቱም አንደኛ፥ የስሙን ጥንታዊነት ያሳያል፤ ሁለተኛም፥ ምንጮቹ "ጭፍራ" የሚለውን ከአሮሞዎች የተወሰደ ቃል አድርገው ትርጉሙ "የእሮምታ፥ በአንድነት የግር ብሎ ሰልፍ" ማለት እንደሆነ ይናገራሉ:: "በጭፍራ አምሳለ ጋላ" ማለት "እንደ ጋላ በጭፍራ (በተናጠል ሳይሆን በአንድነት፥ በእሮምታ ለመውጋት መሰለፍ)" ማለት ነው::

የግዕዙ ምንጮች እስላሞችን "እስላም" ወይም "መለሳይ"፥ አሮሞዎችን "ጋላ" ስለሚሏቸው "ጋላ" የሚሉት ክርስቲያንም እስላምም ያልሆነውን ነው ያሰኛል:: ግን አሮሞ ያይደሉትንና ክርስትናን ወይም እስልምናን ያልተቀበሉትን ሌሎቹን ኢትዮጵያውያን "ጋላ" አይሏቸውም:: "ጋላ" የሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የጋራ ቋንቋ ያላቸው ሰዎችም (የነገድም ስም) መሆኑ አያጠራጥርም:: ክርስትናን ወይም እስልምናን የተቀበሉትንም ባህላቸው፥ ቋንቋቸው አሮምኛ እስከሆነ ድረስ "ጋላ" ይሏቸዋል::

## (3) የአሮሞ አንድነት

ሆኖም ይህ ሁሉንም "ጋላ" ብሎ ጠቅላላ አጠራር አሮምኛ ተናጋሪዎች አንድ ቤት (ቤተ ጋላ) ለመሆናቸው ማስረጃ አይሆንም:: ታች ታች ግብጽ (Lower Egypt) በአስቄጥስ ገዳማት የሚኖሩትን መነኮሳት ከምዕራብ በኩል እየመጡ የሚዘርፏቸውን በርበሮች መጽሐፎቻችን "በርበር የሚባል ጋላ" ይሏቸዋል[3]:: በርበሮችንና አሮሞዎችን በአንድ ስም እንዲጠሯቸው ያደረጋቸው ምንድን ነው? "ፈረንጅ" እንደማለት ነው፤ ለኛ ይምሰለን እንጂ ፈረንጆች የምንላቸው ሁሉ አንድ ቤት (ቤተ ፈረንጅ) አይደሉም::

2. ኪወክ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ* ገ. 317::
3. ለምሳሌ፥ *ውዳሴ ማርያም ቅዳሴ ማርያም*፡ ገ. 206-11::



ሌላ ምሳሌ፡ ከአውሮፓ መጥተው አሜሪካውያን የሆኑት ("ፈረንጆች") ቀድመዋቸው አገሩን የያዙትን "ኢንዲያንስ" ("ህንዶች") ይሏቸዋል:: "ህንዶቹ" ግን "ህንዶች" መባላቸውንም ሆነ እንደ አንድ ሕዝብ መታየታቸውን አይቀበሉም:: ተስማሚው ምሳሌ ግን የዓረቦች ሁኔታ ነው:: አንድ ቋንቋ (ዓረብኛ)፥ አንድ መንፈሳዊ መሪ (ነቢዩ መሐመድ) አላቸው፤ ሲጀምሩም ብዙ ጎሳ ግን አንድ ነገድ ወይም አንድ ሕዝብ ነበሩ:: በኋላ እንደ ሱዳን ያሉትን ሌሎች ሕዝቦች ሃይማኖታቸውንና ቋንቋቸውን በማውረስ አሳረቧቸው (ዓረቦች አደረጓቸው):: ምንጮቹ የአሮሞዎቹን ሁኔታ በዚህ መልክ ነው የሚያቀርቡት፤ ለምሳሌ፥ "ጋላ ዘይብልዎ ቦረን" ("ቦረን የሚባል ጋላ") ማለት "ጣሊያን የሚሉት ፈረንጅ" ወይም "ናቫሆ የሚሏቸው ህንዶች" እንደማለት ነው:: አለቃ ታየ ገብረ ማርያምም ይህን ልብ በማለት የሚባለውን ሲነግሩን፥

> ከዚያ (ጌታቸውን አዝማች እንድርያስን ከገደሉበት) ዘመን ጀምሮ እስከ አፄ መለክ ሰገድ (ሠርፀ ድንግል) ዘመን ድረስ በክርስቲያንና በጋላ መሀከል ሁለግዜ ጠብና ጦርነት፥ ሁከት፥ መጋደልም ሆነ፤ ስለዚህም እነዚያ በጋላን ወንዝ ስለነበሩ ጋላ ተባሉ:: የጋላ ወገንም ሁሉ በጥቅሉ በዚህ ስም ጋላ ተባለ:: ጥንት ግን የጋሎች በጥቅሉ ባንድ የሚጠሩበት ስም አልነበራቸውም፤ ባባቶቻቸው ስም በየነገዳቸው በርቱማ ቦረና ይባሉ ነበር ይላሉ

ብለው ነግረውናል[4]:: ይህ እምነት የነበረው አሮሞዎች አንድ ስም ቢኖራቸው ባይኖራቸው ልዩነት በማያመጣበት ዘመን ስለሆነ ታሪኩ ሊታመን የሚችል ይመስላል፤ ፖለቲካ የለበትም::

ሆኖም ባህልን፥ በተለየም ቋንቋን፥ መገመቻ ካደረግን አሮምኛ ተናጋሪዎች አንድነት ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም፥ አንድ ስም ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም፥ ሲጀምሩ አንድ ዓይነት ሕዝብ ነበሩ:: አባ ባሕርይም እንዷንድ ሕዝብ ነው የሚያይዋቸው::

## (4) አሮሞዎች ከሌሎች ይለያሉ?

አሮሞዎች ኢትዮጵያ ከታዩበት ጊዜ ጀምሮ "ሲዳማ" ከሚሉት ሕዝብ ጋራ (ከሲዳሞች፤ ከአማሮች፥ ከአገዎች፥ ወዘተ) በፍቅርም በጠለፋም ይጋቡ ነበረ:: በሃይማኖት ካልሆነ "ሲዳማዎች" "ጋሎችን" በዘር እኩዮችና ተመሳሳዮች እንጂ ልዩዎች ወይም ከፍተኞች ወይም ዝቅተኞች አድርገው አላዩዋቸውም:: ቋንቋቸው ኩሳዊ ወይም ካማዊ ስለሆነ ለሱማሌዎች፥

4. JE692E, p. 582. ከአዝማች እንድርያስ ጋራ ስላደረጉት ግጭት የሚባለው ከዚህ ቀጥሎ (ቍጥር 6 ውስጥ) ተጽፏል:: ስለ JE692E ገጽ 60፥ ኅዳግ ቍ. 21ን ተመልከት::

ለአገዎች ለቤጃዎች በአንደኛ ደረጃ፡ ቋንቋቸው ሴማዊ ለሆነ ለአማሮች፡ ለትግሬዎች፤ ለጉራጌዎች፤ ለአደሬዎች እና ቋንቋቸው ኦሜታዊ ለሆነ ለኦሜቶዎች፥ ለጊሚራዎች፥ ለጃንጀሮዎች በሁለተኛ ደረጃ ያቀርባቸዋል። ኩሳዊ/ካማዊ፥ ሴማዊ፥ ኦሜታዊ እነዚህ ሶስቱ በከፍተኛ ደረጃ "ወንድማማች አባት ቋንቋዎች" መሆናቸው ነው። የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ዝምድናቸው የአንድ አባት ወይም የአንድ አያት ልጆች እንደመሆን ማለት ነው። የረጅም ጊዜ ምርምር ያደረገውን ጀርመናዊውን አይኬ ሃበርላንድን፥ "ዛሬ የሰሜንና የደቡብ ባህላዊ ተቃርኖ ቢኖላም፥ ኢትዮጵያ አንድ አንድነት ያለው ባህል አገር ሆናለች"[5] ከሚል እምነት ያደረሰው የሕዝቡ መዛመድ ነው።

በዚህ አጋጣሚ ሁለት ነገሮች ማስታወስ ያስፈልጋል፤ አንደኛ፥ ኩሳዊ/ካማዊ ቋንቋዎች ከአፍሪካ ውጪ ተናጋሪ የላቸውም። ፍጹም አፍሪካውያን ናቸው። የውጪ ለመሆን ሐሜት እንኳን ቢመጣ ከአፍሪካ ውጪ ተናጋሪ ባላቸው በሴማዊ ቋንቋዎች እንጂ በኩሳዊ/ካማዊ ሊመጣ አይችልም። ሁለተኛ፥ ኦሮምኛ ከሱማልኛ፥ ከቅማንትኛ (ከአገውኛ) ወዘተ ጋራ ያንድ አባት ልጅ ከሆነ ኦሮሞዎቹን ከነዚህ ለይቶ በቅርብ ጊዜ ከወዲያ ማዶ መጡ ለማለት ያስቸግራል።

አይኬ ሃበርላንድ ስለ ጋዳ ሥርዓት የሰጠውን (ከታች በኅዳግ ቍጥር 28 ስር የጠቀስኩትን) አስተያየት እዚህ ከጠቀስኩለት ጋራ አቀራርበን ብናየው የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያለ አንድ ትልቅ እንቆቅልሽ ሊፈታልንም ይችላል። እንደምናስታውሰው፥ የአክሱም "ነገሥታት" ስም "እለ" የሚል መነሻ አለው፤ ለምሳሌ፥ "እለ ዓሚዳ"፥ "እለ አለዳ፥ "እለ አዝጓጓ"፥ "እለ ገበዝ" የሚባሉትን "ነገሥታት" እናስታውስ። የ"እለ" ትርጕሙ "እነ" ነው፤ ብዙ ቍጥርን ያመለክታል። ሁለተኛ፥ በዚህ ቃል ከሚጀምሩ ስሞች

5. Haberland, *Untersuchungen*, p. 219. ሃበርላንድ በደቡብ ኢትዮጵያ ክርስትና ተስፋፍቶ እንደነበረ ለማስረዳት ንግግር ሲያደርግ ደግሞ እግረ መንገዱን እንዲህ ይላል፤ "Die so häufig zu findende Apostrophierung der Amhara als "Semiten" im rassischen und auch im kulturellem Sinne ist rein Phantasie. (Es ist unmöglich, einen linguistischen Namen auf den rassischen Befund zu übertragen). Die meisten Völker Äthiopiens, wie z. B. die Galla oder die Kaffa oder die Agau -- die Urbevölkerung Nord-Äthiopiens --, haben das gleiche Aussehen wie die Amhara und Tigray" ("ይኸ ብዙ ጊዜ የሚገኘው አማሮችን በዘርና በባህል ረገድ ከሴማውያን ማገጣጠም ፍጹም ቅዠት ነው። (አንድን የቋንቋ ስም ወደ ዘር ግኝት ማስተላለፍ አይቻልም።) አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ለምሳሌ ጋሎች ወይም ከፋቾች ወይም -- ሰሜን ኢትዮጵያን በጥንታዊ ሕዝብነት የያዙ -- አገዎች መልካቸው ያው የአማሮቹና የትግሬዎቹ ዓይነት ነው።") Eike Haberland, "Altes Christentum in Süd-Äthiopien", p. 3.



ጋራ አብሮ የሚሄደው ግሥም ብዙ ቍጥር ነው፡ ለምሳሌ፡ "ነግሡ" (ነገሡ)፡ "ሞቱ" (ሞቱ) ይላል።

"እለ" እና ግሡ የሚያመለክቱት ብዙነትን ከሆነ፥ ይህ አክሱማዊ የገዢ ስም አወጣጥ አባ ባሕርይ በክፍል 4 ስለ ሉባ ከጻፉልን ኦሮማዊ የገዢ ስም አወጣጥ ጋራ ተመሳሳይ ነውኮ። እነዚህ ስሞች የነገሥታቱ ሳይሆኑ እንደ "ሥሉስ ኀይሌ"፥ እንደ "ሜልባሕ" የገዢው ሠራዊት ስሞች ይመስላሉ። "ግሡ ብዙ ቍጥር የሆነው ንጉሡን ለማክበር ነው" የምንለው ቢቸግረን ነው፤ በግዕዝ ሲጻፍ ንጉሦችን በብዙ ቍጥር ግሥ ማክበር የተጀመረው በቅርብ ጊዜ ነው።

ዛጔዎችም ተመሳሳይ የዓውደ ግዛት (ጋዳ) ሥርዓት ሳይኖራቸው አይቀርም። ለምሳሌ፥ የግዛት ዘመናቸው የተመዘገበ ሁለት የነገሥታት ዝርዝር አለ። ባንደኛው ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት 11 "ነገሥታት" 7ቱ፡ በሁለተኛው ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት 9 "ነገሥታት" 8ቱ 40 40 ዓመት ገዝተዋል። ይህ 40 ዓመት ዓውደ ግዛት መሆን አለበት። አለዚያማ ይህ ሁሉ ተመሳሳይነት እንዴት አጋጣሚ ሊሆን ይችላል። የጸሐፊዎች ፈጠራ ነው የሚል ትርጕም መስጠትም አያረካም።

ባጭሩ፥ ኢትዮጵያ ሀገርነቷ የነገደ ኩሳ ነው፤ ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ቋንቋቸውን ገፈፍ አድርገን ብናያቸው አብዛኞቹ አገዎችና ቤጃዎች ናቸው፤ ልብ አላልነው እንደሁ፥ በጌምድር ማለት ምድረ ቤጃ ማለት ነው። አንዳንድ የታሪክ ምንጮች በጌምድርን እንደ "አገው ምድር" "በጀ ምድር" የሚሉትን እናስታውስ። የግዕዙና የዐረብኛው ምንጮች ኢትዮጵያንና ሐምን/ካምን አንድ ያደርጓቸዋል።

ይኸ ስለቋንቋዎች አመሠራረት ነው። ዛሬ ማን የማንን ቋንቋ ቋንቋዬ ብሎ እንደያዘ ለማወቅ ወደ ታሪክ፥ ወደ አንትሮፖሎጂ፥ ወደ አርኬዎሎጂ መሄድ ያስፈልጋል። በዚያን ጊዜ ኦሮሞነትና አማራነት ከዳቦው ውስጥ እርሾው ሆነው የቀረው ትልቁ የዳቦው ክፍል የኢትዮጵያ ነገዶች ውሕደት ሆኖ ያገኘዋል። የምርምሩን ውጤት ለማወቅ የሚጓጓ በጌምድርን፥ ጎጃምን፥ አምኃራን፥ ወለቃን፥ ፈጠጋርን፥ ያጥለቀለቁት ኦሮሞዎች አማራ እንደሆኑ፤ ኦሮሞዎች ደቡቡን ስላጥለቀለቁት ጉጂ፥ እናርያ፥ የአሩሲ ሐድያዎች ኦሮሞዎች እንደሆኑ ይረዳል። እዚህ ድርሰት ውስጥም በመጠኑ አንዳንድ ምልክት እናገኛለን።

"የምናገረው ቋንቋ የጥንት አያቶቼ ቋንቋ ነው" የሚል ሊሳሳትም ላይሳሳትም ይችላል፤ በጭለማ ማነጣጠር የሚሉት ዓይነት ነው። ክቡር አቶ ዐማኑኤል አብርሃም በትዝታቸው መጽሐፍ ውስጥ ባባቴም በናቴም ኦሮሞ ነኝ ያሉት ወላጆቻቸው ኦሮምኛ ሲነጋገሩ ስላገኟቸው መሆን አለበት። ቋንቋዎቻችን እንደልብስ የሚቀያየሩ ሆነዋል፤ በበጋው ወራት እንዳንቸገር ሰውን በክረምት ወራት በለበሰው ልብሱ አንከፋፍለውም።

## (5) "ጋላ" ስድብ ነው?

አንድ ቋንቋ የሚናገር ሕዝብ ሌላ ቋንቋ የሚናገውን ሕዝብ የሚጠራበት ስም ይኖረዋል። ያንን ስም ወይም ከተጠሪዎቹ ያገኘዋል፥ ወይም በአንዳች ምክንያት ይፈጥረዋል፥ ወይም "በሙዝገበ ቋንቋ" ውስጥ ካሉት ቃላት አንዱን የሚስማማ የሚመስለውን ቃል ይመርጠዋል። "አፍሮ አይገባ"፥ "ሥሉስ ኃይሌ"፥ "ኃይላት"፥ "አርባብ"፥ "ቍርባን" ወዘተ እያሉ ለጦር ሠራዊቶቹ የሚሰጧቸውን ስሞች እናስታውስ። ያ እንዲህ ሆኖ የወጣው የሕዝብ ስም በኋላ በአንዳች ታሪክ ምክንያት (**"ጀግናው የእገሌ ሕዝብ"**) እየተባለ መደነቂያ ወይም (**"አይ የእገሌ ሕዝብ ነገር"**) እየተባለ መሰደቢያ ይምሰል እንጂ ሲወጣ **"እገሌ"** ይህን ዓይነት ትርጉም እንዳለው ማስረጃ አይገኝም።

እርግጥ ጠላት የጥላቻ ስምም ያወጣል፤ አባ ባሕርይ እንደነገሩን፥ ለቦረን ኦሮሞዎች አንዱ ክፍል "ዳዌ" የሚለውን ስም ያወጡላቸው ኦሮሞዎቹ ሳይሆኑ ሌላው ሕዝብ ነው (የድርሰታቸውን ክፍል ፲፫ ተመልከት)። ይህ የነገድን ስም ስድብ አድርጎ አነጋገር ደግሞ ብዙ ነገዶች በሚኖሩበት አገር ዐዋጅም የማያቆመው በሕይወት (በነገድነት) የመቆያ የሰው ልጅ ጠባያዊ ዘዴ (survival) ነው። ሆኖም፥ "ጋላ" ለስድብ የወጣ ስም ለመሆኑ ምንም ማስረጃ የለንም።

ዛሬ "ጋላ" ስድብ ነው ሲባል እሰማለሁ እንጂ ባደግሁበት አካባቢም ሆነ በማውቃቸው ምንጮች ዘንድ ቃሉ እንደ ማንኛውም የሕዝብ ስም ገለልተኛ መጠሪያ እንጂ ስድብነት የለበትም። ባደግሁበት አካባቢ እረኞች ስንከባበር በአማርኛ "አማራ" እና "ጋላ"፥ በኦሮምኛ "ሲዳማ" እና "ኦሮሞ" እንባባላለን፤ ስንናናቅና ስንሰዳደብ ደግሞ "ጋሎ ..." እና "ሲዳምቲቲ እነና ... " እንባባላለን። ቤተሰቦቻችን ተቈጥተው አቁሙ የሚሉን "ጋላ"፥ "ሲዳማ" መባባሉን ሳይሆን "ጋሎ" እና "ሲዳምቲቲ" መባባሉን ነው።

በነገዱ የተሰደበ ሁሉ የነገዱን ስም ቢለውጥ ዓለም ዝብርቅርቋ ይወጣ ነበረ። ጎሳዎችና ነገዶች ዝብርቅርቃቸው ቢወጣ ሳይሻል ይቀራል? በአሁኑ ዘመን ብዙ አማሮች "አማራ" እንዲባሉ አይፈልጉም። ምክንያታቸው ግን ኦሮሞዎች "ኦሮሞ እንጂ ጋላ አትበሉን" ከሚሉበት ምክንያት የተለየ ነው፤ "አማሮች" አማራነታቸውን አይክዱም፤ አማራ መባልን የማይፈልጉት ጎሰኝነት ኢትዮጵያዊነትን ሲቀናቀን ስላዩ ነው እንጂ ስድብነቱን ለመሸሽ አይደለም። አማሮች፥ ኦሮሞዎች ኦሮሞ መባልን የሚፈልጉትን ያህል አማራ መባልን አይፈልጉትም። ምርጫቸው ኢትዮጵያዊ መባል ነው። ግን አማሮች ኦሮሞዎችን ራሳቸው ኦሮሞዎቹ በፈለጉት ስም ለመጥራት ሲጥሩ፥ እነሱ አማሮቹ አማራ መባልን እንደማይፈልጉ እያወቁ "አማራ" ይሏቸዋል።



የ"ጋላ" ሕዝባዊ ትርጕሞችም ቢሆኑ እውነትነት ባይኖርባቸውም ደጋጎች ናቸው። አንዱ፡ "ነቢዩ መሐመድ እስልምናን እንዲቀበሉ ቢልኩባቸው (ለእነማ?) መልክተኞቹ ሲመለሱ ለነቢዩ ያመጡላቸው መልስ ነው፡ በአፍሪካዊ ዐረብኛ፥ "ጋል ላ" ("እምቢ አለ") የሚለው ነው። (በዐረባዊ ዐረብኛ ቢሆን "ቃለ ላ" ይሆን ነበረ።) ሌላው፥ "ነገዱ የመጣው ገላን ከሚባል ከሀገሩ ወንዝ ስለሆነ በወንዙ ስም ጋላ ተባለ" የሚለው ነው። ያም ይኸም ስድብ የለበትም።

ያም ሆነ ይህ፥ ዛሬ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች "ጋላ ስድብ ነው፤ ስትጠሩን ኦሮሞ በሉን እንጂ ጋላ አትበሉን" ካሉ ፈቃዳቸው ይሁንላቸው።

ኦሮሞ መባል ትክክል ቢሆንም በአማርኛ ስንነጋገር በደስታ እንድንጠቀምበት ተገንጣይ ኦሮሞዎችን እንዳያስታውሰን ኦሮሞዎች ነን የሚሉ አስፈላጊውን ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ሁለተኛው ድክመት ሌላ ቋንቋ እየተናገሩ አማርኛን እናርም ማለት ነው። ጀርመኖች ጀርመን አትበሉን፥ ስዊድኖች ስዊድ አትበሉን አይሉም፤ ሁሉም በመሰለው ሲጠራቸው ተቀብለውታል። እነሱ ግን ራሳቸውን ለራሳቸው ባወጡት ስም ይጠራሉ። ዋናው ነገር ከመግባባቱ ላይ ነው። እርግጥ አንድ ሰው በኦሮምኛ ሲነጋገር "ጋላ" ቢል አያምርበት ይሆናል።

ከላይ እንደጠቀስኩት ወደኋላ ዘመን የተጻፉት ካልሆኑ በቀር ምንጮቹ "ጋላ"ን ላንድም ለብዙም ይጠቀሙበታል። ለምሳሌ፥ "ወመጽአ ጋላ" ሲሉ እንደሁኔታው "ጋላ መጣ" ወይም "ጋሎች መጡ" ማለታቸው ሊሆን ይችላል። ስለዚህ፥ *ዜናሁ ለጋላ* እና ከምንጮቹ የምቀዳቸውን ሌሎቹን የግዕዝ ጥቅሶች ስተረጕም ከ"ጋላና" እና ከ"ጋሎች" አንዱን የምመርጠው እንደ ሁኔታው ለአማርኛ ተስማሚውን ነው። ለግዕዙ የተቻለውን ያህል ለመቅረብ ስል በነጠላ አነጋገር "ሕዝቡ" እንደሚባለው፥ "ጋላው" የምልበትም ጊዜ አለ።

## (6) የጋላ/የኦሮሞ ዜና ለምን ተጻፈ?

ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ የብዙ ነገዶችና ጎሳዎች ሀገር ሆና ሳለ በግዕዝ ስላንዳቸውም ተለይቶ ኦሮምኛ ስለሚናገሩ ኢትዮጵያውያን (ስለ ጋላ) የተጻፈውን ያህል አልተጻፈም። ከሌሎቹ ይልቅ ስለኦሮሞ በይበልጥ ለማወቅ የቻልነው በምን ምክንያት ነው? በሌላ አነጋገር፥ ታሪክ ጸሐፊዎቻችን ስለሌሎቹ ኋሳዎች ያንን ያህል የግል ዜና ያልጻፉልን ለምንድን ነው?

መልሱ ቀላል ይመስለኛል። ጸሐፊዎቻችን ስለ ሌሎቹ ጎሳዎች ብዙ ያልጻፉልን የመጻፍ ፍላጎት ሳይኖራቸው ቀርቶ ሳይሆን ስለነሱ ብዙ የሚያውቁት ስለሌላቸው ነው። ሌሎቹ ጎሳዎች ወይም ነገዶች ኢትዮጵያውያን የሆኑት ታሪክ ጸሐፊዎቻችን ከመገኘታቸው በፊት ነው።

ጸሐፊዎቹ እነዚህን ነሳዎችና ነገዶች ኢትዮጵያ ውስጥ አገኟቸው እንጂ ወደ ኢትዮጵያ እንዴትና በየት በኩል እንደመጡ አላዩም፤ ያየም አላገኙም፡፡ እንዲህ ከሆነ ስለማያውቁት ነገር ምን ብለው ይጻፉልን? "የኢትዮጵያውያን አባታቸው ኢትዮጲስ ይባል ነበረ፡፡ የነገደ ዮቅጣን፥ የነገደ ኩሳ ልጆች በዚህ ወጥተው በዚያ ወርደው ኢትዮጵያ ሰፈሩ፥ ወዘተ" የሚሉ ታሪኮች ሁሉ ያላየ፥ ያልሰማ የነገረን ገና የምርምር ማስረጃ ያልደገፋቸው ከአፍ ወደ አፍ የተላለፉ ቅርሶች ናቸው፤ የአንድ ሰው የአንድ ዘመን ጣፋጭ ፈጠራ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ብዙ ያፍ ታሪኮች በምርምር መስቀልኛ ጥያቄ ሲወጠሩ በድቡሽት ላይ እንደተሠራ ቤት ይንኮታኮታሉ፡፡ ቅርሶች ስለሆኑ ግን ከመዝገብ አይፋቁም፡፡

ስለኦሮሞዎች የምናውቀው ከዚህ በፍጹም የተለየ ነው፤ ምክንያቱም ስለነሱ የተጻፈው ወደ ማህል ኢትዮጵያ ሲገቡና ከገቡም በኋላ ምን እንዳደረጉ ባዩ የዓይን ምስክር ታሪክ ጸሐፊዎች ነው፡፡ *የዜናሁ ለጋላ* ደራሲ ክፍል ፩ ላይ፥ "እንደዚሁ ባሊን መውጋት በጀመረበት ጊዜ የተገዘረው (ሉባ) ሜልባሕ ይባላል፡፡ የአባቱን ስም አላውቅም፤ ምክንያቱም የሚነግረኝ የለም" ያሉትን እዚህ ላይ እናስታውስ፡፡

ይኸም ሆኖ፥ ስለ ኦሮሞዎች ካፍ ታሪክ የሚቈጠር ብዙ ተጽፏል፡፡ ሁለቱ እንዲህ ይላሉ[6]፤

6. (1) EMML 7346, ff. 13a-14a; (2) EMML 1521, pp. 55-6, Getatchew Haile and William F. Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*, Vol. V, p. 20. አፄ ገላውዴዎስ ግራኝ እንደሞተ የፖርቱጋልን ሰዎች (ካቶሊኮቹን) አገር ሰጥቶ ማስፈሩ እርግጥ ነው፡፡ እነሱም ስለገላውዴዎስ ሲናገሩ፥ "ግራኝን ለማሸነፍ እንድንረዳው ሃማኖቱን በናንተ ሃይማኖት እለውጣለሁ ያለውን ቃል አጠፈብን" ይሉ ስለነበረ፥ ለበቀል ኦሮሞዎቹን አርፈው ከተቀመጡበት አስነሥተውበት ይሆናል፡፡ አፄ ፋሲል "ካገሬ ውጡ" ቢላቸው ወንድሙን ማሳመፃቸው በታሪክ የተመዘገበ ነው፡፡ የካቶኞኞሊኮቹ ጳጳስ ሲባረሩ፥ "እግዚአብሔር የሐበሾችን እምቢተኛነት ለመቅጣት መጀመሪያ በግራኝና በአደል እስላሞች እጅ የጣላቸውን ዱላ እና አለንጋ አሁን ለጋሎች እንደሰጣቸውና እነሱም የበለጠ ጨካኝ መቅሠፍቶችና የዚህ ያልለዘበ መንግሥት አውዳሚዎቹ እንደሚሆኑ ገልጾላቸዋል"፥ እሳቸውም "የሀገሬቷን መንግሥቶችና አውራጃዎች የሚወሩና የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ፈጽሞ ለመውደም የሚያደርሱ ጥቁር ጉንዳኖች አሉ" ብለው እርግማንና ትንቢት እንደተናገሩ የሳቸው ሰዎች መዝግበውላቸዋል፤ Beckingham and Huntingford, *Some Records of Ethiopia*, p. 135. አለቃ ታየ ስለኦሮሞዎች የሚነገሩትን እውነት ያልሆኑ ታሪኮች የሚሏቸውን በብዙው ሰብስበዋል፡፡ እዚያ የወይዘሮዋ ታሪክ የተለያየ ትረካ አለው፤ አንዱ እንዲህ ይላል፤ "ባፄ ዓምደ ጽዮን ዘመን (1307-1336) በሃይማኖት የተነካ እጨጌ ፊልጶስ ረግመውት በሀገራችን ጽኑ ረኀብ ሆነ፡፡ በዚያን ጊዜ የቸገራት ሴት ወይዘሮ (ልዕልት) በፈጠጋር ነበረች፡፡ ደግሞ አዝማች እንድርያስ የሚባል የደዋሮና የከተታ መኰንን ነበረ፡፡ የሱም ሳሎ የሚባል የሳም ራስ ባሪያ ነበረው፡፡ ያቺ ሴት ወይዘሮ ቢርባት ወተት ቢያጠጣኝ ብላ ለሳሎ አደረችለት፡፡ እሱም ምሽት አደረጋት፤ ፱ ወንዶች ፫ ሴቶች ልጆች ወለደችለት፡፡ ስማቸውንም የወንዶቹን



(1) አዝማች እንድርያስ የሚሉት መኰንን (አገረ ገዢ) የአርእኝ፥ የደዋሮ፥ የፈጠጋር ጌታ ነበረ፡፡ (የዚያን ጊዜውን) የሳም ራሱን ("ሳም ራስ" የወረዳ ገዥ የማዕረግ ስም ነው) ሳሎ ይሉት ነበረ፡፡ ደኻ ወይዘሮ (ልዕልት) ብታድርለት ሚስት አደረጋት፡፡ ልጅ ብትወልድ ትልቁን ከረዩ አለው፡፡ ተከታዩን ሜጫ አለው፤፥ ሶስተኛውን ቱለማ አለው፤ አራተኛውን ወሎ አለው፡፡

እሊህን አራቱን ምድር እየማሰች፥ ጨርቅ እየጐዘጐዘች አሳደገቻቸው፡፡ እዚያ ሰይጣን አደረባቸው፤ ሌላ ቋንቋ (ኦሮምኛ መሆኑ ነው) ያናግራቸው ገ[ፖ]መር፡፡ ከሰው ሳይገናኙ አደጉ፡፡ ካደጉም (በኋላ) አባታቸውን እያስከተሉ የሰው ከብት (መቀማት) በፍየልና በበግ ዠመሩና ፈረሱን ላሙን (ከብቱን) ያገኙትን ሁሉ ይቀሙ ዠመር፡፡

ሰው ሁሉ ተሰበሰበና እጌታ(ቸ)ው ዘንድ አቤት አቤት አለ፡፡ ጌታቸው ቢሰማ ተዉ አላቸው፥ ስንኳን ይተዉ የጌታቸውን ግትል (ከብት?) አስቀሩ፡፡ ላሙን ይዘው ጋላ የሚሉት ወንዝ አለ፥ ዱር እዚያ ገብተው ዐመፁ፡፡ ጌታ(ቸ)ው ሰዉን ክተቱ አለና ተዋጋቸው፤ ድል ነሡና ጌታቸውን ገደሉ፤ ሰውንም ፈጁት፡፡

ከዚያ ወዲያ የሚቆም (የሚቋቋማቸው) ጠፋ፡፡ (አገሩ) በ፩ ዓመት ሙገር ድረስ ጠፋ፡፡ በ፪ ዓመት ደራ አደረሰው፡፡ በአፄ ኢያሱ ዘመን ወለቃ፥ ሸግላ፤ ወኰሉ አምሐራ እስከ መልዛ ጠፋ፡፡

(እነሱም) በወንዙ ስም ጋላ ተባሉ፡፡

(2) በሡርፀ ድንግልም ዘመን ጋላ ተነሥቶ ክርስቲያንን ሁሉ ይዋጋቸው ጀመር፡፡ እሱም በጥቂት ዘመን እረብቷልና በረታባቸው፡፡

የጋላም አመጣጥ ታሪኩ እንዲህ ነው፡፡ ባፄ ገላውዴዎስ ዘመን ነፍጥ ይዞ የመጣ ፈረንጅ ግራኝ ከሞተ በኋላ ከገላውዴዎስ ጋራ ወደ ሸዋ ሄደ፡፡ ያፄ ልብነ ድንግልን ላም (ከብት) እየጠበቀ ገላን በሚባል አገር ወንዠ ዳርቻ ከሚኖሩ ዘላኖች ጋር ይኖር ጀመር፡፡ ከነዚህም ወገን ሚስት አግብቶ ፪ ልጆች ወለደ፡፡ እነዚህም በዘላኑ ቤት አደጉ፥ በጥቂት ዘመን አካለ መጠን አደረሱ፤ ጐለመሱ፡፡ እነሱም በዘላኑ ቤት በአዳል ከሚኖሩ ከእስላሞች ወገን አገቡ፤ ፺ ልጆች ወለዱ፡፡ እነሱም ፲፪ ነገድ (ሆኑ)፡፡ ገላን በሚባል አገር ወንዝ ስለኖሩ ጋላ ተባሉ፡፡ ሸዋን፤ አማራን፥ ወለቃን፥ ጐጃምን፥ ዳሞትን፤ በጌምድርን፥ እንደርታን፥ ላስታን ሁሉ ወረሱ፡፡ ክርስቲያንን ሁሉ ዙሪያውን ከበቧቸው፡፡

ከረዩ፡ ትሎማ፡ መጫ፡ ወሎ አላቸው፡፡ ሴቶችንም አልኮ፡ ዱረቲ፤ አያንቱ አላቸው" (JE692E, p. 564). ሌላው ታሪክ ሴት ወይዘሮዋን "ያጼ መለክ ሰገድ የእኅት ልጅ ነኔት (መኒት/መና እሥራኤል) የምትባል"፡ ሳሎን ደግሞ "ከጥቁር ምድር ማርኮ ያመጣው" ይላቸዋል፤ እዚያው ገ. 570፡፡ የዚህን ታሪክ ሌላ ትረካ ካኩት *የኢትዮጵያ ዓመታዊ መጽሔት* ውስጥ በ፲፱፻፺፱ ዓ. ም. አሳትሞታል፤ Caquot, "Histoire Amharique de Grañ et des Gallas," pp. 124-132.

ስለ ኦሮሞ የሚታመን ዜና የተጻፈልን ምክንያቱ የኦሮሞዎች ወደ ማህል ኢትዮጵያ ሲመጡ ጸሐፊዎች ስላዩዋቸውና አመጣጣቸው የመንግሥቱና የክርስቲያኑ ሕዝብ ወገን የሆኑ ጸሐፊዎችን ለጽሕፈት የሚጋብዝ ሆኖ ስለተገኘ ነው።

ኦሮሞዎች ከደቡብ (ምናልባትም ከደቡብ ምሥራቅ) ተነሥተው ወደ ማህል ኢትዮጵያ የገቡት የሕዝብ ንቅናቄ ከሚወስደው ዘመን ጋራ ሲተያይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው። ሲገቡ ጉዟቸው ከፍ ባለ ጥድፊያ ነበረ። በ1570 ዓ. ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ከአፄ ሠርፀ ድንግል ጋራ ተጋጭተው በአፄ ሱስንዮስ ዘመን (1600-1625) አገሩን እስከ ትግሬ ድረስ እንደአጥለቀለቁት፥ ሕዝቡንም እንደአርበደበዱት እንመልከት[7]፤

*ወእምድኅረ ኀልፈ ክረምት በወርኃ ጥቅምት ኮነ ሁከት ዓቢይ በውስተ ኵሉ ሀገረ መንግሥት ፡፡ ወተሰምዓ ከመ ከረዩ በምልኡ ወረደ መንገለ ትግሬ፥ ወመረዋ ወፅኣ መንገለ በጌምድር፥ ወከመ ኢቱ ወቦረን ይፈቅዱ ፀቢአ ጐዣም።*

❖

ክረምት ካለፈ በኋላ በጥቅምት ወር በመንግሥቱ ሀገር[8] ሁሉ ትልቅ ሁከት ሆነ፤ ከረዩ በሙሉ ወደ ትግሬ እንደ ወረደ፥ መረዋ ወደ በጌምድር እንደ ወጣ ኢቱና ቦረን ጎጃምን ሊወጋ እንደሚፈልግ ተሰማ።

ኦሮሞዎች ወደሰሜን ሲገፉ መንገዱ የቀናቸውና ሀገሪቷን በአጭር ጊዜ ውስጥ ያጥለቀለቋት ስለተደራጁ እንጂ ተቃዋሚ ስላልነበረባቸው ወይም "ሰርዶ ሁን መሬቱን አላብስ" ተብለው በመመረቃቸው ያገኙት የቍጥር ብዛት የወረሩትን አገር ሕዝብና የጊዜውን መንግሥት ለማሸነፍ የሚያስችላቸው ሆኖ አይደለም። ቍጥራቸውን አቅም ያደረገላቸው አሸንፈው ከወረሩት ሕዝብ ያጠፉትን አጥፍቶ የተረፈውን ኦሮሞ የማድረግ ችሎታቸው ነው። አንድ አገር በያዙ ቍጥር "ሲዳማ" ከሚሉት ነባር ሕዝብ ግማሹን ደምስሰው የቀረውን ቋንቋቸውንና ባህላቸውን በማውረስ እንደነሱ ኦሮሞ ያደርጉታል፤ "ሲዳማነቱ" ይቀራል፤ ከተወራሪነት ወራሪነትን ስለሚመርጥም ኦሮሞ ሆኖ አብሮ ወረራ ይወጣል። ለምሳሌ ዛሬ ከኦሮሞ ነገድ ውስጥ ገብተው የሚቈጠሩት እነ

7. Pereira, *Chronica de Susenyos*, p. 165.
8. "ሀገረ መንግሥት" ("የመንግሥት ሀገር") የሚሉት "ጻር አገር" የማይሉትን፡ ማእከላዊው መንግሥት (ንጉሡ) የራሱን ሰው በነጋሪት (በዐዋጅ) የሚሾምበትን ክፍለ ሀገር ነው፡ ሁለቱን አስተዳደሮች አንዱን "ሀገረ መንግሥት" ሌላውን "ምድረ ግብር" ይሏቸው እንደነበረ በዘርአ ያዕቆብ ታሪክ ውስጥ ይታያል፤ Perruchon, *Les Chronique de Za'a Ya'eqob*, p. 15. ንጉሡ የሁለቱም አስተዳደሮች የበላይ መሆኑን ለማመልከት "ንጉሠ ጽዮን፤ ንጉሠ ነገሥት



ሰዮ፥ አቦኖ፥ ቱምኤ፥ ሌቃ፥ ሐገለባቦ፥ አቦ፥ ሐርሱ፥ ሊሙ ኦሮሞነታቸው "በጥምቀት" እንጂ በዘር እንዳይደለ ብላታ መርስዔ ኀዘን ይናገራሉ። ይኸ ልክ የአማራ ባህል (ቋንቋውና ሃይማኖቱ) በሀገሪቱ ሰሜንና ማእከል እየተስፋፋ ሌሎቹን አማራ እንዳደረጋቸው ማለት ነው።

ማስረጃ የለኝም እንጂ ለኦሮሞዎች ድል አድራጊነት ሌላም ምክንያት እጠረጥራለሁ። ሕዝቡ የመንግሥቱ ጨቋኝነትና ዘራፊነት ስለመረረው ኦሮሞዎች እንዲመቱት ረድቶ ይሆናል። ታሪክ ጸሐፊው የአገዛዙን መራርነት ሲመዘግብ እንዲህ ይላል[9]፤

ዘድንግል (1596-7) በነገሠ ጊዜ ለኢትዮጵያ ሰዎች ፪ በጉነት ሠራላቸው፤ ፪ ዕዳ ፋቀላቸው፤ ፩ ዕዳ አንበሳ ወደቅ ነው። በቀኝ በግራ ጕኑ የተመሰገነው ከብት በንጉሡ ማኅተም ኢየተተኰሰ ለንጉሡ ይሆን ነበረ። (ዘድንግል፥) "ይህ ዘረፋ ነው፤ እንደ ዓቅሙ ኢየተቋጠረ (ቀረጡን) ፍሪዳ ይክፈል" አለ።

፪ተኛ ዕዳ ገብሮ ገብሮ ሲደኸይ የግብር መሬት ለገዢ ሰጥቶ በጤና መሄድ አልነበረም። የሚከፍለው ገንዘብ አጥቶ ሁለንተናውን ሲጨርስ ልጁን ለግብር ያሳልፍ (ይሰጥ) ነበረ። ልጅ የሌለው ከነምሽቱ ራሱ ባሪያ ሆኖ ይገዛ ነበረ። አጼ ዘድንግል ግን "ሰው ባሪያ፥ ምድር እናሪያ አይሁን፤ ምድር ባሪያ፥ ሰው እናሪያ ይሁን" ብሎ አዋጅ ነገረ። ግብር ሲቸግረው መሬቱን ለገዢው ጥሎ ይሀድ እንጂ ብሎ።

"አንበሳ ወደቅ" ሲሉ ሞአ አንበሳ ከትልቁ በሬ ላይ ጉብ አለ ማለታቸው ነው። ከብቱ "የተመሰገነ" ከሆነ ሁሉም ይወሰድበታል። ከብት በድብቅ ማድለብ አይቻልም።

*የዜናሁ ለጋላን ክፍል ፲፱ ስናነብ እንደምንረዳው ምድሩ የነጌቶች* ሆኖ ገበሬው ተጋዝቶ ገባር ይሆን ነበረ። የአፄ ዘድንግል ትልቁ "በጉነት" መገበር ያልቻለ መሬቱን ለቆ ይሂድ ማለቱ ነበረ፤ አልሆነለትም። መኳንንቱ ገባር ሊያሳጣን ነው ብለው በጦር ልብ እራሱን ብለው ገደሉት።

ይኸ ወንጀል ይፈጸም የነበረው በክርስቲያኑ አገር ነው። ሌላውማ እንደ "ጎንካ እና እንደ ሻንቅላ" ያለው ዘወትር ባሪያ

ዘኢትዮጵያ" ይባል ነበር፤ Perruchon, "Histoire des Guerres d'"Amda Şyon," p. 280. ሀገረ መንግሥት/ጽዮን ዳሞትን፡ ደምቢያን፥ ስሜንን፥ ጎጃምን፥ ሸዋን፥ ትግሬን፡ ምድረ ባሕርን ("ኤርትራን") ይጨምራል። ሀገሮቹ በዓምደ ጽዮን ታሪክ ውስጥ ተዘርዝረዋል፤ እዚያው ገ. 280-1። በሁለቱ አስተዳደሮች መካከል ያለው ልዩነት የዳራገሮቹ የራሳቸው ፈላጭ ቈራጭ ባላባት ነበራቸው። "በእስላም ባሕር ውስጥ የክርስቲያን ደሴት" የሚሉት አነጋገር የሚያመለክተው ጠቅላላዋን ኢትዮጵያን ሳይሆን በተለይ ንጉሡ በዚህ "ሀገረ መንግሥት/ጽዮን" በሚባለው ክፍለ ሀገር የዘረጋውን አስተዳደር መሆኑ ነው።

9. *የጎጃም ታሪክ* EMML 5403, ff. 63b-64a.

የሚታደንበት ጫካ ነበረ፡፡ ታዲያ እንዲህ ያለውን መንግሥት የሚያርበደብድ ኀይል ቢመጣ ተገፊው ምን ይላል? በግራኝ ወረራ ጊዜና በኛስ ሕይወት ተመሳሳይ ነገር አልደረሰምን?

አሮሞዎች ያሸነፉትን እያስገደዱ አገልጋይ ("ገበር") ማድረግንም የወሰዱት ከጠላቶቻቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ቃሉ/ስሙ ለአማርኛ አዲስ አይደለም፡፡ አፄ ይሥሐቅ (1406-1421) የተዘፈነለት ምክንያት አንዱ ዘምቶ ብዙዎችን "ገበር" ስላደረጋቸው ነበር[10]፤

ስንቱን እቈጽር፡፡
የሐባባ ገበር፡፡
የጣይቶ ገበር፡፡
የላቦላ ገበር፡፡
ስንቱን እቈጽር፡፡
የጉዴላ ገበር፡፡
ሲፈክር ነበር፡፡
ስንኳን ለአምሐራ ዠር (ወታደር)፡፡
ሰማይ ቢከነበል፡፡
እናቆም (እናቆማለን) ሲሉ ነበር በጸር (በጦር)፡፡
ሲፈክሩ ነበር፡፡
አጠፉዋቸ ለዝክር፡፡

## (7) የኦሮሞ ታሪክ ከምንጩ

አሮሞዎች ከዓሥራ ስድስተኛው ምእት ዓመት ጀምረው ወደ ማህል ኢትዮጵያ ከመምጣታቸው በፊት አገሪቱን ቀደም ብለው በያዙት ሕዝቦች፥ በተለየም በላያቸው በተቋቋመው በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ስለተፈጸመው ግጭት በይበልጥ ለማወቅ የሚፈልግ ከአፄ ሠርፀ ድንግል ጀምሮ ከግራኝ በኋላ የተነሡ ነገሥታትን ታሪክ እና ዜና መዋዕላቸውን[11]፥ በተጨማሪም የአቶ ዐፅሜን መጽሐፍ[12] (ስድባቸውን እየናቀ) ማንበብ ይኖርበታል፡፡ አሮሞዎች ከየት ተነሥተው በየት በኩል ወደማህል ኢትዮጵያ እንደገቡ በአማርኛ ከተጻፉት ውስጥ ሊጠና የሚገባው ሆኖ ያገኘሁት ክቡር አቶ ይልማ ዴሬሳ የጻፉትን ነው[13]፡፡

10. Guidi, "Le canzoni geez-amariña", p. 59.
11. ብዙውን ለቅሜ *ባሕረ ሐሳብ* ውስጥ አስፍሬዋለሁ፡፡
12. Bairu Tafla, *Aṣma Giyorgis and His Work*. ዶ/ር ባይሩ የአቶ ዐፅሜን መጽሐፍ ለኅትመት ሲያዘጋጅ ሽልማት የሚያስጥ ሥራ ሠርቷል፡ ግን የመጽሐፉን ርእስ ባይለውጠው ደግነት ይሆንለት ነበር፡፡
13. ይልማ ዴሬሳ፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፡ ገጽ 212 ላይ የሚጀምረውን ምዕራፍ 40ን ተመልከት፡፡ ክቡር አቶ ይልማ በዚህ መጽሐፋቸው ውስጥ በአሮሞዎች ላይ ጠብ



እነዚህን ምንጮች ሳይመረምር ምዕራባውያንና በሚሲዮኖቻቸው ያደጉና ሌሎችም ለኦርቶዶክስ ክርስትና ጥላቻ የሚሰማቸውና እንደ ጠላት የሚያዩዋት የጻፏቸውን "የኦሮሞ ታሪክ" የሚያነብ እነዚህ ዘመናዊ ጸሐፊዎች የኢትዮጵያን ሕዝብና አገሪቱን የቱን ያህል እንደበደሉ ልብ አይለው ይሆናል፡፡ እነዚህ ጸሐፊዎች "የኦሮሞ ሽማግሌዎች ጠይቀን ያገኘነው ነው" የሚሉትን እውነት ይሁን ሐሰት ማመሳከረ እንደማንችል ያውቃሉ፡፡ ለዚህ ትውልድ የጊዜው ትልቁ እንቅፋት ታሪክ ነገሥቱና ዜና መዋዕሉ በግዕዝ መሆናቸውና ቢተረጐሙም ያሁኑ ትውልድ በሰፊው በማያውቃቸው የምዕራባውያን ቋንቋዎች መተርጐማቸው ነው፡፡ የተተረጐሙትም ቢሆኑ የምርምር መጻሕፍት ስለሆኑ የሚገኙት በታላላቅ ቤተ መጻሕፍት እንጂ በሕዝብ የመጻሕፍት መደብር አይሸጡም፡፡

የኢትዮጵያን ታሪክ ከምንጩ የሚያነብ ከሁሉ አስቀድሞ በክርስቲያኑ መንግሥት ባለሥልጣኖችና በሚገዙት ሕዝብ መካከል ሁል ጊዜ ግጭት እንደነበረ ያያል፡፡ ከዚያም የኦሮሞዎች ወደ ማህል ኢትዮጵያ አመጣጥ ለምን "የመንግሥቱ ወገን የሆኑ ጸሐፊዎችን የሚጋብዝ ሆኖ" ተገኝቷል እንዳልኩ ይረዳል፡፡ ከዚህ በታች ከዋናዎቹ ዘመን (ከዓሥራ ስድስተኛው እስከ ዓሥራ ስምንተኛው ምእት ዓመት) የታሪክ ምንጮች ለዚህ አጭር ጥናት ለምሳሌነት የሚበቁትን ያህል በጥቂቱ እጠቅስላቸዋለሁ፡፡

### (ሀ) መንግሥትና ሕዝብ

የሕዝብና የመንግሥት ግጭት መሠረታዊ ምክንያት፥ ከቤተ መንግሥት ጀምሮ እስከ ቀበሌ ገዢው ድረስ ያሉ ባለሥልጣኖች ወታደሮቻቸውን፥ ሎሌዎቻቸውን፥ ባሮቻቸውን ጨምሮ ብዙ ስለሆኑ፥ በተለይ ድርቅ ሲገባ፥ ለነሱና ላግበሰበሱት ሠራዊታቸው ቀለብ፥ ለፈረሶቻቸው መኖ ማቅረብ ሕዝቡን ስለሚከብደው አልፎ አልፎ አልገብርም ይል ስለነበረ ነው፡፡ በዚያ ላይ ከመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋራ በሃይማኖት የማይመሳሰሉ ነገዶች

አጫሪ ሱማሌዎች ናቸው እንጂ አሮሞዎችስ ሰላማዊ ሕዝቦች ናቸው የሚሉትን አስተያየት ሰላማዊነታቸውን ከኤኮኖሚ ሥርዓታቸው ጋራ እያስተያዩ የሚገባውን ያህል አላብራሩትም፡፡ አቶ ብርሃኑ ለሜሶና አቶ ታቦር ዋሚ *የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ* በሚል ርእስ ያሳተሙትን መጽሐፍ ሳነበው የተረዳሁት እነሱም እንደገለጹት የመጽሐፉ "ዋና ዓላማም የኦሮሞ ሕዝብ መፍለቂያና ጥንተ መኖሪያ በዚህች የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ መሆኑን የሚያረጋግጡ የታሪክ ማስረጃዎች ማቅረብ ነው" (ገ. 41)፡፡ መጽሐፉ ከመታተሙ በፊት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ክፍል መምህራን ካዩት፡ ቢቀሩ የደራሲዎቹን የተቀደሰ ዓላማ የማያደናቅፉትን አነጋገሮች እንዲያስቀሩና *ዜናሁ ለጋላንም* ከግዕዙ የሚተረጉምላቸው ሰው እንዲፈልጉ ወይም ክቡር ብላታ መርስዔ ኀዘን የተረጐሙትን (EMML 3749ን) እንዲያነቡ ለምን ሐሳብ እንዳላቀረቡላቸው ግልጽ አይደለም፡፡

ሰብላቸው ቢሠምርላቸውም አቅም ካገኙ (ወይም ያገኙ ሲመስላቸው) አንገብርም ይሉና መተላለቅ ይመጣል::

ለምሳሌ ከፈላሾች ጋራ ከሆኑት ግጭቶች ውስጥ አንዱን ዘገባ ከአፄ ሠርፀ ድንግል ታሪክ እንቅዳ[14]፤

*ወበውእቱ ወርኃ ክረምት ተንሥአ ደዌ በከተማ ወሞቱ ብዙኃን ሰብእ በውእቱ ደዌ:: ወእምቅድመ ዝንቱ ኮነ ምክረ ሐዬጌ ከረሞ ከመ ይሖር ለፀቢአ ጋላ እንዘ እምአንጎት እስከ ግድም ወኢፋት ወፈጠጋር ወደዋሮ::*

*ወዘንተ ምክረ ዐቀመ ወአጽንዓ ምስለ ኵሎሙ ሥዩማን ዘለፌ ወለፌ ጊዜ አስተፋነዎሙ ለለ ብሔሮሙ፤ ወባሕቱ ይመስለነ ዘይቤ እግዚአብሔር በውእቱ ጊዜ ኢኮነ ምክርየ ከመ ምክርክሙ ወኢኮነ ሕሊናየ ከመ ሕሊናክሙ::*

*ዘንተሰ ዘንብል እስመ በፈቃደ ዚአሁ ዘትሜግብ ኵነታተ ዓለም ኮነ ሙራደ ሐዬጌ ድኅረ ኃለፈ ክረምት መንገለ ፈላሻ፣ ወተርፈ ፀቢአ ጋላ:: ወምክንያተ ተኃድጎቱሰ ለውእቱ ምክር በእንተ ፀብአ ጋላ ናየድዕ በዝየ::*

*መጽአ መልእክት ዘይብል አትረፈ ረዳኢ ፈንዎተ ጸባሕት ዘይቤ ለሐዬጌ እንዘ ሀለዉ በጉባኤ እፎኑ ግብርየ ብዙኃ እክለ ወመዓረ አልህምተሂ ወአባግዓ ከማሁ አልቦ እምዝ ኵሉ ኢወሀበ ምንተኒ::*

*ወዘንተ ሰሚዖ ነደ ልቡ ከመ እሳት:: ወሶቤሃ ወጠነ ምክረ ከመ ይፅብአሙ ለፈላሻ ወይኅድግ ፀቢአ ጋላ:: ወለአከ ኀበ ኵሎሙ ጨዋ ውኁበ ሠየምተ ትግሬ ከመ ይብጽሑ በዕድሜ ዘዓደሞሙ:: ወምስለ ዝኒ ኮነ ይብል፥ ይኄይሰኒ እትበአስ ምስለ ዕድወ ደሙ ለእግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ እምእሖር ለፀቢአ ጋላ:: ዘንተ ምክረ አጽንዓ በወርኃ ክረምት...::*

*ወበይእቲ ዕለት ወረዱ ሽዋዳ ብዙኃን ሰብአ እግር ወመስተጽዕናነ አፍራስ ወማኅረኩ ብዙኃ አልህምተ እስላም ወክርስቲያን ዘተመይጡ እምክርስትና ኀበ አይሁድና፣ እስመ ነበሩ ልኢኮሞ ኀበ ሐዬጌ እንዘ*

14. Conti Rossini, *Historia Regis Sarṣa Dengel (Malak Sagad)*, pp 84-6. የመንግሥቱ ባለሥልጣኖች ከልዩ ልዩ የአገው ጎሳዎችና ከሌሎችም ጋራ ይጣሉ ነበር፤ ፈላሻዎቹን የሚመለከተውን ጥቅስ በተለይ የመረጥሁት "ፈላሾች ፈላሻ የተባሉት ርስታቸውን ተነቅለው ፈላሲዎች እንዲሆኑ ስለተፈረደባቸው ነው" የሚለው ትክክል አለመሆኑንና እንዲያውም የሚያኅን ርስት እንደነበራቸው በዚያው ለማሳየት ነው:: ሱስንዮስ "የወንድጌ እና የለግ ሰዎች ግብር ከማግባት እንደለገሙ በሰማ ጊዜ ተቆጥቶ "ሠራዊቱ እንዲዘርፋቸው" እንዳዘዘ ሠራዊቱም "ብዙ ከብቶች" እንደማረኩ የሚያሳየውን ጥቅስ ገጽ 131 135 ላይ ተመልከት:: ገጽ 31 ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል፡ "በከተማ ረኀብ በገባ ጊዜ ፋሲሉ ሐዬጌ ዘንድ መጥቶ እንዲህ ሲል ምክር አቀረበ፡ 'እነሆ ከተማው ተራብ ዘረፋ ልወስዳቸው መውጣቱ ነውና የከተማው ሰው ይከተለኝ' ሐዬም እሺ አለ (ተስማሙ)::"



*ይብሉ ናሁ መጻእነ ኀበ እግዚእነ ምስለ አልህምቲነ ወአንስቲያነ ወደቂቅነ:: ሀላዌሆሙሰ እምቅድመዝ ኮነ ኀበ ምድረ ምልክናሁ ለረዳኢ::*

*ወበፈቃደ እግዚአብሔር ተሰነአወ ምጽአተ እሉ ምስለ ሙራደ እሉ ኃያላን ከመ ትትዓወቅ ኂሩተ እግዚእነ በአግብአተ ንዋዮሙ ለእሉ እምድኅረ ተማኅረኩ፤ ዘመደ እክልኒ ብዙኀ ተዘርፈ በይእቲ ዕለት:: ወባሕቱ ኢፈቀዱ ነሚአቶ ለዳኅሳ ወዘይመስሎ እንበለ ስርናይ ወጽሩይ እክል ዘከማሁ:: ለእሉሰ እለ ተማኅረኩ አግብአ ሎሙ በግዘት ኵሎ ንዋዮሙ ዘተነሥአ:: ወኢያመክነዮ እንዘ ይብል ሚሳዕሌየ እመ ነሥኡ ሠራዊትየ ክርስቶሳዊያን ንዋየ እስላም ወፈላሻ:: አለዛቲ ኂሩት ዘትመስል ኂሩተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘያሠርቅ ፀሐዮ ላዕለ ኄራን ወእኩያን ወያዘንም ዝናመ ላዕለ ጻድቃን ወኃጥኣን::*

*ወበሳኒታሁ በዕለተ ዓርብ ወዓልነ በሀየ፣ ወፈነዎ ለአዛዥ ሐሊቦ ቅድመ ገጹ ከመ ይጺሕ ፍኖቶ ወይምላእ ኵሉ ማዕምቀ:: እስመ አንሀሉ ፈላሻ በውእቱ መዋዕል ወአጥፍኡ ፍኖተ ከመ ኢይሖርዎ አብቅልት ወአፍራስ:: ወበይእቲ ዕለት አስተራትዓ አዛዥ ሐሊቦ መብእሰ ወጕጻጕጸ ወረሰዮ መጽያሕተ ርቱዓ::*

*ወበሳኒታሁ ዘውእቱ ዕለተ ቀዳም ተንሥአ እምህየ ወረሰየ ፍኖቶ መንገለ ለርዊ ወሰፈረ በጻሮጻ:: በይእቲ ዕለት አልቦ ዘተዓቅፈ ወአልቦ ዘድኅፀ በፍኖት እምሰብእ እስከ እንስሳ እስመ የማነ እግዚአብሔር ትሜግብ ፍኖተ ዝንቱ ንጉሥ:: ወበዕለተ ሰንበት ወዓልነ ኀበ ሰፈርነ በዕለተ ቀዳም::*

*ካሌፍሰ እኅወ ረዳኢ ወጠነ ያውዒ በእሳት አብያተ ምስለ ኵሉ ዘውስቴቱ:: ወእክለኒ ዘሀሎ በገራህት አውዓየ፣ እስመ ጻዕደወ በውእቱ ጊዜ ወበጽሐ ለማእረር:: ከላስስተኒ ኀበ ተከምረ አውዓየ እንበለ ምሒክ:: ዘንተሰ ዘይገብር እስመ ይመስሎ ዘይትመየጡ ሶበ ኃጥኡ ሲሳየ፣ ወኢያእመረ ከመ ፈትሐ ቦቱ እግዚአብሔር::*

*ንሕነሰ ሶበ ርኢናሃ ለሀገር እንዘ ኵለንታሃ ሥርጉት በሐመልማለ ዘርእ ወፍሬ ማእረር ተነደፍነ በፍቅራ ወፈቀድነ ነቢረ ውስቴታ በከመ ይቤሎ ጴጥሮስ ለእግዚእነ በደብረ ታቦር፣ ይኄይሰነ ንንበር ዝየ::*

*ኢንኀድግ ትንቢተ ቃሉ ለረዳኢ ዘተነበየ አመ መጽአ ኀቤሁ ሐርቦ:: ወውእቱ ከዊኖ ጅደን ፈነወ ሠራዊቶ ምሁራነ ፀብእ ኀበ ሽዋዳ ዘዘረፍዎ ሰብአ ሐዬጌ:: ለይእቲሰ ፈለግ ዘሀለወት በማእከል አልቦ ዘተሀበለ ዓዲዎታ::*

*ውእተ አሚረ ለአከ ቃለ ትዕይርት ኀበ ሐርቦ እንዘ ይብል፥ ኦኃያል አዝማች ሐርቦ ነያ ቅድመ ገጽከ ምድረ ርስት እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ:: አፍጥን መጺአ ወኢትትሀከይ ከመ ትትዋረሳ ውትትካፈል አዕጻዳቲሃ::*

*ሐርቦሰ አርመመ ወኢያውሥአ ምንተኒ አላ አግብአ ለዘ ይኬንን ጽድቀ:: ሶበኒ ተቃተሉ ሠራዊቱ ጸንዕዎሙ ፈላሻ በውእቱ ዕለት፣*

*ወአንትዕዎሙ ለሠራዊተ ሐርብ ወዴገንዎሙ እስከ ማእከለ ዓቀብ:: ወባሕቱ ኢተሐገሉ እምኔሆሙ እንበለ ፩እምዐበይተ ሕዝብ:: ዝንቱ ኵሉ ከዊኖ ተመይጠ ሐርብ ብሔሮ በዳኅን መበሰላም::*

*ወበብዙኅ ዓመታት ፍዳ ይእቲ ትዕይርቱ መጽአ ንጉሥ ኀያል መለክ ሰገድ ኀበ ሰሜን:: ዝንቱሰ ምጽአቱ ይመስል ከመ ዘይቤሉ ለረዳኢ ለእከ ኀበ ሐርብ ከመ ይምጻእ ኀቤከ:: ወሀየንቴሁ ናሁ መጻእኩ ከመ እትካፈል አዕጻዳቲከ፣ ዘኢኃሠሥከኒ ረከብከኒ፣ ወዘኢጸዋዕከኒ ተሰጠውኩከ፣ ከመ ዘይብል ዘንተ ይመስል ምጽአተ እግዚእነ ኀበ ፈላሻ:: እስመ ተሀውከት ኵላ ሀገር እምግርማሁ በከመ ተብህለ አድለቅለቃ ለምድር ወሆካ::*

*ወበዕለተ ሰኑይ ተንሢአነ እምጻሮጸ ሰፈርነ በሠሉስ ኀበ ቅሩበ አምባሁ ለካሌፍ:: ወኀዳጣን ሕዝብ ወረዱ ቈላ እንበለ የአዝዝዎሙ:: ወሶቤሃ አርአዮሙ ብዙኃ ወሊታ ወኵናተ፣ ወባሕቱ ኢመጽአ ኀቤሆሙ ውእቶሙኒ ኢሖሩ ኀቤሆሙ:: ወተፋርሁ በበይናቲሆሙ:: ከተማሆሙኒ ገብሩ በአንጻሪሁ ዘሪፎሙ እክለ:: በይእቲ ሌሊት አልቦ ዘተሀበለ ቀሪበ ኀቤሆሙ ለአሕስሞ እምሰብአ ፈላሻ፣ እስመ ሞገሰ ግርማሁ ለዝንቱ ንጉሥ ትተልዎሙ፣ ወመልአኩ ይትዐየን ዓውዶሙ:: ዝንቱ ኵሉ ኮነ አመ ፳ወ፱ለወርኃ ጥቅምት:: ሰፍራሰ ዘሐዜጌ ምድረ ደግዓ ውእቱ፣ ወብዙኅ ቍሩ::*

*ወበሳኒታሁ በዕለተ ረቡዕ ወረዱ ሐዜጌ እመልዕልት ኀበ መትሕት ከመ ይፅብእዎ ለካሌፍ:: ወአትረፍዎሙ በስፍራ ለዶባ ሥልጣን (ወ)ሳዊሮስ ምስለ ብዙኅ አፍራስ ወነፍጥ ወምስለ ብዙኃን ሰብአ ወሊታ:: ሐዜጌሰ ወሪዶሙ ገብሩ ከተማ ኀበ ሰፈሩ ሰብአ ትማልም:: ዝንቱሰ ኮነ አመ፴ሁ ለወርኃ ጥቅምት::*

*ወፍኖተ ይእቲ ዕለት ኮነ በ፲ጸታ:: ለእለሰ የሐውሩ በግልሳይ ፍኖት ተንሥኡ ኅዕሌሆሙ ፈላሻ፣ እስመ አእመሩ ከመ ኢሀሎ ሀየ ዝንቱ ንጉሥ መዋኢ ወሖረ እንተ ካልእ ፍኖት:: ወሶቤሃ ተኀየለ ኅዕሌሆሙ ፊቅጦር ወልደ አዛዥ ፋኑኤል:: ወቀተለ ብዙኃ እምኔሆሙ ወአወፈየ ለሐዜጌ መጠነ ፳ሸብሸቦ:: ዝውእቱ ቀዳማይ መዊአቱ ለእግዚእነ ወጥንተ ተመውኦቶሙ ለፈላሻ::*

*ወቤተ ይእተ ሌሊተ ለጸቢሐ ሐሙስ እንበለ የሀብ ንዋመ ለአዕይንቲሁ ወኢድቃሰ ለቀራንብቲሁ እንዘ ይኄሊ ወይመክር ዘከመ እፎ ይፀብእ ለካሌፍ ወዘከመ እፎ ያወርዶ እመልዕልተ ደብር ዘተጸወነ ቦቱ:: ወበይእቲ ዕለተ ሐሙስ አንግሀ ገይሰ፣ ወሖረ ከመ ይዕብኦ ለካሌፍ::*

*ወእምዝ ፈነዎሙ ለመስተቃትላን በ፫ፍናዊት:: ወእንተ ታሕታይ ፍኖት ሖረ አዛዥ ሐሊቦ ምስለ ባሕር አሥባ:: ወኮኑ ቅድመ ገጹ ደጓረጎት ጕዝም ኒጋሽ ምስለ ሠራዊት:: ወበለፈ እሉ ኮኑ ቍርባን ኃያላን ዝንቱ ንጉሥ እለ ኢይመይጡ ገጾሙ እምደርብዮ ኵናት ወእምውግረ እብን ወነፍጥ ወአንፃ:: ለዕሉ ኵሎሙ ፈነዎሙ ምስለ ብዙኅ ነፍጥ በበ ነገዶሙ ወበበ ሕዘቢሆሙ:: ውእቱሰ ቆመ አንጻረ*



*ገጹ ለካሌፍ ኀበ ተዓየነ ምስለ ሠራዊቱ:: ወዓቅመ ርኅቀቱሰ ለሀላዌሆሙ የአክል መጠነ ፲፪ምዕራፍ አው ይበዝኅ:: ወምስለ ዝኒ ጸድፍ ዓቢይ ማእከሌሆሙ ዘኢይትከሃል ይዕድውዎ::*

*ወኮነ ዐቢይ ፀብእ በይእቲ ዕለት ማእከለ ሠራዊተ ዝንቱ ንጉሥ ወማእከለ ፈላሻ:: ወተፃብኦቶሙሰ ለሰብአ ካሌፍ ኮነ በአእባን እንዘ ያመረግሑ ኅዕሌሆሙ ይክልእዎሙ ዓሪገ እመትሕት ኀበ መልዕልት:: በዘ ከመዝ ግብር ጐንደየ ሰዓተ ነዋኃ፣ ወጊዜ ፲ሰዓት አዘዘ ዝንቱ ንጉሥ ይውግሩ መዳፍዓ:: ወበውግረተ ፩መድፍዕ አውደቅዎ ለጸዋሬ ዓላማ ወለአሐቲ ብእሲት ዘነበረት ተኃቢአ ታሕተ ዕፅ::*

*ውእተ ጊዜ ተሀውከ ካሌፍ ወኵሉ ሠራዊቱ፣ ወተፈትሐ ኵሉ ሠራዊተ ፀብኡ:: እስመ መሰሎሙ ዘወድቀ ኅዕሌሆሙ መብረቅ እምሰማይ:: ወዶብዓ ሥልጣንኒ ወረደ ኀቤሆሙ እመንገለ መልዕልት፣ እስመ ነበረ ተሪፎ በላዕላይ ስፍራ ለዓቂበ በር:: ወተራድኡ በበይናቲሆሙ ዘየማን ወዘጸጋም ዘመልዕልት ወዘመትሕት::*

*ካሌፍሰ ኃጥአ ልቡናሁ፣ እስመ አምሠጠ ልቡ እምብዝኃ ፍርሀት:: ወሶበ ተመንደበ እምኵለሄ ዓርገ ኀበ ዐቢይ ጸድፍ ምስለ ኀዳጣን ወዓልያኒሁ:: ኀበ ዝንቱሰ ጸድፍ አልቦ ዘዓርገ እምቅድመዝ አላ ዳእሙ አዕረገቶ ፍርሀቱ ለዝንቱ ተሐባሊ::*

*ወሠራዊተ ፀብኡሰ እለ ተፈልጡ እምኔሁ እምግርማ መድፍዕ ወእምፀብአ ኃያላኒሁ ለዝንቱ ንጉሥ እለ ይመስሉ ኃያላነ ዳዊት ዘአስተማሰለ መጽሐፍ ሩጸቶሙ በሩጸተ ንስር ወጽንዖሙ በጽንዓ አንበሳ:: ውእተ ጊዜ መንፈቆሙ ወድቁ በኵናት፣ ወመብዝኅቶሙ ተወርዉ ውስተ ጸድፍ (እንዘ) ይጐይዩ:: ወእምእንስሳሂ እለ ከመ አልህምት ወአባዕር ወአብቅልት ወአእዱግ ወኢኃደጉ ሕያወ አላ ዳእሙ አሕጐሉ በከመ ተብህለ ወቀተለ በኵርሙ ለግብጽ እምሰብእ እስከ እንስሳ:: እስመ አውገዘ አባ ንዋይ ከመ ኢይምሐኩ እደ ወአንስተ ኤእሩገ ወሕፃናተ ወኢያትርፉ ኵሎ ዘየሐውር በእግር::*

*ዕፁብ ዜና ዘኮነ በይእቲ ዕለት ለአሐቲ ብእሲት ዘተማኅረከት እንዘ ያመጽኣ ፩ብእሲ አሲሮ እዳ ምስለ እዱ:: ወሶበ ርእየት በጥቃሐ ዓቢየ ጸድፈ እንዘ ተሐውርአ አዶናይ ርድአኒ ብሂላ ተወርወት ውስተ ጸድፍ ወተማልአቶ ምስሌሃ እንበለ ፈቃዱ ለውእቱ ብእሲ ዘአሰረ እዳ ምስለ እዱ::*

❖

በዚያ የክረምት ወራት በሰፈሩ በሽታ ተነሥቶ በበሽታው ብዙ ሰዎች ሞቱ:: ከዚህ ቀደም ብሎ የአፄ ውሳኔ ክረምቱን አሳልፎ ጋላን ከአንጎት አንሥቶ ግድም፥ ይፋት፥ ፈጠጋር፥ ደዋሮ ድረስ ለመውጋት ለመሄድ ነበረ::

ይህንን ውሳኔ ከዚህም ከዚያም ሹሞች ጋራ ወደየሀገራቸው ሲሸኛቸው አጽድቆና አጽንቶ ነበረ:: ግን እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ

"ምክሬ ከምክራችሁ ጋራ አይደለም፥ ሐሳቤም ከሐሳባችሁ ጋራ አይደለም"[15] ያለ ይመስለናል።

ይህንን ያልነው፥ የዓለምን ሁኔታ በምታስተዳድር ፈቃዱ ምክንያት ከክረምት በኋላ የአፄጌ ዘመቻ ወደፈላሻ ስለ ሆነ ነው፤ ጋላን መውጋት ቀረ። ጋላን የመውጋት ውሳኔ የቀረበትን ምክንያት እዚህ ላይ እንገልጻለን፤

"አፄጌ በጉባኤ (ከተማ) በነበሩ ጊዜ፥ ረዳኢ ግብሬን ብዙ እህልና ማር እልካለሁ፥ ከብትና በጎችም እንዲሁ ያለዎትን ግብር መላክ አስቀረ። ከዚህ ሁሉ ምንም የለም፤ አንዳችም ነገር አልሰጠም" የሚል መልእክት (ከጉባኤ ከተማ) መጣ።

(ንጉሡ) ይኽንን ሰምቶ ልቡ እንደ እሳት ተቃጠለ፤ በዚያን ጊዜ ጋላን መውጋት ትቶ ፈላሾችን ሊወጋ ምክር ጀመረ። ወታደሩ ሁሉና የትግሬ ሹማምንት ከቀጠራቸው ቦታ ድረስ እንዲመጡ ላከባቸው። ከዚሁ አያይዞ እንዲህ ይል ነበረ፤ "ጋላን ለመውጋት ከምሄድ ይልቅ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ደመኞች ጋራ ብጣላ ይሻለኛል።" ይኽንን ውሳኔ በክረምት ወራት አጸና...።

በዚያች ዕለት ብዙ እግረኞችና ፈረሰኞች ወደ ሸዋዳ ወርደው ብዙ የእስላሞችንና ከክርስትና ወደ ይሁዲነት የተመለሱ ክርስቲያኖችን ከብት ማረኩ። ምክንያቱም ወደ ሐፄጌ "እነሆ ከከብቶቻችን፥ ከሴቶቻችን፥ ከልጆቻችን ጋራ ሆነን ወደጌታችን መጥተናል" ብለው ልከው ነበረ። ከዚያ አስቀድሞ ግን ኑሯቸው በረዳኢ የግዛት ምድር ውስጥ ነበር።

እነዚህ የተማረኩት ከተማረኩ በኋላ ገንዘባቸውን በመመለስ የጌታችን (የንጉሡ) ቸርነት ትታወቅ ዘንድ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ፥ የነሱ መምጣት ከነዚህ ኃይለኞች ዘመቻ ጋራ ገጠመ። በዚያን ዕለት የእህል ዓይነት ብዙ ተዘርፎ ነበረ፤ ግን ከስንዴና እንደ(ስንዴ) ጥሩ ከሆነ እህል በቀር ዳጉሳና እሱን የመሰለውን አልወሰዱም፤ ለተማረኩባቸው የተወሰደባቸውን ገንዘባቸውን ሁሉ በግዝት መለሰላቸው። "ክርስቶሳዊያን ሠራዊቴ የእስላሞችንና የፈላሾችን ገንዘብ ቢወስዱ ምን ቸገረኝ" ብሎ አላመካኘም። አቤት ይቺ ደግነት፤ ፀሐይን በደጎችና በክፉዎች ላይ የሚያወጣ፥ ዝናምንም በጻድቃንና በኃጢአተኞች ላይ የሚያዘንም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ደግነት የምትመስል!

በማግስቱ ዓርብ ዕለት እዚያ ዋልን። መንገድ እንዲጠርግና ጉድጓዶቹን ሁሉ እንዲሞላ አዛዥ ሐሊቦን በፊቱ ላከው። ምክንያቱም ፈላሾች በዚያን ጊዜ መንገዱን በቅሎና ፈረስ እንዳይሄድበት አፈራርሰው አውድመውት ነበረ። አዛዥ ሐሊቦ በዚያች ቀን የተበላሸውንና ወጣ ገባውን አሣምሮ የቀና ጥርጊያ አደረገው።

15. ኢሳይያስ 55፡ 8።



በማግስቱ፥ ቅዳሜ ዕለት መሆኑ ነው፥ (ንጉሡ) ከዚያ ተነሥቶ ጉዞውን ወደ ለርዊ አደረገና ጳሮጳ ላይ ሰፈረ። በዚያች ዕለት ከሰው እስከ እንስሳ በመንገድ የተደናቀፈ ያዳለጠውም አልነበረም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቀኝ (እጅ) የዚህን ንጉሥ መንገድ ታካሂደው ነበረ። እሑድ ዕለት ቅዳሜ ዕለት በሰፈርንበት ዋልን።

የረዳኢ ወንድም ካሌፍ ደግሞ ቤቶቹን በውስጣቸው ካለው (ንብረት) ጋራ ሁሉ በእሳት ማቃጠል ጀመረ። በማሳ ላይ ያለውንም እህል (አዝመራውን) አቃጠለው፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ነጭ ሆኖ ለስብሰባ ደርሶ ነበረ[16]። ነዶውንም ከተከመረበት ያላንዳች ምሕረት አቃጠለው። ይኽን የሚያደርገው (ሠራዊቱ) የሚበላ ሲያጡ የሚመለሱ መስሎት ነው፤ እግዚአብሔር እንደፈረደበት አላወቀም።

እኛ ግን ሀገሪቷን ሁለንተዋ በዘር ልምላሜና በሰብል ፍሬ አጊጣ ስናያት በፍቅሯ ተነደፍን[17]። ጴጥሮስ በደብረ ታቦር ለጌታችን፥ "እዚህ ብንኖር ይሻለናል"[18] እንዳለው፥ በውስጧ መኖርም አማረን።

ረዳኢ ሐርቦ (ካሁን በፊት) የመጣበት ጊዜ የተናገረውን የትንቢት ቃል እዚህ ላይ (ሳናነሣው) አንተወው። እሱ ደጀን ሆኖ በጦርነት የሰለጠኑትን ሠራዊቱን የአፄጌ ሰዎች ወደዘረፉት ወደሸዋዳ ልኮ ነበረ። ያችን በማህል ያለችዋን ወንዝ ግን ሊሻገራት የደፈረ አልነበረም።

በዚያን ጊዜ (ከወንዝ ማዶ ሆኖ) እንዲህ ሲል የስድብ ቃል ወደ ሐርቦ ላከ፤ "ኃይለኛው አዝማች ሐርቦ ሆይ፥ ማርና ወተት የምታፈስ ምድረ ርስት[19] ከፊትህ እነሆትልህ፤ እንድትዋረሳትና አትክልቶቿን እንድትከፋፈል ፈጥነህ ና፥ አትዘግይ።"

ሐርቦ ግን ዝም አለ፤ አንዳችም ነገር አልመለሰም። ግን ለእውነት ፈራጁ ነግሯል። ሠራዊቱ ሲዋጉም በዚያች ዕለት ፈላሾች ጠነከሩባቸው፤ የሐርቦን ሠራዊት አባረሯቸው። እስከ ዓቀበቱ ማህል ድረስ አሳደዷቸው። ሆኖም ከታላላቆቹ ሰዎች ውስጥ ካንዱ በቀር ከማህላቸው ሰው አልተበላሸባቸውም። ይህ ሁሉ ሆኖ ሐርቦ ወደሀገሩ በደኅናና በሰላም ተመለሰ።

ከብዙ ዓመት በኋላ የዚች ስድብ ፍጻ ሆኖ (እነሆ) ኀይለኛው ንጉሥ መለክ ሰገድ (ሠርፀ ድንግል) ወደ ስሜን መጣ። ይኽ አመጣጡ ለረዳኢ "ወዳንተ እንዲመጣ ለሐርቦ ላክህበት፤ በሱ ፈንታ አትክልትህን ልካፈል እኔ መጣሁ። ያልፈለግኸኝን አገኘኸኝ፤ ያልጠራኸኝ መለስኩልህ"[20] የሚለው ይመስላል። የጌታችን ወደፈላሻ

16. ምንጭ ዮሐንስ 4፡ 35፡ "ዓይናችሁን አንሡ፤ አዝመራውም አሁን እንደ ነጣ እርሻውን ተመልከቱ።"
17. ምንጭ መኃልይ 2፡ 5 "በፍቅሩ ተነድፌያለሁ።"
18. ማቴዎስ 17፡ 4።
19. "ማርና ወተት የምታፈስ ምድረ ርስት" እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጣት አገር መጠሪያ ነው፤ ለምሳሌ ዘፀአት 13፡ 5ን ተመልከት።
20. ምንጭ መኃልይ 5፡ 6፡ "ፈለግሁት፣ አላገኘሁትም፤ ጠራሁት አልመለሰልኝም።"

መምጣት ይኸንን የሚል ይመስላል፤ ምክንያቱም በግርማው አገሪቷ በመላ ተሸበረች -- "ምድርን አድለቀለቅሃት፤ አሸበርካትም"[21] እንደተባለ።

ሰኞ ዕለት ከጻሮጸ ተነሥተን ማክሰኞ ዕለት በካሌፍ አምባ አጠገብ ሰፈርን። ጥቂት ሰዎች ሳያዟቸው ወደ ቈላ ወረዱ። በዚያን ጊዜ (ካሌፍ) ብዙ ጋሻና ጦር የያዙ ወታደሮች አሳያቸው። ግን ወደነሱ አልመጣም፤ እነሱም ወደሱ አልሄዱም፤ እርስ በእርሳቸው ተፈራርተዋል። እህል ዘርፈው (ብቻ) ሰፈራቸውን ፊት ለፊቱ አደረጉ። በዚያች ዕለት ከፈላሾቹ ወደእነሱ ቀርቦ ሊጐዳቸው የደፈረ አልነበረም። ምክንያቱም የዚህ ንጉሥ የግርማው ሞገስ ትክለክላቸው፥ መልአኩም በዙሪያቸው ሰፍሮ ነበረ[22]። ይህ ሁሉ የሆነው በጥቅምት 29 ቀን (1572 ዓ. ም.) ነው። የአዜጌ ሰፍራም ደጋ ምድር ነበረ፤ ብርዱ ጠንካራ ነበረ።

አዜጌ በማግሥቱ ረቡዕ ዕለት ካሌፍን ለመውጋት ከላይ ወደ ታች ወረዱ። በሰፈሩ ዶባ ሥልጣን እና ሳዊሮስን[23] ከብዙ ፈረሰኛና ጠመንጃ (ያዥ)፥ ከብዙ ጋሻ (ተሸካሚ) ጋራ አስቀሯቸው። አዜጌም ወርደው የትናንትናዎቹ ሰዎች ከሰፈሩበት ሰፈሩ። ይህ የሆነው በኅዳር (በጥቅምት?) 30 ነው።

የዚያች ዕለት ጉዞ በሶስት ክፍል ነበረ። በሶስተኛው መንገድ በሚሄዱት ላይ ፈላሾች ተነሡባቸው፤ ምክንያቱም ይህ አሸናፊ ንጉሥ እዚያ እንዳልነበረ፥ በሌላ መንገድ እንደሄደ፥ ዐውቀው ነበረ። በዚያች ጊዜ የአዛዥ ፋኑኤል ልጅ ፊቀጦር አየለባቸው። ከነሱም ብዙ (ሰው) ገደለባቸው። ለአዜጌ ሃያ የሚያክል ሽብሽቦ[24] አስረከበ። ይህ የጌታችን (በፈላሾች ላይ) የመጀመሪያ ድል ነው፤ የፈላሾችም የመሸነፍ መጀመሪያቸው ነው።

---

21. መዝሙር 59፡ 4።
22. ምንጭ መዝሙር 33፡ 7፡ "የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል።"
23. ዶባ ሥልጣን የአፋር (የጥልባል) ገዢ የሹመት ስም ነው። ግዕዙ የሹመቱን ስምና ሳዊሮስን በዋዌ (በመስተጻምር) ስላያያዛቸው ሁለት ሰዎች አስመሰላቸው እንጂ ሹሙ ሳዊሮስ ሳይሆን አይቀርም።
24. ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙበት ቃል "ችብችቦ" ነው። ተዋጊዎች የሰው ቍንቅላት "ግድያ ይጥላሉ"፤ ምናልባትም ይፎክሩበት ይሆናል። ከጥንት ጀምሮ ባህል ሆኖ ሁለቱም ተጋጪ ወገኖች ጠላት ሲገድሉ ቍንቅላት እየቈረጡ ያሳያሉ፡ ለምሳሌ ማቴዎስ 14፡ 8-10 ላይ ያለውን ስለመጥምቁ ዮሐንስ ራስ ተቈርጦ በሳህን መቅረብ የተጻፈውን ተመልከት። በኛ ዘንድ እስከ ቅርብ ጊዜ ቀጥሎ እንደነበረ የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ያሳያል። ጋረድ የሚባል ያጎታቸው ልጅ ጦር አዘጋጅቶ ሥልጣናቸውን እንደተቀናቀነ ይታወሳል። ሲያሸንፉት አንድ ሺ አምስት መቶ ያህል ወታደር ማርከውበት ነበር፤ "(አፄ ቴዎድሮስ) ይኸን ሁሉ ሰው ሰብስቦ ደባርቅ ከሚባል ገበያ ላይ ወስዶ እንገት እንገቱን ቈርጦ እንደ ካብ ካበው"፤ የጎጃም ታሪክ ፡ EMML 5403, f.108b.



በዚች የሐሙስ ዕለት አጥቢያ ሌሊት ለዓይኖቹ መኝታ፥ ለሽፋሽፍቶቹም እንቅልፍ ሳይሰጥ[25] ካሌፍን እንዴት እንደሚወጋውና ከተሸሸገበት ተራራ ጫፍ እንዴት እንደሚያወርደው ሲያስብና ሲመክር አደረ። በዚች የሐሙስ ዕለት በግሥጋሤ (ሲሄድ) አነጋና ካሌፍን ለመውጋት ሄደ።

ከዚህ በኋላ ተዋጊዎቹን በሶስት መንገድ ላካቸው። አዛዥ ሐሊቦ ከባሕር አሥባ ጋራ በታችኛዋ መንገድ ሄደ። በፊቱ ጐዣም ነጋሽ ደጎረጎት ከውራን ጋራ ሆነ። በነሱ ጐን ከጦር ውርወራ፥ ከድንጋይ፥ ከነፍጥ፥ ከወስፈንጥር ምት ፊታቸውን የማይመልሱ የዚህ ንጉሥ ኀይለኞች (እነ) ቍርባን ሆኑ። እነዚህን ሁሉ በየነገዳቸውና በየሕዝባቸው ብዙ ጠመንጃ ጨምሮ ላካቸው። እሱ ደግሞ ካሌፍ ከሠራዊቱ ጋራ በሰፈረበት ፊት ለፊት ቆመ። ካሉበት የርቀቱ መጠን ሰባት ምዕራፍ ወይም በለጥ ይላል። በዚህ ላይ ደግሞ፥ ሊሻገሩት የማይቻል ትልቅ ገደል በማህላቸው አለ።

በዚያች ዕለት በዚህ ንጉሥ ሠራዊትና በፈላሾች ማህል ትልቅ ጦርነት ተካሄደ። የካሌፍ ሰዎች ጦርነት በድንጋይ ነበረ። በላያቸው ላይ እየናዱባቸው ከታች ወደላይ መውጣትን ይከለክሏቸው ነበረ። በዚህ ሁኔታ ረጅም ጊዜ ቆየ፤ በስድስት ሰዓት ላይ ንጉሡ መድፎቹን እንዲተኩሱ አዘዘ። በአንድ መድፍ ተኰስ (ስንደቅ) ዓላማ ተሸካሚውን ጣለው -- ከዛፍ ስር ተደብቃ የነበረችውን ሴት ጨምሮ። በዚያን ጊዜ ካሌፍና ሠራዊቱ ሁሉ ተሸበሩ። የጦር ሠራዊቱ በሞላ ተፈታ፤ ምክንያቱም ከሰማይ መብረቅ የወደቀባቸው መሰላቸው። ዶብዓ ሥልጣንም[23] ከላይ በኩል ወደነሱ ወረደ፤ ምክንያቱም በር ለመጠበቅ እላይኛው ሰፈር ቀርቶ ነበረ። የቀኙም የግራውም፥ የላዩም የታቹም እርስ በእርሳቸው ተረዳዱ።

ካሌፍ ደግሞ ልቡናውን አጣ፤ ምክንያቱም ልቡ ከፍርሃት ብዛት አምልጦት ነበረ። በሁሉም አቅጣጫ ሲጨነቅ ጊዜ ከጥቂት ሎሌዎቹ ጋራ ሆኖ ከትልቅ ገደል (አፋፍ) ወጣ። እዚህ ገደል ላይ ካሁን በፊት ማንም አልወጣም። ይኸንን ኀፍረተ ቢስ ግን ፍርሃት አወጣው።

በመድፉ ግርማና መጽሐፍ ፍጥነታቸውን በንስር ፍጥነት፥ ጥንካሬያቸውን በአንበሳ ጥንካሬ ያስመሰላቸውን የዳዊትን ኃይለኞች[26] ከሚመስሉት የዚህ ንጉሥ ኃይለኞች ጦር ፍርሃት የተለዩት የጦር ሠራዊቱ ደግሞ በዚያን ጊዜ ግማሻቸው በጦር ወደቁ፤ አብዛኞቹ ሲሸሹ ገደል ገቡ። ከእንስሳም እንደነ ላም፥ በሬ፥ በቅሎ፥ አህያ ያሉትን በሕይወት አልተዋቸውም፤ "የግብጾችን በኵሮቻቸውን ከሰው እስከ እንስሳ ገደለ"[27] እንደተባለው አጠፏቸው እንጂ። ምክንያቱም

---

25. ምንጭ መዝሙር 131፡ 4፡ "ለዓይኖቼ መኝታ፡ ለሽፋሽፍቶቼም ዕንቅልፍ፡ ለጉንጮቼም ዕረፍትን አልሰጥም።"
26. ሳሙኤል ካልዕ 1፡ 23።
27. ዘፀአት 12፡ 29።

እንዳይምሩ፥ ወንድ፣ ሴት ሽማግሌ፣ ሕፃን፣ በእግሩ የሚሄደውን ሁሉ እንዳያስተርፉ አባ ንዋይ አውግዘው ነበረ።

በዚያች ዕለት የሚያስገርም ታሪክ ሆነ፤ አንዲት የተማረከች ሴት አንድ ሰው እጇን ከእጁ ጋራ አስሮ ሲያመጣት በመንገድ ሳለች አጠገቧ ትልቅ ገደል ስታይ፥ "አዶናይ እርዳኝ" ብላ ገደል ተወረወረች። እጇን ከእጁ ጋራ ያሰረውን ሰውም ያለፈቃዱ ይዛው ሄደች።

## (ለ) የኦሮሞዎች "ሰብአ ትካትነት"

በኦሮሞዎችና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ከመጀመሪያው ላይ የነበረው ግጭት ኦሮሞዎች እንደ ፈላሻዎቹ ግብር ስለከለከሉ አይደለም፤ ከዚህ ፈጽሞ የተለየ ነው። በኋላ የመጡ የዛሬ ታሪክ ጸሐፊዎች እንደሚተረጉሙትም ኦሮሞዎች ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ መንግሥት በኀይል ሊከለክላቸው ስለሞከረም አይደለም። እስከ ቅርብ ታሪኳ ድረስ ኢትዮጵያ ማንም ሰው፥ ጎሳ፥ ወይም ነገድ፥ ማንም ሳይከለክለው ገብቶ ከባዶ ቦታ ሰፍሮ አገሩ ሊያደርጋት የሚችል አገር ነበረች። በአፄ ሱስንዮስ ዘመን የስናር ንጉሥ ከነሠራዊቱ ቢመጣ ሱስንዮስ ጭልጋን ጠቅልሎ እንደሰጠው አንብበናል፤ እዚህም ገጽ 131-135 ላይ ተመልከት። በሰላማዊ መጤዎችና በመንግሥት መካከል ግጭት ለመፈጠሩ የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ የለንም። የኦሮሞዎች ጊዜ ግን ጠርነት ነበረ፤ ያውም ቢሆን አባ ባሕርይ "ጋላ ዘድኅር" ("የኋለኞቹ ጋሎች") ከሚሏቸው ከዳዌ ጋራ ነበረ። ለምን?

የግጭቱ መንሥኤ የዚያን ጊዜ የኦሮሞዎች የኑሮ ዘዴ ነው። ኦሮሞዎች ወደማህል አገር የገቡ ጊዜ አገሬው አርሶና አሳርሶ፥ ነግዶና አስነግዶ፥ ቀድሶና አስቀድሶ የሚኖር "ነባር" ወይም "ሰፋሪ" ሕዝብ ነበረ። ዘላኑም ቢሆን በዚያው በሚኖርበት (በሰፈረበት) አገር አካባቢ የግል ከብቶቹን እየነዳ "ይዘልን" ነበረ እንጂ፥ እንደ ሕዝብ፥ እንደ ነገድ፥ እንደ ጎሳ በአንድነት ካካባቢው እየወጣ አይመላለስም።

ኦሮሞዎች፥ በተለየም "ዳዌ" የሚባል ስም የወጣለት ነገድ፥ በ16ተኛው ምእት ዓመት ወደ ማህል ኢትዮጵያ ሲመጡ የኑሮ ዘዴያቸው ከነዚህ ኢትዮጵያውያን፥ ከነባሩም ሆነ ከዘላኑ፥ ኑሮ ፈጽሞ የተለየ ነበረ። የጎሳቸው አወቃቀር እንደሌሎች ኩሳዊ ነገዶች[28] ኅብረተ ሰባዊ፥ ወይም በዛሬው ቋንቋ አነጋገር፣ **በእኩልነት የተደራጀ ወታደራዊ ኮሚኒዝም ሆኖ ኢኮኖሚያቸው ዝለና** ነበረ። የሚዘልኑትም በባዶው ሀገር ላይ ሳይሆን በነባሩ ሕዝብ ኑሮ ላይ ነበረ። በሰብሉ ላይ ከብታቸውን ያሰማሩበታል፤ ከብቱን ይነጥቁታል፤ ንብረቱን ይዘርፉታል። ሰዉንም እየፈነገሉ አገልጋዮቻቸው ያደርጉታል። የጸሎት ቦታዎች (አብያተ ክርስቲያንና መስጊዶች) ለነሱ ምንም ትርጉም የሌላቸው የሚፈርሱ የጠላት ንብረቶች ነበሩ። ኑሯቸው በከብት ርቢ ቢሆንም የዱር አውሬ እያደኑና የዱር ፍሬ እየሰበሰቡ የሚኖሩ የሰብአ ትካትን (ማለት፥ የጥንት ሰዎችን) ኑሮ ይመስላል፤ ብቻ የአደኑና የፍሬ ስብሰባው ልዩነት የሰብአ ትካቱ በዱር፥ የኦሮሞዎቹ በመንደር ሆነ እንጂ።

አባ ባሕርይ ***ሰላመ ቅዱሳን*** ደርሰው ሲጨርሱ ዘመኗን "**ይቅርታ ያጣች**" (የፈረደባት) እንዳሏት እናስታውሳለን (ገጽ 51)። መዝሙር 73ን የደረሱት ለዚያች "**ይቅርታ ያጣች**" ላሏት ዘመን ነው። መዝሙሩ ስሜታቸውን ስለሚገልጽና የዘመኑን ታሪክ ስለሚያንጸባርቅ እንዳለ እዚህ ቦታ ቢጠቀስ ተስማሚ ነው (ከቅጠል 70ለ-እስከ 71ለ)፤

*ለምንት ገደፍከነ እግዚኦ ለዝሉፉ፤*
*ዘታስተጋብእ ዝርዋነ ወተኑሥሥ እለ ተገድፉ (ኪዳን)፤*
*ተዘከር ሕዝበከ ዘተግኅጸከ ተወክፉ፤*
*ወበመቅሰፍትከ ዘተቀስፉ፤*
*ወአልቦ አመ እምሁከት አዕረፉ።*
*ወበእንተዝ አሕዛብ ኅዕሌነ ይጸርፉ።*
*መጠነሰ አኀሠመ ፀራዊ ዲበ ቅዱሳኒከ፥*
*ኵሎ ተአምር ወኢትፌቅድ ከመ ይንግሩከ።*
*እስመ ይትዔየር ዲበ እለ ይሰምዩከ አምላከ፤*
*ፈድፋደሰ በቤተ መቅደስከ።*
*ናሁ ከመ ዕፀ ገዳም አውዓየ መዓፀወ ኆኅታ።*
*ወከመ ልገተ አቅማሕ ነሰተ አረፍታ።*
*አስተሐቀረ ክብራ ወአርኰሳ።*
*ወረሰያ ለቤተ ቅዳሴ ምርአየ እንስሳ።*
*እፎ አዕበይከ ኪያሃ አመ መዋዕለ ንእሳ፤*
*ይእዜሰ ለምንት ተኃሥሮ ለክብራ፥ ወተአትቶ ለሞገሳ።*
*እሞኒ ወሀከተከ በአበሳ፥*
*ቦኑ ሐቃላዊ ይኄይሳ።*
*አለልቡ ዘፊንሐሰ እንፊሳ (ዘኍልቍ)፥*

28. "ለጋዳ ሥርዓት መስፋፋትም ቢሆን ጋሎችን ተጠያቂዎች ማድረግ አይቻልም። እንደእውነቱ፥ ይህ ልዩ የሆነ የኅብረተ ሰብ አወቃቀር በጠቅላላው ከምሥራቅ ኩሳዊ የቋንቋ ቤተ ሰብ ሕዝብ ጋራ የተያያዘ ነው፤ እርግጥ የጋሎቹን፥ የሲዳማ-ሐዲያዎቹን ወይም የኮንሶዎቹን ሥርዓቶች፥ የቅርብ ጊዜ የጋራ ግኝት ያላቸው ሊሆኑ ስለሚችሉ፥ የተለየ አድርጎ ማየት ይኖራል" ("Auch für die Verbreitung des gada-Systems kann man die Galla nicht verantvortlich machen. Diese eigentümliche Sozialverfassung ist zwar ausschließchlich mit den Völkern der ostkuschitischen Sprachfamilie verbunden, doch sind die Systeme der Galla, Sidamo-Hadya oder Konso zu verschieden, als daß sie eine jüngere gemeinsame Herkunft haben könnten."), Eike Haberland, *Galla Süd-Äthiopiens*, p. 3.

*እስከ ማእዜኑ በመዓት ታረምማ ወትትዓገሣ::*
*መኑ እምይእዜ ለሕግከ የኃሥሣ፤*
*ወበምንትኑመ ለስምከ ንቄድሳ፤*
*እስመ መጻሕፍት ውዕየ ወተደምሰሳ (ዕዝራ)::*
*ተሠሃል ኅዕሌነ አምሳለ እም ኅዕለ ውሉደ ከርሣ::*
*መኑ እግዚእ ዘኢይቀስፍ ሶበ ተምዓ፤*
*ወአልቦ መምህር ዘኢይጌሥጽ ረድአ::*
*ወኢረከብነ ዘኢይምሕር እምድኅረ ቀጥዓ::*
*እስመ በትር ወመቅሰፍት ቅድመ ተሠርዓ፡*
*ለዘ ተሀከየ ቅኔሁ ወለዘ ትእዛዞ ረስዓ::*
*ወይምሕርዎ ለእመ ነስሐ ወገብአ::*
*ወአምሳለዝ በመጻሕፍት ተየድዓ፤*
*ከመ እምድኅረ ዓመታት ሰብዓ፤*
*ተሠሃልካ ለጽዮን ወመሐርከ ሰብአ (ኤርምያስ)፤*
*ወዝርወታተ ደቂቀ ሕዝባ ተጋብአ::*
*ኦክርስቶስ ርእሰ አሕይዎ፤*
*መሐር ሕዝበከ ወለፀሮሙ ሠርዎ፤*
*ወአስተጋብኦሙ እምተዘርዎ፤*
*እስመ ለአባሲ ይምሕርዎ፤ ወለሰአሊ ይሁብዎ::*
*ወኢትበለነ ከመ በዜና ነቢያት ትብል (ሕዝቅኤል)፤*
*እመ ቆሙ ቅድሜየ በስኢል፤*
*ጻድቃነ ዘመን ብሉይ ኖኅ ወኢዮብ ወዳንኤል፤*
*ዲበ ዝንቱ ሕዝብ ኢይሠሃል::*
*ወእመኒ መድሎተ ጌጋይነ ይኄይል፤*
*እምጽድቀ እሉ ዓበይተ ሕዝብ ክቡድ፤*
*ተዘከር ንጽሐ እምከ እምኮሉ ዘይፈደፍድ፤*
*ወሐሊ ቅንዋተ አእጋር ወእድ፤*
*ከመ ትምሐረነ ወትሠሃል ኪያነ፤ ኦወልደ አብ ዋሕድ::*

❖

ጌታ ሆይ፤ ለምን ለሁል ጊዜ ተውከን፤
የተበተኑ የምትሰበስብ፤ የወደቁ የምትፈልግ (ሆይ)[29] (*ኪዳን*)፤
ተግሣጽሕን የተቀበሉ ሕዝብህን አስታውስ፤
በቅጣትህም የተቀጡትን::
ከብጥብጥ ያረፉበት ጊዜ የለም::
በዚህም ምክንያት አሕዛብ ይሳደባሉ::
ጠላት በቅዱሶችህ ላይ የቱን ያህል ክፋት እንደፈጸመ፤

29. "ያስተጋብኦሙ ለዝርዋን" ("የተበተኑትን ይሰበስባቸው ዘንድ" -- በፈቃዱ ሞተ፤ ተቀበረ)፤ *መጽሐፈ ቅዳሴ በግዕዝና በአማርኛ*፤ አዲስ አበባ ፲፱፺፩ ዓመተ ምሕረት፤ ገ. 95፡ 40::



ሁሉን ታውቃለህ፡ እንዲነግሩህ አትፈልግም::
አምላክ በሚሉህ ላይ ያላግጣልና፡
በይበልጥም በቤተ መቅደስህ ላይ::
እነሆ የበሯን መዝጊያ እንደዱር እንጨት አቃጠለው::
ግድግዳዋንም እንደ ሰብል ጎጆ[30] አፈረሰው::
ክብሯን አዋረደ፤ አረከሳትም::
የቅዳሴውን ቤት የከብት መዋያ (በረት) አደረገው::
በልጅነት ዘመኗ እንዴት ከፍ ከፍ አደረግሃት፤
አሁንስ ለምን ክብሯን ታዋርደዋለህ፡ ሞገሷንም
    ትገፈዋለህ::
በጥፋት ብታበሳጭህስ፤
በውነት ዘላን ይሻላታልን::[31]
የፊንሐስን ልብ ያሳረፍክ ሆይ (*ዘኁልቍ*)[32]፤
እስከመቼ በቁጣህ ዝም ትላታለህ፤ ትታገሥባታለህም::
ካሁን በኋላ ሕግህን ማን ይፈልጋታል፤
ስምህንስ በምን እንቀድሰው፤
ምክንያቱም መጻሕፍቱ ተቃጠሉ፤ ተደመሰሱም (*ዕዝራ*)[33]::
ይቅርታ አድርግልን (እንጂ)፤ እንደ እናት በሆዷ ልጆች
    ላይ::
ሲቆጣ የማይቀጣ ጌታ ማነው፤
ደቀ መዝሙር የማይገሥጽ መምህርም የለም::
ከቁጣ በኋላ የማይምርም አላገኘንም::
ዱላና ቅጣት ከጥንት ተሠርተዋል፤
በግዴታው ላይ ለሚለግምና ትእዛዘን ቸል ለሚል::
ሲጸጸትና ሲመለስ ደግሞ ይምሩታል::
የዚህ ምሳሌ በመጻሕፍት ታውቋል፤
ከሰባ ዓመት በኋላ፤
ጽዮንን ይቅር እንዳልካትና ሰዎቿን እንደማርክ (*ኤርምያስ*)[34]፤
የሕዝቧ ልጆች ብትንታኔ እንደ ተሰበሰበ::
የሕይወት መስጠት ራስ ክርስቶስ ሆይ፤

30. ሚክያስ 3፡ 12 ("ወትከውን ኢየሩሳሌም ከመ ልገተ ዓቃቤ ቀምሕ" ያለውን ሲጠቅስ ነው::)
31. "ዝኩ ... ሐቃላዊ" ("ይህ ዘላን ...")፤ የሠርፀ ድንግል/መለክ ሰገድ ታሪክ፤ Conti Rossini, *Historia Regis Sarṣa Dengel (Malak Sagad)* p. 53.
32. ዘኁልቍ 25፡ 10-13::
33. ሱቱኤል 2፡ 23::
34. ተረፈ ኤርምያስ:: መጽሐፉ በሞላ የሚተርከው የእስራኤልን ወደ ባቢሎን በግዞት (በዔዋዌ) መወሰድንና በእግዚአብሔር እርዳታ ወደ ኢየሩሳሌም መመለስን ነው:: መጽሐፉን ፕሮቴስታንቶች አይቀበሉትም፡ "ተረፈ ኤርምያስ" ማለት ከመጽሐፈ ኤርምያስ የተረፈ (ተቆርጦ የቀረ) ማለት ነው::

ሕዝብህን ማር፥ ጠላታቸውንም ንቀለው፤
ከመበተንም ሰብስባቸው፤
አጥፊን ይምሩታልና፥ ለለማኝም ይሰጡታል።
በዜና ነቢያት እንዳልከው አትበለን (*ሕዝቅኤል*)[35]፥
"በልመና ከፊቴ ቢቆሙም፥
የብሉይ ዘመን ጻድቃን -- ኖኅ፥ ኢዮብ፥ ዳንኤል --
ይኸንን ሕዝብ ይቅር አልለውም።"
የኃጢአታችን ሚዛን ቢከብድና፥
ከነዚህ የከባድ ሕዝብ ታላላቆች የጽድቅ (*ሥራ ሁሉ*)
    ቢበልጥ እንኳን፥
ከሁሉ የሚበልጠውን የናትህን ንጽሕና አስታውስ፤
የእግርና የእጅ(ህ)ን የምስማር ቍስሎች አስብ፤
እንድትምረንና ይቅር እንድትለን፥ የአብ አንድ ልጅ ሆይ።

አድያም ሰገድ ኢያሱ በ1676 ዓ.ም. ውጫሌን ለመውጋት ወደ ወሎ ሲዘምት የጸለየው እንዲህ ብሎ ነበር[36]፤

*ኦእግዝእትየ ወልታየ በውስተ ፀብዕ ወምስዋርየ እምሀከከ ሰብእ...ይእዜኒ አንቲ ሠርሒ ፍኖትየ ወጸግውኒ ኃይለ መዊእ ላዕለ ፀርየ ወጸላእትየ እለ ይቀትሉ ምዕመናነ ወካህናተ ወያውዕዩ አብያተ ክርስቲያናት ዘውስቴቶን ይጠባሕ ሥጋሁ ቅዱስ ወውስቴቶን ይትቀዳሕ ደሙ ክቡር ለወልድኪ አምላከ ሰማይ ወምድር ... ኢትረስዒኒ ስላቀ ለጸላእትየ እለ ያመልኩ ስብሐ ...*

❖

እመቤቴ ሆይ፥ በጦርነት ጊዜ ጋሻዬ፥ ከሰው ንዝንዝ መደበቂያየ ነሽ፤ ... አሁንም መንገዴን አንቺ አሣምሪው፤ ምእመናንና ካህናትን በሚገድሉ፥ የሰማይና የምድር አምላክ የሆነው የልጅሽ ቅዱስ ሥጋ በውስጣቸው የሚሠዋባቸውን፥ ክቡር ደሙ የሚቀዳባቸውን ቤተ ክርስቲያኖችን በሚያቃጥሉ ጠሬና ጠላቶቼ ላይ የድል ኀይል ስጭኝ።...ስብ ለሚያመልኩ ጠላቶቼ መሳለቂያ አታድርጊኝ።

ግራኝ ከማመፁና ኦሮሞዎች ወደ ማህል ኢትዮጵያ በዳመጣ ከመስፋፋታቸው በፊት ከፖርቱጋል መልእክተኞች መጥተው አገሪቷንና መኳንንቱን (ንጉሡንም ጳጳሱንም) ጐብኝተው እንደሄዱ እናስታውሳለን። ሀገራቸው ሲመለሱ ለንጉሣቸውና ለሕዝባቸው ያቀረቡት ዘገባ እንደሚያመለክተው፥ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ከከፍተኛ ሥልጣኔ ደርሳ ነበረ። ለምሳሌ፥ መልእክተኞቹ ስለ አንዳንዶቹ የአብያተ ክርስቲያን

35. ሕዝቅኤል 14፡ 14።

36. I. Guidi, *Annales Iohannis I 'Iyāsu I et Bakāffā*, part II, p. 73.



ሕንፃዎች ሲጽፉ እንዲህ ያለ ሕንጻ ፖርቱጋል ውስጥም አላየን ብለዋል[37]። ግራኝ እንዲዋጉለት በወርቅ አባብሎ ያመጣቸው ቱርኮችና ዓረቦችም የመሰከሩት ይኸንኑ ነው[38]። ሱስንዮስ ያመጣቸው የካቶሊክ ጳጳስ (ሜንዴዝ) ተሰብስበው ለተቀበሏቸው የሀገሪቱ ባለሥልጣኖችና ሊቃውንት ያደረጉት ንግግር ለአካዴሚ ጉባኤ የተሰጠ ይመስል ነበረ[39]። ጳጳሱ ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣታቸው በፊት እነማን እንደሆንን ለማወቅ ጥረት አድርገው እንደነበረ ግልጽ ነው።

በየገዳማቱ የተቋቋሙት በአካዴሚ ደረጃ የሚታዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የነበሩ ሊቃውንት በዚያን ጊዜ የተረጐሟቸውንና የደረሷቸውን መጻሕፍት እስካሁን መርምረን አልጨረስናቸውም። የግራኝ ወታደሮችና የኦሮሞ ቄንደላዎች በማቃጠል ባይቀንሷቸው ኖሮማ ጥናታቸው ገና ብዙ ዘመን ይፈጅ ነበር። እንግዲህ የዚያን ጊዜው ግጭት ባንድ በኩል እንደዚህ በተራቀቀ ሕዝብና በሌላ በኩል በሰብአ ትካትነት ሕይወት በሚኖሩ ነገዶች መካከል ነበረ። ግጭቱ ሀገሪቷን ዶጋ አመድ ነው ያደረጋት። ዛሬ እንኳን መጻሕፍቱን አንዳንዶቹ ገዳማት መኖራቸውን እንኳን የምናውቀው ስማቸውን ከታሪክ መጻሕፍት ውስጥ ስናገኘው እንጂ ከዚያ ውጪ የት እንዳሉ አናውቅም። ኦሮሞዎች ወደ ማህል ኢትዮጵያ ገብተው የያዙት ሀገር ግራኝ ባዶ ያደረገውን ነው የሚሉትን የዛሬ የኦሮሞ ታሪክ ጸሐፊዎችን የአባ ባሕርይ ጥናት አይደግፈውም። ኦሮሞዎች ሀገር ሲወሩ ነባሩን ሕዝብ እያጠፉና ኦሮሞ እያደረጉ ነበረ።

## (8) የመንግሥት አቅምና ኦሮሞዎች

ዘበኛ የሌለው ወይም ራሱን ለመጠበቅ ያልተደራጀ ሰላማዊ ሕዝብ "ጋላ መጣ" ሲሉት የሚያመጡበትን አደጋ ስለሚያውቅ "ኡኡ" ይል ጀመረ። አውላላ ሜዳ ላይ ሆና የተራበ ነምር ያየች ሚዳቋ መሰሉ። አንዳች ኮሽታ

37. Lord Stanley of Alderley, *Narrative of the Portuguese Embassy to Abyssinia During the Years 1570-1527. By Father Francisco Alvarez*, New York 1881, pp. 75 and 122. "They also were surprised at our coming into the church with our shoes on, and still more at our spitting in it," p. 30. ("ደግሞ ጫማችንን እንዳደረግን ከቤተ ክርስቲያን በመግባታችን፥ ይልቁንም ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመትፋታችን፥ ተገረሙ")።

38. M. René Basset, *Histoire de la conquête de l'Abyssinie (XVIe siècle) par Chihab Eddin Ahmed Ben 'Abd el Qâder surnommé Arab-Faqih*, Paris Vol. I (1897), pp. 213-4.

39. Philip Caraman, *The Lost Empire The Story of the Jesuits in Ethiopia 1555-1634,* Notre Dame (Indiana), 1985, p. 142: "The speech was spattered with quotations from Aristotle, Tertullian, Eusebius and Jerome, and would have been an impressive display of erudition in any European university" ("ንግግሩ ከአርስጣጣሊስ፥ ከተርቱሊያኖስ፥ ከአውሳብዮስ፥ ከኢየሮም የተወሰዱ ጥቅሶች

ሲሰማ መበርገግ ሆነ። ታሪክ ጸሐፊው እንደመዘገበው፡ አንድ ጊዜ አንዲት ሴት አሻሮ ስትቈላ ማገዶ ልታገባ እዳሪ ወጥታ ሳለ ጎረቤቷ እሳት ልትጭር ወደቤቷ ብትገባ አሻሮዋ ሲያር አገኘችው። ባለቤቷን ለማስጠንቀቅ "አሻሮው አረረ፥ አሻሮው አረረ" ብላ ብትጣራ "ባላስተናበረ ጆሮ ጋላ ወረረ፥ ጋላ ወረረ" ያለች መስሏት አማራ ተሸበረ። ጓዙን እየነዳ ሸሸ ይባላል[40]።

ካህናቱ ለደረሰው መቅሠፍት ምክንያት ሲፈልጉ የአፄ ልብነ ድንግል ጥጋብ ያመጣው ቅጣት አድርገው ይናገራሉ። ለዚህም ማስረጃ ሲሰጡ ጦር አምጣ ብሎ እግዚአብሔርን ለምኗል፤ ገዳማቱም ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልዩለት ዕጣን አስጭኖላቸዋል ብለው ጽፈዋል። ታሪኩን በመቀጠል፥ ንጉሡ በጸሎት ያገኘው መቅሠፍት ስለጸናበት ተጸጽቶ ቅድስት ማርያምን ቢማፀን የኦሮሞዎች ዘመን መቼ እንሚፈጸም በራእይ ነግራዋለች ይላሉ። ሕዝቡ የሚያደርገውን ከማጣት የተነሣ ደብተራዎቹን ይጠይቃል። ደብተራዎቹም "ጋላ የሚመጣበትንና የማይመጣበትን፥ ቢመጣም የሚሸነፍበትንና የማይሸነፍነትን ቀን" መጽሐፍ ገልጠው (ኮከብ ቈጥረው) ለማግኘት *ሐሳበ ጋላ* እስከ መድረስ በቅተዋል[41] ። የጻድቃኑ ገድል ጸሐፊዎችም ጻድቆቻው ከኦሮሞ ወራሪ እንዳዳኗቸው የሚያሳይ ተአምር ደርሰውላቸዋል። አንዱ በአፄ ሱስንዮስ ዘመን የኖሩ የአባ ሐራ ድንግል ገድል ነው። ታሪኩን ከሌላ ቦታ ስላላየሁት አዲስ ሊሆን ይችላልና እንጥቀሰው[42]፤

*እንዘ ይገብር ምግባራተ ንጹሐተ ውስተ ገዳሙ ቅድስት ተሐውከት አሜሃ ኵላ ሀገር በጸቢዓ አረሚ ዘይብልዎ ወርዳያ። ብዙኃነ ሰብአ ቀተለ በእዴሁ፤ ወብዙኃነ ሰብአ ጼወወ። ወማህረከ አልህምተ ወአባግዓ ወእንስሳተ ብዙኃተ ዘሀለዋ ኵሎን አህጉራተ እንበለ ያትርፍ ፩ሂ እምኵሉ ሀገር።*

*ወበውእቱ ጊዜ መጽአ ጸባኢት ብዙኃን ኀበ ዝንቱ ብሔር። ወቆሙ መንፈቆሙ በክሐ ወመንፈቆሙ በለፌ፤ ወኢበጽሑ ኀበ ገዳሙ ለአቡነ እንተ ሀለወት ማዕከሌሆሙ እንዘ ይሬእይዋ ወይጉጕኡ ለበጺሖታ እስመ ከልአሙ መልአከ እግዚአብሔር፣ ወአፍርሆሙ ከመ ይርኃቁ እምአድያሚሃ ወእምጽናፌሃ ለገዳሙ። ወተመይጡ እሙንቱኒ ነገደ አረሚ እምሀገረ አቡነ ኀበ ካልእ ሀገር ዘይጸብእዋ።*

❖

(አባ ሐራ ድንግል) በቅድስት ገዳሙ ውስጥ ንጹሕ ሥራዎች ሲሠራ ወርዳያ በሚሉት አረሚ ጦር ምክንያት ሀገሪቷ በሞላ ተሸበረች።

ተዘርተውበት ነበር፤ በየትኛውም የአውሮፓ ዩኒቨርስቲ (ቢደረግ) የሚደነቅ የሊቅነት ትርኢት ይሆን ነበር")።

40. የጎጃም ታሪክ፥ EMML 5403, f. 62b.



በእጃቸው ብዙ ሰው አጠፉ፡ ብዙ ሰውም አጋዙ። ከብትም፣ በጎችም በየአገሩ ያሉትን እንሰሶች አንዳችም አገር ሳያስተርፍ ዘረፈ።

በዚያን ጊዜ ብዙ ጦረኞች ወደዚህ ሀገር መጡና ግማሾቹ በዚህ ግማሾቹ በዚያ ቆሙ። እያዩዋትና ሊደርሱባት ቢጣደፉም በማህላቸው ወዳለችው ወደ አቡነ (ሐራ ድንግል) ገዳም አልደረሱም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር መልአክ ከልክሏቸዋል፤ ከገዳሙ ሀገሮችና ከድምበሯም እንዲርቁ ፍርሃት ጣለባቸው። እነዚያ የአረሚ ነገድ የአቡነ (ሐራ ድንግልን) ሀገር (ትተው) ወደሚወጉት ወደሌላ አገር ፊታቸውን አዞሩ።

ሕዝቡ የመንግሥት እርዳታ ለመጠየቅ ቢሞክርም፥ መንግሥትና ወታደሩ ያሉት ሩቅ በመሆኑ መልክቱ ሳይደርስ የኦሮሞዎች አደጋ ይቀድማል። አባ ባሕርይ ስለ ዳሞት ጥፋት ሲጽፉ "አገሪቷን የሚያድንና የሚያስጥል የሌለ ሆኖ ሲያገኛት ሰውና ከብት አጋዘ" ያሉት ለማንኛውም አውራጃ የሚጸና አነጋገር ነበር (ክፍል ፲፬ን ተመልከት)።

በዚያ ላይ የክርስቲያኑ መንግሥት ከእስላም ኃይል ጋራ የጀመረው መጨረሻ አልባ ትግል በግራኝ መሪነት የክርስቲያኑን ሕዝብ ጉልበት ሰብሮት፥ ቅርሱንም እንዳያንሰራራ አድርጎ መትቶት ነበረ። ይህ በመቶ በሚቈጠሩ ዓመታት ከግራኝ በፊት የጀመረ ጦርነት በግራኝ ሞት አላከተመም፤ በመቶ ለሚቈጠሩ ዓመታት ቀጥሏል። በምሥራቅ ከአዳሎች ጋራ፥ በሰሜን ከቱርኮች ጋራ ይዋጉ ነበረ። ለምሳሌ አፄ ሠርፀ ድንግል ከደምቢያ እየተነሣ ዳሞት፥ ጉራጌ፥ እናርያ ብዙ ጊዜ፥ ዋቢ ሸበሊ ወንዝ አንድ ጊዜ፥ ደኸኖ (ምፅዋ) ሁለት ጊዜ ዘምቷል። ኢትዮጵያን የሚያውቃትና ያንን ሁሉ ወጣ ገባ መንገድ በእግርና በከብት ለመጓዝ ያለበትን ድካምና የሚፈጀውን ጊዜ የሚገምት ሰው አገሪቷ ለወራሪ ክፍት እንደነበረችም መገመት አያዳግተውም።

ሁለተኛም፡ የመንግሥቱ ሠራዊት የኦሮሞዎቹን ያህል የጦር ስልትና ጨክኖ እየተዋደቁ የማሸነፍ ፍላጎት ያላቸው አይመስሉም።

41. ለምሳሌ፥ EMML 5298, f. 153b. ኮከብ የሚቈጠረው በተፈራው ጎሳ ስም (ወርድያ፡ አበጢ፣ ወዘተ)፥ በሀገሩ ስም (ደምቢያ፥ ወሊቃ፣ ወዘተ)፥ በወሩ (ታኅሣሥ፥ የካቲት፥ ወዘተ)፥ በወንጌላዊው (ማቴዎስ፥ ሉቃስ፥ ወዘተ) ሆኖ በ6 ይገደፋል። ውጤቱ 1 ከሆነ ወሬ ብቻ ነው፤ 2 ከሆነ አይመጣም፤ 3 ከሆነ (ይመጣል) ሰውም ከብትም ያገኛል፤ 4 ጥሩ ነው (ጋላ) አይመጣም። 5 ይመጣል፡ ሰው ያጠፋል።

42. *ገድለ አባ ሐራ ድንግል*፥ EMML 69, f. 41ab, Macomber, *A Catalogue of Ethiopian Manuscripts*, Vol. I, p. 71. ታሪኩ አባ ባሕርይ በ*ዜናሁ ለጋላ* ክፍል ፲፯ ውስጥ የነገሩን ሳይሆን አይቀርም። ጎጃም ውስጥ የዲማ ጊዮርጊስም ተአምር ሠርቷል። በቀዳማዊ ኢያሱ ዘመን (ደጃዝማች) ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያኑን ሲያሠራ አራት ቤት ቱለማዎች ወረው ነበረ። በሰማዕቱ እርዳታ ተሸነፉ (EMML 5747, ff. 141b-142b)።

የሠራዊቱ ዓላማ ዝርፊያ ስለነበረ ባካባቢያቸው የሚዘረፍ ካገኙ የሩቁን ሕዝብ ለማዳን ሲጠሩ ያጕረመርማሉ[43]::

ሶስተኛ፥ ንጉሥ ሲሞት አዲስ ንጉሥ የበላይነቱን የሚይዘው ጥቅመኞች መኳንንት የራሳቸውን ሰው ለማንገሥ "እስራኤላውያኑን" ከወህኒ እያወረዱ ረጅም ጊዜ የሚፈጅ፥ ብዙ ሕዝብ የሚጨርስ፥ ብዙ ንብረት የሚያወድም ትግል ካካሄደ በኋላ ነው:: አንዳንዶቹማ ክርስቲያኖች ነን እያሉ የአዳሉ አሚር በላያቸው እንዲነግሥ እስከመላላክ ደርሰዋል[44]::

አራተኛ፥ የሃይማኖት ጭቅጭቅ ያስከተለው ኋላ ቀርነት በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: "ባሕታዊያን" ከንጉሡ ዘንድ በጓሮ ገብተው "ይህንን ሃይማኖት (ቅብዓት ወይም ጸጋ) ካልያዝክ የግዛት ዘመንህ ባጭር ይቀጠፋል" ይሉታል:: ይሄ እንዲደርስበት የማይፈልግ ንጉሥ ሃይማኖቱን ሲለውጥ፥ አንዱ ሃይማኖት በነገሠበት ጊዜ የተሰደዱት (ስዱዳን) ይመለሳሉ፤ በሥልጣን ላይ ያሉት ተራቸውን ስዱዳን ይሆናሉ፤ እርስ በእርስ መጨራረስ ይጀምራል:: አፄ ሱስንዮስ ሃይማኖቱን የለወጠውና በዚህም ምክንያት ረጅም ጊዜ የፈጀና በመቶ ሺህ የሚቈጠር ሕዝብ ያለቀበት የእርስ በርስ ጦርነት የተካሄደው አሮሞዎች ለዝርፊያ በጕለበቱበት ዘመን ነው::

ሌሎቹን የድክመት ምክንያቶች አባ ባሕርይ በቅርብ ሆነው ታዝበው በዜናሁ ለጋላ ውስጥ አንድ ሙሉ ክፍል ሰጥተው ዘርዝረዋቸዋል (ክፍል ፲፱ን ተመልከት)::

ከትንተናቸው የምንገነዘበው ግራኝ በወታደር ብቻ ያሸነፈውን መንግሥት ሞላው የኦሮሞ የሉባ ትውልድ የጦር ሠራዊት ሆኖ ሲዘምትበት ቢያሸንፈው የማይገርም መሆኑን ነው:: የኦሮሞዎች ዋና ዋናዎቹ የኀይል ምንጮች ሶስት ናቸው፤

<u>አንደኛ፥</u> በየስምንት ዓመት አዲስ ትውልድ ሲተካ አዲሱ የግዝረት ትውልድ ዘመናቸውን የሚጀምሩት በኅብረት ተገዝረው አዲስ ሹም ተክተው፥ ትንሽ ትልቅ ሳይሉ ሁሉም አብሮ በመዝመት አዲስ ሀገር

43. Pereira, *Chronica de Susenyos*, p. 108: "ከጥቂት ጊዜ በኋላ (ሱስንዮስ) በወሊቃ ያለውን ጋላ ሊወጋ መሄድ ፈለገ:: የንጉሡ ሠራዊት ሲሰሙ እንዲህ ሲሉ አጕረመረሙ፥ "በአንድ በጋ ጋላን አራት ጊዜ ድል አደረግን፡ ደግሞ አሁን እንዴት ወደጋላ ዘመቻ ይወስደናል?" ንጉሡ እንደ ተሳነፉበት ሲሰማ ይህንን ጉዳይ ተወው::"

44. የአፄ ዮሐንስ/አእላፍ ሰገድን ታሪክ ገጽ 28 ላይ ብንመለከት እንዲህ የሚል እናገኝበታለን፡ በዚህ ወር ውስጥ ፋሬስና ዘማርያም የጌታችንን የንጉሥ ነገሥት አዕላፍ ሰገድን መንግሥት ለማፍለስ ፈልገው ለአደሉ ሹም እንዲህ ሲሉ ላኩበት፤ "እነሆ ፈረስና ፫ በቅሎዎች ከብዙ ንብረትና ገረዶች ከሚሆኑህ ከተማረኩ ሴቶች ጋራ ልከንልሃል:: እኛም አምነንብሃል፥ እንገዛልሃለንም፤ ብቻ በኛ ላይ እንድትነግሥ አመጣጥህን አፋጥን::"



በኅብረት በመምታት መራቸውን (ግዴታቸውን) በማውጣት ነው:: አውሬ ወይም "ሲዳማ" (ነገዱ ኦሮሞ ያልሆነ ማለት ነው) ያልገደለ ቅማል ቢፈጅውም እንኳን ጠጉሩን አይላጭም፤ ሕጋቸው ነው:: ራስ ላይ ከቁንጮ የበለጠ ጠጉር መታየት የሀፍረት ምልክት ነው:: ካገባም ሚስቱ "የጠጉራም ሚስት" እንዳትባል፥ ክብሩንና ክብሯን ለማስጠበቅ የሚያስፈልገውን ያደርጋል:: ቀናው መፍትሔ "ሲዳማ" መግደል ነው:: ካልገደለ "የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት" እድሜ ልኩን ሐዘንተኛ ሆኖ ይሞታል::

<u>ሁለተኛ፥</u> ድንገት ካልተደረሰባቸው በቀር ምንም ቢሆን ከጠላት ጦር ጋራ ፊት ለፊት ውጊያ አይገጥሙም:: የጦር ኀይል መምጣቱን ሲሰሙ በተገኘው አቅጣጫ ሁሉ ይሸሻሉ፤ ሲሸሹ ገደል አይመልሳቸውም:: የሚወሩት ሰላማዊውን መንደር ሲሆን ምሕረት የሚባል ባህል የላቸውም:: አባ ባሕርይ ክፍል ፲፬ ላይ፥ "ዳሞትን ... የሚያድንና የሚያስጥል የሌለ ሆኖ ሲያገኙት ጊዜ ሰውና ከብት አጋዘ" ያሉትን ማስታወስ ይበቃል:: በሕዝቡ ሰላማዊነት ያላግጡበታል፤ "ከብት" ይሉታል:: ሰዎች የክርስትና ጥምቀት ሲጠመቁ አይተው፥ እያሳደዱ ከውሐ ይደፍቁና፥ "ባሕር የሚለብሱትን ሲዳማዎች ከባሕር ገፈተርኳቸው" እያሉ ይፎክራሉ (*የዜናሁ ለጋላን* ክፍል ፲፩ ተመልከት)::

ፋሲልን የሚያህል የዘመኑን ትልቅ ባለሥልጣን እንደገደሉ አባ ባሕርይ ነግረውናል (ገጽ 79):: ቢዘመትባቸው ምን እንዳደረጉ ከአፄ ሠርፀ ድንግል ታሪክ ውስጥ የተመዘገበውን እንመልከት[45]፤

*እምድኅረ ዝንቱሰ ንትመየጥ ኀበ ዜና ፍኖቱ ለንጉሥ መለክ ሰገድ ዳግማዊ ቈስጠንጢኖስ ዘአጸወ አብያተ ጣዖታት ወአርኃወ አብያተ ክርስቲያናት:: ወበራብዓዊ ዕለት እምዕለተ ክርስትና አመ ሠላሳሁ ለወርኃ መጋቢት ተንሥአ እምውእቱ ሰፍራ ወአርትዓ ፍኖቶ መንገለ ወጅ ለጸቢአ ጋላ:: ዝንቱሰ ሑረቶሙ ኮነ በወርኃ ዐቢይ ጾም:: ወበመኃትው ፋሲካ በጽሑ ሴፍ በር::*

*ጋላሰ ሶበ ሰምዑ ዜና ምጽአቱ እንዘ ሀለዉ በጕራጌ ፍርሃት ወረዓድ አኀዞሙ ወጐዩ ምስለ አንስቲሆሙ ወደቂቆሙ ወአልህምቲሆሙ ወተዘርዉ ውስተ ኵሉ ፍናዋት ከመ ተዘርዎተ ጢስ እምገጸ ነፋስ:: ወእምዝ መከረ ከመ ይጽብእ ለጋላ ዘሀሎ በበጥራሞራ ዘይትበሀል ዳዌ ዘአንጐሎ ለፋሲሎ ምስለ ሰራዊቱ::*

*ውእቱኒ ሶበ ሰምዐ ዜና ምጽአቱ ለዝንቱ ንጉሥ ግሩም ዘይጌርም እምነገሥተ ምድር ጐየ ርሑቀ እስከ ተኃጥአ አሰረ ሀላዌሁ:: ወሶቤሃ መከሩ ዓበይተ መንግሥት እንዘ ይብሉ ምንተ ነኃሥሥ እምድኅረዝ:: ናሁ ተኃጥአ አሰረ ጋላ ወኢተአውቀ ኀበ ሖረ:: እክልኒ ለዘረፋ ወለመሸመቻ ተኀጥአ፤ ናሁ ጸንአ ረሀብ በከተማነ:: እምድኅረ ዝንቱሰ*

45. Conti Rossini, *Historia, Regis Sarṣa Dengel (Malak Sagad)*, pp. 127-8.

*ንትመየጥ ውስተ ከተማን ዘይእቲ አሐቲ ጉባኤ እንተ ሐዋርያት አኮኑ ተብህለ ይኄይስ መዊት በኵናት እመዊት በረኃብ:: ውእቱኒ ተሰጥዎሙ እንዘ ይብል፥ አሆ ይኩን በከመ ትቤሉ:: ወዘንተ ብሂሎ ሜጠ ገጾ ወረሰየ ፍኖት እንተ ፍኖተ ጉራጌ ወሑረቱኒ ኮነ ጕጕአ::*

*ወእንዘ ሀለዉ በጉራጌ ነሥአ ቦሻ ሹም ጥምቀተ ክርስትና አመ ፳ወ፫ ለወርኃ ሚያዝያ በዕለተ ዕረፍቱ ለቅዱስ ጊዮርጊስ:: ወኮነ ሎቱ ተሐባቤ ዝንቱ ንጉሥ መሲሐዊ ርቱዓ ሃይማኖት፣ ወወሀቦ ሥርጋዌ ዘይዔድም ለዓይን ወሰመየ ስሞ ጊዮርጊስ:: ወወሀቦ መምህረ መንፈሳዌ ከመ ይምሐሮ ሃይማኖተ ወከመ ያጥምቅ ኵሎ ሰብአ ሀገሩ:: ወበዘ ከመዝ ግብር አስተፋነዎ ወሖረ ብሔሮ በሰላም::*

*ወእምድኅረዝ አርትዓ ፍኖተ በቀዳማዊ ፍኖት ዘመጽአ ባቲ:: ሰብአ ሐዴጌሰ ኮነ ይጽሕቁ በጺሐ በፍጡን ለለ አብያቲሆሙ ወለለ ሥርዓቶሙ:: ወብጽሐቶሙኒ ኮነ ኀበ ጉባኤ አመ ረቡዑ ለወርኀ ሐምሌ ዘበሳኒታሁ ተዝካረ ዕረፍቶሙ ለጴጥሮስ ወጳውሎስ ብርሃናተ ዓለም::*

*ዝንቱሰ ኵሉ ኮነ በ፳ወ፯ዓመተ መንግሥቱ ለንጉሥ መለክ ሰገድ:: ይእቲ ክረምት ኮነት ክረምተ ሣህል መምሕረት፥ ክረምተ ትፍሥሕት ወኃሤት::*

❖

ከዚህ በኋላስ አብያተ የጣዖትን ዘግቶ አብያተ ክርስቲያንን ወደከፈተ ወደ ዳግማዊ ቈስጠንጢኖስ ወደ ንጉሥ መለክ ሰገድ (ሠርፀ ድንግል) ጉዞ እንመለስ:: ከክርስትና ዕለት (ከስቅለት) በአራተኛይቱ ቀን፥ በመጋቢት ሰላሳ፥ ከዚያ ቦታ ተነሥቶ ጋላን ሊወጋ መንገዱን ወደ ወጅ አቀና:: ይኸ ጉዟቸው በዐቢይ ጾም (በሑዳዴ) ነበረ:: በፋሲካ ዋዜማ ሴፍ በር ደረሱ:: ጋሎች ግን መምጣታቸውን ሲሰሙ በጉራጌ እንዳሉ ፍርሃትና ድንጋጤ ያዛቸው:: ሴቶቻቸውን፥ ልጆቻቸውን ከብቶቻቸውን ይዘው ሸሹ፣ ጢስ ከነፋስ ፊት እንደሚተን በየአቅጣጫው ተነኑ::

ከዚያ በበጥራሞራ ያሉትን ፋሲሎን ከነሠራዊቱ ያበላሹትን ዳዌ የተባሉትን ጋሎች ሊወጋ ወሰነ:: እነሱም የዚህን ከምድር ንጉሦች ሁሉ የሚያስገርም ባለግርማ ንጉሥ የመምጣት ወሬ ሲሰሙ ያሉበት ፈለጉ እስኪጠፋ ድረስ ርቀው ሸሹ::

በዚህ ጊዜ የመንግሥቱ ታላላቅ ሰዎች "ከዚህ በኋላ ምን እንፈልጋለን? እነሆ የጋላ ፈለጉ አልተገኘም፤ ወዴት እንደሄደ አልታወቀም:: እህልም ለዘረፋም ሆነ ለሽመታ የለም:: እነሆ በሰፈራችን ረኀብ ጠና:: እንግዴህስ የሐዋርያት ጉባኤ ወደሆነችው ወደመዲናችን እንመለስ:: በረኀብ ከመሞት በጦር መሞት ይሻላል አልተባለምን?"[46] ሲሉ ምክር አቀረቡ:: እሱም "እሺ፥ እንዳላችሁ ይሁን" ሲል መለሰላቸው:: ይኸንን ተናግሮ ፊቱን አዙሮ መንገዱን ወደ ጉራጌ አደረገ:: ሂደቱም በጥድፊያ ነበረ::

በጉራጌ ባሉበት ጊዜ፡ ሚያዝያ 23 ቀን፡ የቅዱስ ጊዮርጊስ ዕረፍት ዕለት፡ ቦሻ ሹም ክርስትና ተነሣ:: ይህ አርቶዶክሳዊው መሲሐዊ ንጉሥ ዋስ (የክርስትና አባት) ሆነው:: ለዓይን የሚያስገርም ጌጥ ሰጠው:: ስሙንም "ጊዮርጊስ" አለው:: ሃይማኖት እንዲያስተምረውና የሀገሩን ሰዎች ሁሉ እንዲያጠምቅ መንፈሳዊ መምህር ሰጠው:: (ጊዮርጊስን) በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ሸኝቶት ወደሀገሩ በሰላም ተመለሰ::

ከዚህ በኋላ በመጣበት በፊተኛዋ መንገድ ጉዞውን አቀና:: የሐዴጌ ሰዎችም ቶሎ በየቤታቸውና በየትዳራቸው እንዲደርሱ ይጓጉ ነበረ:: ከጉባኤ (ከከተማቸው) የደረሱትም፥ በማግስቱ የዓለም ብርሃናት ጴጥሮስና ጳውሎስ ዕረፍታቸው በሚሆንበት በሐምሌ አራት ቀን ነበረ::

ይህ ሁሉ የሆነው በንጉሥ መለክ ሰገድ 27ኛ ዓመተ መንግሥት ነው:: ያቺ ክረምት የይቅርታና የምሕረት ክረምት፥ የደስታና የመደሰቻ ክረምት ሆነች::

ሶስተኛ፡ አሮሞዎች መዋጋት ካለባቸው፥ ጭፍራ የሚሉት የጦር ስልት አላቸው፥ ሁሉም ባንድነት ሄደው ከጠላት ላይ ይረባረቡበታል:: ለዚህ ምሳሌ የሚሆን አፄ ሱስንዮስን እንዴት እንደመቱት ገጽ 146-150 ላይ እናያለን፤ አሁን የኦሮሞዎች ሰብአ ትካታዊ ወረራ ምን እንደሚመስል ከዚህ በታች የተጠቀሱት ዘገባዎች እንጨምር::

ከአፄ ሠርፀ ድንግል (1555-1589 ዓ. ም.) ታሪክ[47]፡

*ወእምድኅረ በዓለ ፋሲካ ተንሥአ እምደምብያ ከመ ይሖር ሸዋ፥ እስመ ጕጕኡ ውእቱ ለዓቂበ ሀገር እምነ ጋላ:: እስመ ሸዋ ሀገረ መንግሥት ይእቲ:: ወአሜሃ ወሀበ ሐርቦ አምኃ ለአስተፋንዎቱ አፍራሰ ኀሩያነ ዘኢየኃፅፅ እምዘ ወሀበ ይስሐቅ፥ በውእቱኒ ጊዜ ዳግመ ነሥአ ቡራኬ:: ዝኮሉ ሀብተ ሐርቦ ኮነ በምክረ ሠርፀ ክርስቶስ ማእምር ወለባዊ ላዕሌሁ ሰላም፥ ይምሐሮ ወይሠህሎ እግዚአብሔር::*

*ወእምዝ አርትዐ ፍኖቶ መንገለ ግንድ በረት:: ወከረመ በህየ:: ወኃሊፎ ወርኃ ክረምት ሰምዓ ከመ መለክዋ ጋላ ለምድረ ወጅ:: ወሶቤሃ ለአከ ውስተ ኵሉ አህጉረ መንግሥቱ ከመ ይትጋብኡ ጪዋ እምለፌ ወእምለፌ:: ወለአከ ጐግርም ኀበ ዘርአ ዮሐንስ፥ ውነበ ተክለ ጊዮርጊስ ዳሞት ጸሐፈ ላም፥ ውኀበ ዳኅረኀት ወጅ ቃጽ ከመ ይምጽኡ ኵሎሙ ምስለ ኲሉ ሠራዊተ ፀብአሙ::*

*ወሶቤሃ ተንሥአ እምግንድ በረት ወተራከበ በወረብ ምስለ እሉ ዘዘከርናሆሙ:: ወሶበ በጽሐ ወጅ ረከቦሙ ለጋላ በማየ ወበወጅ*

---

46. ሰቆቃወ ኤርምያስ 4፡ 9::

47. Conti Rossini, *Historia, Regis Sarṣa Dengel (Malak Sagad)*, pp. 44-5.

*መሊአሙ ኵሎ ምድረ ምስለ አልህምቲሆሙ ወደቂቆሙ ወአንስቲያሆሙ። ወነጥአ ፍኖተ ኀበ የሐውሩ እስመ መልአ አልህምቲሆሙ ውስተ ኵሉ መካን። ወእምብዝኖሙ ለአልህምት ኢይትረአይ ፅምስለ ካልኡ። ወእምዕፁብ ግብር የሐውሩ እንዘ ይነድኡ አልህምተ ለፌ ወለፌ ከመ ይርከቡ ፍኖተ። ጋላኒ ኢየእመረ ምጽአቶሙ ለዘመጠነዝ ሠራዊት ዘይከድንዋ ለምድር እንዘ የሐውሩ።*

*ወሥርዐተ ፀብአሙሰ ኮነ በሠለስቱ ጸታ። ቀዳማዊ ጸታ ረከብዎ ሊጋላ ኀበ ተዐይኑ። ወሶበ ርእዮሙ ግብተ ተንሥአ ወተፃብአሙ። ወእምዝ ተታለዉ ክልኤቱ ጸታ አሐዱ ድኅረ አሐዱ፡ ወተፃብእዎ፥ ወቀተሉ እምኔሁ ብዙኃ ዘአልቦ ኍልቌ እስከ አንስቲሆሙ ወደቂቆሙ። አልህምተሰ ኢማህረኩ አላ ዴገንዎ ለዘአምሠጠ ወጐየ እምኔሆሙ እስከ ፈጠጋር ወደዋሮ። ወኢያትረፉ እንበለ ኅዳጣን። ወእንዘ ይትመየጡ እምሰዳዳ ማህረኩ አልህምተ ዘኃደግዎሙ ቀዳሚ። ወአኀዙ በበዐሠርቱ ምእት ወበበ ኃምስቱ ምእት። ኵሉ ማኅረከ አምጣነ ክሂሎቱ። ሰብአ ሀገርኒ ነሥኡ ዘየአክሎሙ ወኃደጉ ዘተሥእኖሙ። ወእምአመ ወፅአ ጋላ አልቦ ዘገብረ መኑሂ ዘከመዝ ኃይለ ዐቢየ በሠርዎተ ጋላ ኢእምእስላም ወኢእምክርስቲያን። ስብሐት ለእግዚአብሔር ክቡር ወልዑል ገባሬ ኃይል በእደ መሲሑ ሠርፀ ድንግል።*

❖

ከፋሲካ በዓል በኋላ (ሠርፀ ድንግል) ወደሸዋ ለመሄድ ከደምቢያ ተነሣ፣ ምክንያቱም ሀገሪቱን ከጋላ ለመጠበቅ ችኩል ነበረ። ሸዋ የመንግሥት ሀገር ነችና። በዚያን ጊዜ ሐርቦ ለመሸኛ የሚሆኑ (ባሕር ነጋሽ) ይሥሐቅ ከሰጠው የማያንሱ ምርጥ ፈረሶች ገጸ በረከት ሰጠ። በዚህም ጊዜ ድጋሚ ቡራኬ (ምስጋና) አገኘ። ይህ ሁሉ የሐርቦ ሀብት የተገኘው በዐዋቂውና በአስተዋዩ (በአፄ ሠርፀ ድንግል መምህር) በሠርፀ ክርስቶስ ምክር ነው፣ ሰላም ይረፍበት፣ እግዚአብሔር ይማረው፣ ይቅር ይበለው።

ከዚህ በኋላ መንገዱን ወደግንደበረት አቀና። ክረምቱንም እዚያ አሳለፈ። የክረምት ወራት ሲያልፍ ጋሎች ምድረ ወጅን እንደተቈጣጠሯት ሰማ። በዚህ ጊዜ ትክለኛ የጦር ሠራዊት (ጨዋ) ከዚህም ከዚያም እንዲሰበሰቡ በመንግሥቱ አውራጃዎች ሁሉ መልእክት አስተላለፈ። ሁሉም ከመላ ጦር ሠራዊታቸው ጋራ እንዲመጡ ጐዣም ወደ (ጐዣም ነጋሽ) ዘርአ ዮሐንስ፡ ወደ ዳሞት ጸሐፌ ላም ተክለ ጊዮርጊስ፥ ወደ ወጅ ቃጽ ዳኅረጎት ላከባቸው።[48]

በዚያን ጊዜ ከግንደበረት ተነሥቶ ወረብ ላይ ከነዚህ ከአነማናቸው ጋራ ተገናኘ። ወጅ ሲደርስ ጋሎችን ከከብቶቻቸው፥

48. "ጐዣም ነጋሽ"፡ "ዳሞት ጸሐፌ/ፌ ላም"፡ "ወጅ ቃጽ" የሀገረ ገዢዎች የማዕርግ ስሞች ናቸው።



ከልጆቻቸው፡ ከሴቶቻቸው ጋራ በማያ እና በወጅ በሞላ መሬቷ ጢም ብለውባት አገኛቸው። (ሠራዊቱ) ማለፊያ መንገድ አጡ፣ ምክንያቱም ከብቶቻቸው በቦታው ሁሉ ሞልተውበት ነበረ። ከከብቶቹ ብዛት የተነሣ (ሰው) አንዱ ከሌላው አይተያይም ነበረ። መንገድ ለማግኘት ከብቶቹን ወዲያና ወዲህ ሃይ እያሉ በጭንቅ ሁኔታ ይሄዱ ነበረ። ጋሎች ደግሞ ሲጓዝ መሬቷን የሚሸፍናት ይኸን የሚያህል ሠራዊት መምጣቱን አላወቁም።

(የንጉሡ ሠራዊት) የውጊያ ሰልፋቸው በሶስት ክፍል ነበረ። ቀዳሚው ክፍል ጋሎችን እሰፈሩበት አገኛቸው። ድንገት ሲያይዋቸው ተነሥተው ተዋጓቸው። ከዚያ ሁለቱ ክፍሎች አንዱ ሌላውን እየተከተለ ወጓቸው። እስከ ሴቶቻቸውና ልጆቻቸው ድረስ ቍጥር የሌው ብዙ (ሰው) ፈጁ። ከነሱ ያመለጠውንና እስከ ፈጠጋርና እስከ ደዋሮ የሸሸውን አሳደዱ እንጂ (መጀመሪያስ) ከብት አልማረኩም። ከጥቂቶች በቀር ምንም አላስተረፉም።

ከማሳደድ ሲመለሱ በፊት የተዋቸውን ከብቶች ማረኩ። በየአንድ ሺው በየአምስት መቶው ወሰዱ፤ ሁሉም እንደችሎታው ማረከ። የሀገሩ ሰውም የሚበቃቸውን ያህል ወሰዱ፤ ያልቻሉትን (የትም) ተውት። ጋላ ከመጣበት ጊዜ አንሥቶ፥ ጋሎችን በመንቀል ከእስላምም ከክርስቲያንም እንደዚህ ከፍ ያለ ኀይል የፈጸመ የለም። በመሲሑ በሠርፀ ድንግል እጅ ኀይል ለሠራ ክቡርና ልዑል ለሆነው ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው።

ከአፄ ሱስንዮስ/ሥልጣን ሰገድ (1600-1625) ታሪክ[49]፥

*ወእንዘ ሀሎ በምድረ በድ መጽአ አሊ ወልደ አጅብ ምስለ አብድልቃድር ንጉሠ ስናር በምክንያተ ሀከክ ዘተንሥአ በውስተ ሀገሩ እንዘ ምስሌሁ ብዙኃን መስተፅዕናነ አፍራስ ወሰብአ እግር። ወነደረ ሎቱ ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ፥ ወኮኖ ንጉሠ ስናር ወዓሌ ወተአዘዘ ሎቱ ከመ ገብር። ወንጉሥኒ አሠነየ ሎቱ ኵሎ መፍቅዳተ ሥጋ፣ ወአሠርገዎ በአልባሰ ሐሪር ወበወርቅ አምባር ወኢያኅጥአ ምንተኒ እምዘ ፈቀደ። ምድረኒ ወሀቦ ጭልጋሃ። ወዘንተ ኵሎ እምድኅረ ገብረ ወዐለ በህየ በዐለ ልደት ዘለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት።*

*ወእምዝ ሶበ ሰምዓ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ከመ ተጐናደዩ አውፅኦ ጸባሕት ሰብአ ወንድጌ ወለግ ተምዕዓ ወአዘዘ ይፃህርከዎሙ፣ ወማህረኩ ብዙኃ አልህምተ። ወአጥፍኡ እክለ ወአውዐዩ አብያተ። ወኵሎሰ ዘተማህረከ አልህምተ እምነ ለግ ወሀበ ለንጉሠ ስናር ወለአሊ ወልደ አጅብ።*

*ወእምዝ ተንሥአ እምውእቱ መካን ወሖረ መንገለ ሳርካ፣ ወበጽሐ ኀበ መካን ዘሀለወ ቦቱ ንስቲት ባሕር ዘትሰመይ ገደማ። ወወዓለ በህየ*

49. Pereira, *Chronica de Susenyos*, pp. 103-7.

በዓለ ጥምቀቱ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት:: ወእምዝ ተንሥአ እምህየ ወሖረ እንተ ፍኖተ ጽላሎ፡ ወዓደወ ፈለገ አብይ ወበጽሐ ምድረ ቡዳ፡ ወአሰንበተ በህየ::

ወእምዝ ተንሥአ እምውእቱ መካን ዘአሰንበተ ቦቱ ወወረደ መንገለ ሣራ እንተ ፍኖተ ወንዳሳ:: ወበጽሐ ኀበ አሐቲ ሀገር ዘሀለወት በጽንፈ ፈለገ ሱኋ፡ ወአሰንበተ በህየ ወወዓለ በዓለ ቀበላ ጾም:: ወእምድኅረ በዓተ ጾም ተንሥአ እምውእቱ መካን ወሖረ ኀበ አሐቲ ሀገር ዘስማ ሻሼ እንተ ስፉሕ መርሕባ፡ ወበህየ ረሰየ ከተማሁ::

ወእንዘ ሀሎ በውእቱ መካን ተሰምዓ ዜና ምጽአተ ጋላ እመንገለ በረንታ:: ወሶበ ሰምዓ ተንሥአ በጊዜሃ፡ ወሖረ በጕጕአ፡ እስመ ጕጕእ ውእቱ ለፀብእ ከመ ይጔጕእ ብእሲ ርኁብ ለመብልዕ፡ ወብእሲ ጽሙእ ለስትይ:: ወእምቅድመ ሑረቱ ፈነዎሙ ለራስ የማነ ክርስቶስ ወለራስ ሥዕለ ክርስቶስ አኃዊሁ እንተ ካልእ ፍኖት:: ወንጉሥኒ ሖረ ምስለ እሊአሁ እንተ ካልእ ፍኖት:: ወአቅዲሞ ፈነዎ ለአቤተጐን ወልደ ክርስቶስ ዘኮነ ብላቴኖች ጌታ በውእቱ ዘመን ምስለ ኀዳጣን ሠራዊተ ፀብእ ጊዜ ፍና ሰርክ::

ወበጽባሕ ተለወ ንጉሥ አሰሮ ወረከቦ ለጋላ ዘውእቱ ወረንሻ በምልኡ ወካልእኒ ጋላ ዘእምነገደ በርቱማ ምስሌሁ በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት አመ ፲ወ፪ ለየካቲት በምድረ ለምጨን:: ወተቃተሉ ጋላ ወሠራዊተ ንጉሥ ዓቢየ ቀትለ:: ወኮነ መዊእ ለንጉሥ:: ወተቀትሉ አሜሃ ብዙኃን ጋላ:: ወእንዘ ይጕይይ ቦዘወድቀ ውስተ ጸድፍ ወውስተ ማይ ዘሀሎ ማእከለ ጸድፍ፡ እስከ ኮነ ውእቱ ማይ ደመ እምብዝኀ ተቀትሎቱ ለጋላ::

ወአኀዊሁሰ ኢረከቡ ጋላ እስመ ተሀከዩ በሙ ሰብእ፡ ወኢየንሑ መንገደ ወኢበጽሑ እስከ አባዊ::

ወእምድኅረ ዝንቱ መዊእ ፈቀደ ንጉሥ ከመ ይሖር መንገለ ወለቃ ከመ ይፅብኦ ለጋላ ዘሀሎ በህየ:: ወአንጕርጕሩ አቄትዘር፡ ወሕቀ ሐዊሮ ተመይጠ እንበይነ ዘአንጕርጕሩ ቦቱ ሰብአ ከተማ:: ወእምድኅረ ተመይጠ ረሰየ ከተማሁ ኀበ ጽንፈ ፈለገ ሱኋ::

ወእንዘ ሀሎ በህየ ሰምዓ ምጽአተ ጋላ እመንገለ ወሰን አምባ:: ወተንሥአ ንጉሥ በከመ ልማዱ እንዘ ይጔጕእ:: ወሖረ ወበጽሐ ኀበ ምድር ዘትሰመይ ዣን በድል:: ወበህየ ረከቦ ለሊበን ጋላ፡ ዓቢይ ነገድ ዘየዓቢ እምኵሎሙ ነገደ ጋላ፡ በምድረ ዣን በድል በጽንፈ ፈለገ ብር:: ወውእቱሰ ሊበን ብዙኀ ጥቀ ከመ አንበጣ ወማእምረ ፀብእ፡ ወኃያል ውእቱ እምኵሎሙ ኀያላነ ጋላ:: ማህረኮ ወአስተጋቢኦ ኵሎ አልህምተ ጋፋት፡ ወአልህምተ ጮሜ፡ አልህምተ አገው፡ ወአልህምተ ዳሞት፡ እስከ ሳከላ ወገበርማ አጥፊኦ ሀገረ፡ ወቀቲሎ ብዙኃነ ሰብአ፡ ወፄዊዎ ደቀ ወአንስተ:: እኂዞ ምህርካሁ እንዘ ይትመየጥ ሀገሮ ረከቦ ንጉሥ በምድረ ዣን በድል በዕለተ ሐሙስ አመ ፳ወ፩ ለየካቲት::



ወርእዮ ጋላ ከመ መጽአ ቦቱ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ምስለ ብዙኃን ሠራዊት ይቤ፡ ምንትኑ ዝነገር፡ አእዋምኒ ወኵሉ ዕፀው አድባርኒ ወኵሉ አውግር ያንሶሰዉ ከመ ሰብእ:: ወነበረ አሜሃ ጋላ ከዊኖ ለኀበ ፫ መ፱ ጭፍራ፡ ሉባ በባሕቲቱ፡ ቄሮ በባሕቲቱ፡ ቈንደላ በባሕቲቱ::

ወበጽሐ ንጉሥ ምስለ ኵሎሙ ሠራዊቱ መስተፅዕናነ አፍራስ በዓቢይ ጕጕአ:: ለሰብአ እግርሰ ኀደጎሙ ይትልውዎ በድኅሬሁ:: ወተፃብኡ ንጉሥ ወሊበን፡ ወኮነ መዊእ ለንጉሥ በጊዜ ዘይፈጥን እምቅጽበተ ዓይን:: ወተቀትለ ጋላ ዘአልቦ ኍልቈ:: አሜሃ አልቦ ብእሲ መስተፅዕነ ፈረስ እምኃያላኒሁ ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ዘኢቀተለ ጋላ ወዘኢያምጽአ ቸብቸቦ፡ ወወገሩ አምሳለ እብን አርአስቲሆሙ ለጋላ ውስተ ኵሉ ገጸ ምድር ኀበ ቆመ ንጉሥ:: ወዝንቱ መዊእ ኮነ በትእዛዘ እግዚአብሔር ክቡር ወልዑል፡ ይዕበይ ስሙ::

ዓዲ በሳኒታሁ ለውእቱ ዕለት ዕለተ ዓርብ አመ ፳ ወ፪ ለዝወርኀ ሰምዓ ንጉሥ ከመ መጽአ ጋላ ማህረኮ አልህምተ ብዙኃ ደቀ ወአንስተ እምነ ጋፋት ወአገው:: ወሖረ ቦቱ ንጉሥ ምስለ ኵሉ ሠራዊቱ:: ወሶበ ርእየ ጋላ ከመ መጽአ ንጉሥ ለፀቢአቱ ኢቆመ ለምዕር፡ ዳእሙ ጐየ ወገብአ ውስተ ጸድፍ ዘፈለገ ብር:: ወንጉሥኒ ተዓየነ በመልዕልቴሁ ወወረደ እንተ ካልእ ፍኖት ምስለ ኵሎሙ እጉዛነ ነፍጥ ወቀስት፡ ወዓርገ ኀበ ሀለወ ጋላ:: ወአኀዘ ይቅትሎሙ እምጊዜ ፫ ሰዓት እስከ ፍና ሰርክ፡ እስከ ኮነ ፈለገ ብር ኵለንታሁ ደመ::

ወእምድኅረ ምሴት ወፅአ ኀበ ትዕይንቱ ዘተዓየነ መልዕልተ ጸድፍ ከመ ይክልአ ሙፃአ ለጋላ:: ወጋላሰ ሀሎ አሜሃ ስቁለ ማእከለ ጸድፍ አምሳለ ሆባይ ወጦጣ፡ ኢይወርድሂ ወኢይወፅእ:: ወባሕቱ በይእቲ ዕለት ዘአምሰጠ እምቀትል ወሪዶ ሌሊተ እምጸድፍ በበ ንስቲት ንስቲት ሖረ መንገለ ሀገሩ::

ወእምዝ በሣልስት ዕለት ሰምዓ ንጉሥ ከመቦ ጋላ በቈላቲሃ ለኵንድል ዘትሰመይ ዘረገም:: ወሖረ ንጉሥ ምስለ ኵሉ ሠራዊቱ:: ወበጺሖ ረከቦ ለጋላ ዘስመ ነገዱ ዲገሉ በውስተ ውእቱ ምድር፡ እስመ ቦቱ ብዙኃ ምህርካ እንስሳ ወሰብእ:: ወውእቱኒ ጋላ ብዙኀ ጥቀ ፈረሰኒ ወእግር:: ወተፃብኡ ንጉሥ ወጋላ ዓቢየ ፀብአ:: ወኮነ መዊእ ለንጉሥ ወተመውአ ለጋላ:: ወተቀትለ ጋላ ዘኢኮነ ብዙኃ ወኢኅዳጠ፡ ወኀደገ ኵሎ ምህርካ አልህምት ዘኢይትኌለቍ:: ወንጉሥኒ ቀቲሎ አምጣነ ተቀትለ ወአኀዲኖ ኵሎ ምህርካሁ ተዓየነ ኀበ ምድር ዘትሜኒ ለትዕይንት::

ወዝንቱ መዊእ ኮነ በዕለተ ሰኑይ አመ ፳ወ፪ ለየካቲት:: ስብሐት ለእግዚአብሔር ወሀቤ መዊእ ለዘ ይትዌከል ቦቱ ወለዘያሰምክ በረድኤቱ::

❖

(ሱስንዮስ) በምድረ በድ ሳለ አሊ ወልደ (ኢብን) አጅብ ከስናር ንጉሥ ከአብድልቃድር ጋራ ሆኖ በሀገሩ በተነሣው ብጥብጥ ምክንያት ከብዙ ፈረሰኞችና እግረኞች ጋራ መጣና ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ አደረለት፡፡ የስናሩ ንጉሥ አሽከር ሆነለት፤ እንደአገልጋይም ታዘዘለት፡፡ ንጉሡም ለሕይወት የሚያስፈልገውን ሁሉ አሟመረለት፡፡ በሐር ልብስና በወርቅ አምባርም አስጌጠው፡፡ ከሚፈልገው ምንም አላሳጣውም፡፡ ምድርም ጭልጋን ሰጠው፡፡ ይኽንን ሁሉ ካደረገ በኋላ ክብር የሚገባውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል እዚያ አከበረ፡፡

ከዚህ በኋላ የወንድጌ እና የለግ ሰዎች ግብር ከማግባት እንደለገሙ በሰማ ጊዜ ተቆጥቶ (ሠራዊቱ) እንዲዘርፏቸው አዘዘ፤ ብዙ ከብቶች ማረኩ፡፡ እህል አጠፉ፤ ቤቶችም አቃጠሉ፡፡ ከለግ የተማረከውን ከብት ደግሞ ለስናሩ ንጉሥና ለአሊ ወልደ አጅብ ሰጣቸው፡፡

ከዚህ በኋላ ከዚያ ቦታ ተነሥቶ ወደ ሳርካ ሄደ፡፡ ገደማ የምትባል ትንሽ ኩሬ ካለችበት ቦታ ደረሰ፡፡ ክብር የሚገባውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀት እዚያ አከበረ፡፡ ከዚያ ተነሥቶ በጽላሎ መንገድ ሄዶ የአብያ ወንዝን ተሻገረ፤ ከምድረ ቡዳ ደረሰ፡፡ እሑድን እዚያ አሳለፈ፡፡

ከዚያም እሑድን ካሳለፈበት ቦታ ተነሥቶ በወንዳሳ መንገድ ወደዠራ ወረደ፡፡ ከሱኋ ወንዝ ዳርቻ ወዳለች አንድ አገር ደረሰ፡፡ እሑድን እዚያ አሳልፎ የጾም ቅበላ አደረገ፡፡ ጾም ከገባ በኋላ ከዚያ ቦታ ተነሥቶ መስኳ ሰፌ ወደሆነው ስሚ ሻሼ ወደሚባል አንዲት አገር ሄደ፡፡ ሰፈራውን እዚያ አደረገ፡፡

እዚያ ቦታ እንዳለ በበረንታ በኩል የጋላ መምጣት ተሰማ፡፡ (ንጉሡ ዜናውን) ሲሰማ ወዲያው ብድግ ብሎ በፍጥነት ሄደ፤ የተራበ ለምግብ፥ የተጠማ ለመጠጥ እንደሚቸኩል ለጦርነት ችኩል ነውና፡፡ ከመሄዱ በፊት ወንድሞቹን ራስ የማነ ክርስቶስንና ራስ ሥዕለ ክርስቶስን በሌላ መንገድ ላካቸው፡፡ ንጉሡ ደግሞ ከራሱ (ሰዎች) ጋራ በሌላ መንገድ ሄደ፡፡ ሲመሻሽ፥ በዚያን ዘመን የብላቴኖች ጌታ የሆነውን አቤተኑን ወልደ ክርስቶስን ከጥቂት የጦር ሠራዊት ጋራ አስቀድሞ ላከው፡፡

ጠዋት ንጉሡ ፈለጉን ይዞ ተከተለው፡፡ ጋሎችን፥ ማለት መላ ወረንሻንና ከነገደ በርቱማ ሌሎችንም ጋሎች፥ አብረው ሆነው ቅዳሜ ዕለት የካቲት 12 ቀን በምድረ ለምጨን አገኛቸው፡፡ ጋሎችና የንጉሡ ሠራዊት ታላቅ ግድያ ተጋደሉ፡፡ ድል ለንጉሡ ሆነ፡፡ በዚያን ጊዜ ብዙ ጋሎች አለቁ፡ ሲሸሹ ከገደልና አገደሉ ታች ካለው ውሐ የገባም ነበረ፡ ከጋሎቹ መገደል ብዛት ውሐው ደም ከመምሰል እስኪደርስ ድረስ፡፡

ወንድሞቹ ግን ጋላ አላገኙም፤ ሰዎቻቸው ተንተብባቸው፡ መንገድ አላረዘሙም፤ እስከ አባይ ድረስ (እንኳን) አልደረሱም፡፡



ንጉሡ ከዚህ ድል በኋላ ወለቃ ያለውን ጋላ ለመውጋት ወደዚያ ለመሄድ ፈለገ፡፡ ግን አቁትዠር (ሠራዊቱ) አጕረመረሙ፤ ትንሽ ሄዶ የሰፈሩ ሰዎች ስላጕረመረሙ ተመለሰ፡፡ ከተመለሰ በኋላ ሰፈሩን ከሱኋ ወንዝ ዳርቻ አደረገ፡፡

እዚያ ሳለ በወሰን አምባ በኩል የጋላን መምጣት ሰማ፡፡ ንጉሡ እንደልማዱ በጥድፊያ ተነሣ፡፡ ሄዶም ዠን በድል ከምትባል ምድር ደረሰ፡፡ እዚያ በብር ወንዝ ዳርቻ፥ ዠን በድል ምድር ላይ፥ ትልቁን ነገድ፥ ከነገደ ጋላ ሁሉ የሚበልጠውን፥ ሊበንን አገኘው፡፡ ይህ ሊበን እንዳንበጣ በጣም ብዙ፥ ጦር ዐዋቂ፥ ከኀይለኞቹ ጋሎች ሁሉ የበለጠ ኀይለኛ ነው፡፡ የጋፋትን ከብቶች፥ የሎሜን ከብቶች፥ የአገውን ከብቶች፥ የዳሞትን ከብቶች ሁሉ ማርኮና ሰብስቦ፥ እስከ ሳከላና እስከ ገበርማ ድረስ አገር አጥፍቶ፥ ብዙ ሰው ገድሎ፥ ሕፃናትንና ሴቶችን አግዞ ምርኮውን ይዞ ወደሀገሩ ሲመለስ ንጉሡ ዠን በድል ምድር ላይ ሐሙስ ዕለት የካቲት 24 ቀን አገኘው፡፡

ጋሎቹ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድን ከብዙ ሠራዊት ጋራ ሲያዩ፥ "ይህ ነገር ምንድነው? ዛፎቹም እንጨቶቹም ሁሉ፥ ተራሮቹም ጋራዎቹም ሁሉ እንደሰው ይንቀሳቀሳሉ" አሉ፡፡ በዚያን ጊዜ ጋሎቹ በሶስትና በአራት ሰልፍ ተደራጅተው ነበረ -- ሉባው ለብቻው፥ ቄሮው ለብቻው፡ ቈንደላው ለብቻው[50]፡፡

ንጉሡ ከፈረሰኛ ሠራዊቱ ሁሉ ጋራ በታላቅ ጥድፊያ መጣ፡፡ እግረኞቹን ከኋላው እንዲከተሉት ተዋቸው፡፡ ንጉሡና ሊበን ተዋጉ፤ ከዓይን ቅጽበት በሚፈጥን ጊዜ ውስጥ ድል ለንጉሥ ሆነ፡፡ ቊጥር የሌላቸው ጋሎች አለቁ፡፡ በዚያን ጊዜ ከንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ኀይለኞች ፈረሰኞች ውስጥ ጋላ ያልገደለና ቸብቸቦ[51] ያላመጣ (ሰው) አልነበረም፡፡ የጋሎቹን ጭንቅላት ንጉሡ በቆመበት ምድር ዙሪያውን እንደድንጋይ ከመሩት፡፡ ይህ ድል የሆነው ክቡርና ልዑል በሆነው በእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው፤ ስሙ ከፍ ከፍ ይበል፡፡

ደግሞ በዚያ ዕለት ማግስት ዓርብ ዕለት ሚያዝያ 25 ቀን ጋሎች ከጋፋትና ከአገው ብዙ ከብት፡ ሕፃናትና ሴቶች ማርከው እንደመጡ ሰማ፡፡ ንጉሡ ከሠራዊቱ ጋራ ሁኖ መጣባቸው፡፡ ጋሎቹ ንጉሡ ሊወጋቸው እንደመጣ ሲያዩ ለአንዳፍታም አልቆሙም፤ ሸሽተው በብር ወንዝ ገደል ገቡ፡፡ ንጉሡም ከበላዩ ሰፈረ፤ ነፍጥና ቀስት ከያዙት (ሠራዊቱ) ሁሉ ጋራ ሆኖም በሌላ መንገድ ወረደ፤ ጋሎች ወደአሉበትም ወጣ፡፡ ከሶስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽት ድረስ ይገድላቸው ጀመረ-- የብር ወንዝ ሁለንተናው ደም እስኪሆን ድረስ፡፡

ከምሽት በኋላ ከገደሉ አፋፍ ሰፈር ወደአደረገበት ሰፈሩ ጋላውን መውጫ ለመከልከል ወጣ፡፡ ጋላ ደግሞ በዚያን ጊዜ በገደል ማህል እንደዝንጀሮና እንደጦጣ ተንጠልጥሎ ነበረ፤ አይወጣ አይወርድ፡፡

50. እነዚህ ምን እንደሆኑ የዜናሁ ለጋላን ክፍል ፳ ተመልከት፡ ጸሐፊው እንዲህ ሲደረድራቸው ኦሮሞዎችን እንደሚያውቃቸው ያመለክታል፡፡

51. ስለ ቃሉና ስለ አንገት ቈረጣ ባህል፡ ገጽ 116፡ ኅዳግ ቍ. 24ን ተመልከት፡፡

ግን በዚያች ዕለት ከግድያ ያመለጠ በሌሊት ከገደል ወርዶ ጥቂት በጥቂት እየሆነ አገሩ ሄደ።

ከዚህ በኋላ በሶስተኛው ቀን ንጉሡ ዘረገም በምትባል የኮንድል ቈላ ጋላ እንዳለ ሰማ። ንጉሡ ከሠራዊቱ ሁሉ ጋራ ሆኖ (ወደዚያ) ሄደ። ሲደርስ የነገዱ ስም ዷገሉ የሆነ ጋላ በዚያ ምድር አገኘ፣ (አገሩ) ብዙ የእንስሳና የሰው ምርኮ ነበረበትና። ጋላውም በጣም ብዙ ነበረ፥ ፈረሰኞችና እግረኞች (ጭምር)። ንጉሡና ጋሎቹ ትልቅ ውጊያ ተዋጉ። ድል ለንጉሡ፥ ሽንፈት ለጋላ ሆነ። ብዙ ወይም ትንሽ ባይባልም ጋላ ተገደለ። ቍጥር የሌለውን የከብት ምርኮውን በሞላ ለቀቀ። ንጉሡም የተገደለውን ያህል ገድሎ፣ ምርኮውን ሁሉ አስጥሎ ለሰፈራ ከምትመች ምድር ሰፈረ።

ይህ ድል የሆነው ሰኞ ዕለት የካቲት 22 ቀን ነው። ለሚታመንበትና ረድኤቱን ድጋፍ ለሚያደርግ ድል ለሚሰጥ እግዚአብሔር ምስጋና ይግባው።

ገለልተኛው ዜና መዋዕል በአፄ ፋሲል ዘመን (1625-1660) ከመዘገበው[52]፤

*መስከረም፣ ዕለቱ ቀዳሚት ሰንበት፣ ወንጌላዊ ማቴዎስ፣*

*ሖረ ጎገርም። ወበውእቱ ዘመን መጽአ ጋላ ብሔረ ትግሬ ዘስሙ ለበቻ መጠነ ፵ሲ.ህ ጋላ፣ ወአጥፍአ ሰራዊ። ወበተመይጦቱ አገትዎ ሰዩማነ ዕራዕ ወተምቤን ወአሕለቅዎ እንበለ አትርፎ በምድረ አላ። ወነበረ ንጉሥ በዶቢት። ወሞተ ወልዱ ዘበኵሩ አቤቶ ቈስጠንጢኖስ።*

*ተፈጸመ ፱ ዓመት።*

❖

መስከረም፥ (የ1633 ዓ. ም. መጀመሪያ) ዕለቱ ቅዳሜ፣ (ዘመኑ) ማቴዎስ፣

(ንጉሡ) ጎጃም ሄደ። በዚህ ዓመት ስሙ ለበቻ መጠኑ አርባ ሺህ የሆነ ጋላ ወደትግሬ መጣ፣ ሰራዊቱንም አወደማት። ሲመለስ የዕራዕና የተምቤን ሹማምንት በምድረ አላ ላይ ከበው ምንም ሳያስተርፉ ፈጁት። ንጉሡ በዶቢት ተቀመጠ። የበኸር ልጁ አቤቶ ቈስጠንጢኖስ ሞተ።

(የግዛቱ) ፱ኛ ዓመት ተፈጸመ።

ቀዳማዊ ዮሐንስ/አእላፍ ሰገድ (1660-1674) በነገሠ በዓመቱ[53]፡

*አመ ፲ወ፪ ለታኅሣሥ ፀብዖሙ ራስ መልክዓ ክርስቶስ ለ፲ወ፪ ቤተ ጋላ ዘውእቱ ውጫላ፣ ወረጣዮ፣ ወረሚኑ፣ ወሬጉ፣ አበጢ፣ አና፣ ጉራ፣ ሱባ፣ ወሬብኮ፣ ወሬጁ፣ አርሱ፣ ኡሩካላ ዘወፅአ በአሽንን ወበጽሐ*

52. ዜና መዋዕል፣ EMML 7109, f. 65b. አፄ ፋሲል ከሰላሳ ዓመታት በላይ ግዙቶ ታሪኩን የጻፈለት የለም፣ ተጽፎለትም እንደሆነ እስካሁን አልተገኘም።

53. Guidi, *Annales Iohannis I 'Iyasu I et Bakaffa*, part I, p. 9.



*ወራሪሁ በምልዓ ቤገምድር። ወወሀቦ እግዚአብሔር ኀይለ ወመዊዓ በረድኤቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ወበጸሎቱ ለአቡነ ሳሙኤል መምህረ ትሩፋት እስከ ቀተለ ብዙኃነ በይእቲ ዕለት።*

❖

ታኅሣሥ 12 ቀን ራስ መልክዓ ክርስቶስ 12ቱን ቤተ ጋላ፣ ማለትም በአሽንን የመጣውንና ወራሪው በሞላ ቤገምድር የደረሰውን ውጫላን፥ ወረጣዮን፣ ወረሚኑን፥ ወሬጉን፥ አበጢን፥ አናን፣ ጉራን፥ ሱባን፥ ወሬብኮን፥ ወሬጁን፣ አርሱን፥ ኡሩካላን፥ ወጋቸው። እግዚአብሔርም በሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ረድኤትና በመምህረ ትሩፋት በአቡነ ሳሙኤል ጸሎት ኀይልና ድልን ሰጠው -- በዚያች ዕለት ብዙዎች እስኪገድል ድረስ።

(ታኅሣሥ 12 ቀን ቅዱስ ሚካኤልና አቡነ ሳሙኤል የሚታሰቡበት ቀን ነው።)

በነዚህ ሁሉ ውጊያዎች ኦሮሞዎች የተመቱት የጠላታቸው ጦር ድንገት ስለመጣባቸው ነው። እነሱ ዘመቻ ሲወጡ ግን የሚደነቅ የጦር ዘዴ እንዳላቸውና ሱስንዮስ ሥልጣን ለመያዝ ሲያምፅ እንደተጠቀመበት እነዚህ ከአፄ ሱስንዮስ ታሪክ የቀዳኋቸው ጥቅሶች ያሳያሉ፤

(1) *ወመከረ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ከመ ይፅብኦ ለዘሥላሴ እንዘ ሀሎ በባሕቲቱ። አጥብዓ ልቦ ወሖረ ምስለ እሊአሁ ኅዳጣን ሰብእ መስተፅዕናነ አፍራስ ወሰብአ እግር። ወጸንሖ ተኀቢኦ ውስተ ትሕት ምድር ዘወግዳ ዘትሰመይ መንታ ደፈር።*

*ወበጽሐ ዘሥላሴ በዓቢይ ትዕቢት ወበተነፍሖ ልብ እንዘ ይብል፣ መኑ ይቀውም ቅድሜየ ወመኑ ይደፍረኒ። ወንጉሥኒ ሥልጣን ሰገድ ተንሥአ እምዘነበረ ወአሠነዮ ጭፍራሁ አምሳለ ጋላ። ወሠራዊተ ዘሥላሴሰ ወኵሎሙ አምኃራ አሜሃ ኢየአምሩ ጭፍራ፤ ወኮኑ ሕውሳነ ከመ ሰብአ ምስያጥ።*

❖

(1) ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ዘሥላሴን ብቻውን ባለበት ሊወጋው ወሰነ። ልቡን አጠንክሮ ከጥቂት (ሰዎቹ)፥ ፈረሰኞችና እግረኞች፥ ጋራ ሆኖ ሄደ። መንታ ደፈር ከምትባል ረባዳ ከሆነች የወግዳ መሬት ተደብቆ ቆየው።

ዘሥላሴ በታላቅ ትዕቢትና በተነፋ ልብ፥ "ማነው በፊቴ የሚቆም፣ ማንኽ ይደፍረኛል" እያለ መጣ። ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ደግሞ ከነበረበት ተነሥቶ ጭፍራውን (የርብርቦሽ ሰልፉን) እንደ ጋላ (አሰላለፍ) አሣመረ። የዘሥላሴና የአምኃራ ሠራዊት ደግሞ በዚያን ጊዜ ጭፍራ (የርብርቦሽ) አሰላለፍ አያውቁም፣ እንደ ገበያተኛ እርምስምሶች ነበሩ[54]።

54. Pereira, *Chronica de Susenyos*, p. 79.

*(2) ወተባህሉ ኵሎሙ ቍርባን፡ እስከ ማእዜ ንነብር እንዘ ንደክም በገቢረ ዘለሳ ወበስዒረ ሰንበት። ለእመ ተቃተልነ ንሕነ ሠራዊተ ንጉሥ ያዕቆብ ይበጽሐነኑ ለ፴ ዕደው ፩ ብእሲ እምኃያላኒሁ ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ።*

*ወእምድኅረ አኀለቁ ቍርባን ምክረ ትዕቢት ወነገረ ትዝኅርት አጥብዐ ልቦ ንጉሥ ያዕቆብ ወዓርገ ለተቃትሎ ኀበ ሀሎ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ፤ እስመ ኮነ በውእቱ ጊዜ መልዕልተ ዓቀብ ውእቱኒ በመትሕቴሁ።*

*ወበጺሖ ንጉሥ ያዕቆብ ሠርዐ ሰልፈ ከመ ሥርዐተ አምኃራ ዘወትር፤ ወአንበሮሙ ለለ ፩፩ ብእሲ በጠወታ ዘውእቱ በተርታ። ወንጉሥኒ ሥልጣን ሰገድ ወረደ ንስቲተ እምዓቀብ በጭፍራ አምሳለ ጋላ። ወአኀዙ ይትቃተሉ፤ ወወገሩ ትርኰ ወናር ብዙኃ እርሳስ ውዑየ እምእፈ ነፍጥ። ወአልቦ ዘቀተሎ እንበለ ፩ ብእሲ። ወኮነ መዊእ በጊዜ ፍጡን ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ እንበለ ያንሥኡ እደ ሠራዊተ ንጉሥ ያዕቆብ።*

❖

(2) ቍርባን (የሚባሉት ሠራዊት) ሁሉም፡ "እስከ መቼ ድረስ ዘለሳ በመሥራትና ሰንበት በመሻር ስንደክም እንኖራለን? እኛ የንጉሥ ያዕቆብ ሠራዊት ብንዋጋ ከንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ኀይለኞች አንድ ሰው ለሰላሳ ሰዎች ይደርሰናልን?" ተባባሉ።

ቍርባን የትዕቢት ምክርና የትጅርት ነገር ሲጨርሱ ንጉሥ ያዕቆብ ልቡን አጠንክሮ ለጦርነት ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ወዳለበት ወጣ፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ እሱ (ሥልጣን ሰገድ) አቀበቱ ላይ፥ እሱ (ንጉሥ ያዕቆብ) ደግሞ ከበታቹ ነበረ።

ንጉሥ ያዕቆብ እንደደረሰ በወትሮው የአምኃራ ሥርዐተ ሰልፍ አሰለፈ፤ እያንዳንዱን ሰው በጠወታ፥ ማለት በተርታ፥ አቆመው። ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ደግሞ ከአቀበቱ እንደ ጋላ በጭፍራ ሆኖ ትንሽ ወረድ አለ። ይዋጉ ጀመር፤ ትርኮና ናር ከጠመንጃ አፈ ሙዝ የሚነድ ብዙ እርሳስ ተኮሱ፤ ከአንድ ሰው በቀር አልገደለም። ድል በአጭር ጊዜ ውስጥ ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ሆነ -- የንጉሥ ያዕቆብ ሠራዊት ገና እጃቸውን ሳያነሡ[55]።

## (9) ኦሮሞዎችን የማስፈር ፖሊሲ

ነገሥታቱ የችግሩ ምንጭ ኦሮሞዎች እንደ ሌላው ሕዝብ ነባር (ሰፋሪ) አለመሆናቸውን ሲረዱ ያሰፍሯቸው ጀመር። አቶ ዐፅሜ የሚሉትን እንስማ[56]፤

55. እዚያው ገ. 91።.

56. Bairu Tafla, *Asma Giyorgis and His Work*, p. 163.



አጼም (ሠርፀ ድንግል) ከብልሃትና ከማስተዋል ጋራ ጐበዝ ነበሩ፤ ... ጋላውን በእርቅ እየሳቡ በጎዣምና በደምቢያ መሬት ያልታረሰውን ውድማ እያዩ መሩት፤ ከክርስቲያን ጋራ ቀላቀሉት።

ቦረኖች ("*ጋላ ዘስሙ ቦረን*") አጼ ሱስንዮስን በልጅነቱ አባቱን ገድለው እሱንና እናቱን ማርከው ወስደው "እንደ ልጃቸው ደግ ስለሠሩለት" ለሱ ፍቅር ነበራቸው። ስለዚህ ዕርቅና ሰላም ለመደራደር እሱም ጥሩ ዕድል ነበረው። ቋንቋቸውን ይናገራል፤ ያምኑታልም። ከዚህ በታች ያሉትን ከንጉሡ ታሪክ ውስጥ አልፎ አልፎ የተቀዱትን ጥቅሶች እንመልከት፤ ፍቅራቸውንና ለማስፈር ያደረገውን ሙከራ ያሳያሉ።

*(1) ወእንዘ ሀሎ በዘከመዝ ግብረ መከራ መጽአ ጋላ ለፀቢአ ወለቃ። ወሶበ በጽሐ ኀበ ሐምቦ ዘትሰመይ ጽጃ በር ቅርብተ አባዊ ርእይዎ ለጋላ። ወጋላኒ ርእየ ከመ ሀለዉ ሰብእ፤ ወጸውዓ በዓቢይ ቃል ወይቤ መኑ ውእቱ ዝንቱ። ወአጠየቅዎ እሊአሁ ወይቤልዎ አቤተኑን ሱስንዮስ ውእቱ ወልደ አቤተሁን ፋሲለደስ ዘአንተ ተአምሮ።*

*ወሶበ አእመረ ጋላ ሮጸ ወበጽሐ ኀበ ሀሎ ወልደ ንጉሥ ውስተ ፈለግ ዘትሰመይ ሰደይ፤ ወወድቀ ታሕተ እገሪሁ ወአንገርገረ በነገረ ጋረ ፍቅር እንዘ ይጠቡ አፃብዓ እግሩ። ወተጋነየ ሎቱ ብዙኃ ተጋንዮ ወስሙ ለውእቱ ጋላ ቡኮ ዘእምነገደ ኮኖ።*

*ወእንዘ ሀሎ ምስለ ውእቱ ጋላ ሰምዓ ዜና ከመ ጥቀ የኀሥሥዎ ሠራዊተ ፀብእ የአኀዝዎ ወይሞቅሕዎ። ውእቱኒ ሖረ ምስለ ዝኩ ጋላ ኀበ ደብር ዘትሰመይ ቋዓት። ወነበረ ህየ ኅዳጠ መዋዕለ።*

❖

(1) (ሱስንዮስ ለመንገሥ ባመፀበት ጊዜ) በእንደዚህ ያለ የመከራ ሁኔታ ላይ እንዳለ፥ ጋሎች ወለቃን ለመውጋት መጡ። አባይ አጠገብ ጽጃ በር ከምትባል አምቦ (ሖራ) ሲደርሱ ጋሎቹን አዩዋቸው። ጋሎቹም ሰው እንዳለ ሲያዩ "ይሄ ማነው?" ብሎ (መሪያቸው) ከፍ ባለ ቃል ተጣራ። የራሱ ሰዎች፥ "የአቤተኑን ፋሲለደስ ልጅ አንተ የምታውቀው አቤተኑን ሱስንዮስ ነው" አሉት።

ጋላው (ይኸንን) ሲያውቅ እየሮጠ የንጉሡ ልጅ ወዳለበት ሰደይ ወደምትባል ወንዝ ደረሰና እግሮቹ ላይ ወደቀ። የእግሩን ጣቶች እየጠባ በፍቅር እንጉርጉሮ አንጎራጎረ። እጅግ ወደቀለት። የዚህ ጋላ ስም ቡኮ ነው -- ከኮኖ ነገድ።

(ሱስንዮስ) ከነዚህ ጋሎች ጋራ ሳለ (የመንግሥቱ) ጦር ሠራዊት ይዘው ለማሰር አጥብቀው እንደሚፈልጉት ወሬ ሰማ። እሱም ከነዚያ ጋሎች ጋራ ቋዓት ወደምትባል ተራራ ሄዶ እዚያ ጥቂት ጊዜ ተቀመጠ[57]።

57. Pereira, *Chronica de Susenyos*, pp. 11-12.

(2) *ወእምዝ እምድኅረ በዓለ ፋሲካ ተንሥአ እምቤተ ጋላ ወሖረ መንገለ ሸዋ ሶበ ጸንዓ ቦቱ ረኃብ። ወእንዘ የሐውር በጽሐ ኀበ ሀገር ዘትሰመይ ደብረ ድኁኃን እንተ ይእቲ መካነ ዝሁሩ ወጸዋሪተ ዓፅሙ ለአብ ክቡር አባ ታዴዎስ ወልደ አበ አበው አባ ተክለ ሃይማኖት በረከተ ክልኤሆሙ ትብጽሐነ።*

*ወበህየ ረከቦ ለጋላ ዘይሰመይ ኮኖ ወተኀዘበ ወሬዛ ማእምር ወጠቢብ ወመስሎ ዘይፀብእ። ወጋላኒ መጽአ ኀቤሁ አእሚሮ ሶበ ጠየቀ ከመ ውእቱ ወልደ ንጉሥ፤ እስመ ኮነ ውእቱ ፍቁሩ እምትካት። ወገነየ ሎቱ በከመ ይገኒ ገብር ለእግዚኡ።*

*ወእምድኅረ ኩነተዝ ነገር ሖረ ወበጽሐ ኀበ ሀገር ዘትሰመይ ብልዕት። ወአመ ዕለተ ብጽሐቱ በጽሑ ህየ ብዙኃን ነጋድያን እምዝዋይ እኒዘሙ ብዙኃ ንዋየ። ወርእዮሙ ሰብአ ሀገር እሉንተ ነጋደ መሰሎሙ ከመ መጽአ ጋላ ለፀቢአ ሀገር። ነገርዎ ለወልደ ንጉሥ እንዘ ይብሉ መጽአ ጋላ ብዙኅ።*

*ወውእቱኒ ሶበ ሰምዓ ዘንተ ተፅዕነ ላዕለ ፈረስ ወሖረ ምስለ እሊአሁ። ወበጺሖ ኀቤሆሙ አእመረ ከመ ነጋድያን እሙንቱ ወኢኮኑ ሠራዊተ ፀብእ። ወበእንተዝ ኢያሕሰመ ላዕሌሆሙ በሞት፤ ዳእሙ ነሥአ ኵሎ ዘቦሙ ወኢኀደገ ምንተኒ ወገብረ ለዘፈቀደ።*

*ወእምዝ ዓለውዎ ሰብአ መገዝ፤ ውእቱኒ አምጽአ ቦሙ ብዙኃነ ጋላ ዘይሰመዩ ቱላማ ከመ ይፅብአሙ። ወእሙንቱኒ ሰብአ መገዝ ርእዮሙ ብዝኃ ፀባኢት ፈርሁ ጥቀ፤ አምኑ ወተጋነዩ ሎቱ።*

*ለጋላኒ ዘመጽአ ለረዲኦቱ አስተፋነዎ ይሖር መንገለ ቤቱ። ወተመይጠ ጋላ እንዘ ያንጐረጕር እስመ ኢማህረከ ወኢቀተለ በከመ ሐለየ ልቡ።*

*ወውእቱኒ ወልደ ንጉሥ ተርፈ ምስለ ሰብአ ሸዋ። ወእምድኅረዝ ሖረ መንገለ ደብረ ሊባኖስ ወነበረ ኀበ አሐቲ ምድር ዘትሰመይ ዓጽቃ።*

*ወአሜሃ ኮነ ቦቱ ዓቢይ ረኃብ ወአልቦቱ ዘይሴሰይ ምንትኒ ዘእንበለ አሐቲ ጸገት። ወኮነ ይሰትዩ ሐሊበ ዚአሃ ጽባሐ ለሊሁ ወልደ ንጉሥ ወምሴተ ቃሶ።*

❖

(2) ከዚህ በኋላ ረኃብ ቢጠናበት፥ ከፋሲካ በዓል በኋላ ከቤተ ጋላ ተነሥቶ ወደ ሸዋ ሄደ። ሲሄድ ደብረ ድኁኃን ደረሰ፤ ይች (ደብር) የክቡሩ አባት፥ የአባቶች አባት፥ የአባ ተክለ ሃይማኖት (የመንፈስ) ልጅ የሆነው የአባ ታዴዎስ የመቃብሩ ቦታና የዓፅሙ ተሸካሚ ናት[58]፤ የሁለቱም በረከት ትድረሰን።

እዚያ፥ ኮኖ የሚባሉትን ጋሎች አገኛቸው፤ ዓዋቂውና ጥበበኛው ጐልማሳ (ሱስንዮስ) ተጠራጠረ፤ የሚወጋው መስሎታል። ጋሎቹ

58. ገድላቸውን ሺሮኒካ ሲክስ አጥንታ ከጀርመንኛ ትርጉሟ ጋራ አሳትማዋለች፤ Six, *Die Vita des Abuna Tadēwos von Dabra Māryām.*



ደግሞ ወልደ ንጉሥ (ሱስንዮስ) መሆኑን ተረድተው ወደሱ መጡ፤ ምክንያቱም ከጥንት ጀምሮ ወዳጆቹ ናቸው። አገልጋይ ለጌታው እንደሚገዛለት ተገዙለት።

ይህ ነገር ከሆነ በኋላ ሄዶ ብልዕት ከምትባል ሀገር ደረሰ። የደረሰ ዕለት ብዙ ነጋዴዎች ብዙ ገንዘብ (የንግድ ሸቀጥና ከብት) ይዘው ከዝዋይ እዚያ ደረሱ። የሀገሩ ሰዎች እነዚያን ነጋዴዎች ሲያዩ ጋሎች ሀገር ለመውጋት የመጡ መስሏቸው፥ "ብዙ ጋሎች መጡ" ሲሉ ለወልደ ንጉሥ (ለሱስንዮስ) ነገሩት።

እሱም ይህንን ሲሰማ በፈረስ ሆኖ ከሰዎቹ ጋራ (ወደዚያ) ሄደ። እነሱ ዘንድ ሲደርስ ነጋዴዎች እንጂ የጦር ሠራዊት እንዳይደሉ ዐወቀ። ስለዚህ በሞት አልጐዳቸውም፤ ግን ያላቸውን ሁሉ ምንም ሳያስቀር ወሰደባቸውና ለፈለገው አዋለው።

ከዚህ በኋላ የመገዝ ሰዎች ከዱት፤ እሱ ደግሞ እንዲወጓቸው ቱላማ የሚባሉ ብዙ ጋሎች አመጣባቸው። እነዚህ የመገዝ ሰዎች የጦሩን ብዛት ሲያዩ እጅግ ፈሩና አመኑ፤ ተገዙለትም።

ሊረዱት የመጡትን ጋሎች ወደቤታቸው እንዲሄዱ ሸኛቸው። ጋሎቹም በልባቸው እንዳሰቡት ስላልማረኩና ስላልገደሉ እያጕረመረሙ ተመለሱ።

ወልደ ንጉሥም ከሸዋ ሰዎች ጋራ ቈየ። ከዚያ በኋላ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄዶ በአንዲት ዓጽቃ በምትባል ሀገር ተቀመጠ። በዚያን ጊዜ ትልቅ ረኃብ ደረሰበት። ከአንዲት ጥገት በቀር ምንም አልነበረውም፤ ወተቷን (ተራ በተራ) ጠዋት ወልደ ንጉሥ፥ ማታ ቃሶ ይጠጡ ነበረ[59]።

(3) *ወእንዘ የሐውር ኀቤሆን ምስለ እሊአሁ ኮነ ፍኖቱ ፍኖተ ዓቀብ። ወበህየ ተጻደቆሙ ጊሜ ጽፉቅ ምስለ ፋፃ እስከ ኢይክሉ ይትረአዩ በበይናቲሆሙ። ወእምድኅረዝ ተዓየነ በወፌማ ወነበረ ህየ ኀዳጠ መዋዕለ።*

*ወእንዘ ሀሎ በህየ ቦኡ ሎቱ ጋላ ብዙኅ ዘኢይትኌለቍ ዘእምነገደ ከረዩ ዘውእቶሙ በላዕ ወጅሌ። ወውእቱኒ ተቀበሎሙ ምስለ እሊአሁ እንዘ ይትሬሰይ ንዋየ ፀብእ እመንገለ ትሕዝብት፤ እስመ ብእሲ ኃያል ኮነ ይትኄዘብ ኵሎ ጊዜ ወይከውን ከመ ድብ ሐራስ ወከመ አንበሳ ዘይጥህር ጊዜ የኃሥሥ መብልዐ። ከማሁ ዝንቱኒ ንጉሥ ሥልጣነ ሰገድ ኮነ ይትኄዘብ በኵሉ ጊዜ ወኢይትየዋህ እስከ ይገብር እግዚአብሔር ክቡር ወልዑል ዘፈቀደ።*

*ወእምዝ ተንሥአ እምወፌማ ወሖረ ኀበ ዱድ ወተዓየነ በህየ። ወእንዘ ሀሎ ህየ ዓዲ ቦአ ሎቱ ጋላ ዘእምነገደ ወሎ።*

❖

59. Pereira, *Chronica de Susenyos*, pp. 37-39.

(3) ከሰዎቹ ጋራ ሆኖ ወደነሱ (ወደ መንደሮቹ) ሲሄድ መንገዱ የዓቀበት መንገድ ሆነበት:: በዚያም እርስ በርሳቸው መተያየት እስኪሳናቸው ድረስ ጥቅጥቅ ያለ ጉም (ከወጨፎ?) ፉጨት ጋራ ቀደማቸው:: ከዚያ ወፊማ ላይ ሰፍሮ እዚያ ጥቂት ቀናት ተቀመጠ::

እዚያ ሳለ ቍጥር የሌላቸው ብዙ ጋሎች ከከረዩ ነገድ በላዕና ጅሌ ገቡለት:: እሱም ከሰዎቹ ጋራ ሆኖ ለጥርጣሬ የጦር ትጥቅ ታጥቆ ተቀበላቸው፤ ምክንያቱም ኃይለኛ የሆነ ሰው እንደ አራስ ድብና ምግብ ሲፈልግ እንደሚያገሳ አንበሳ ሁል ጊዜ ይጠራጠራል:: ይህ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድም እግዚአብሔር የፈቀደውን እስኪፈጽም ድረስ ሁልጊዜ ይጠራጠር ነበር::

ከዚህ በኋላ ከወፊማ ተነሥና ወደ ዱድ ሄዶ እዚያ ሰፈረ:: እዚያ እያለ ደግሞ ከነገደ ወሎ የሆኑ ጋሎች ገቡለት[60]::

(4) *ወእምድኅረ ዝንቱ ተመይጠ ወአደወ ፈለገ አቢያ ወበጽሐ ምድረ ኰሊሳ፣ ወተዓየነ በሀየ ወነበረ ሰሙነ መዋዕለ:: ወእንዘ ሀሎ በሀየ ገብአ ሎቱ ጋላ ዘየአክል መጠነ ሠላሳ::*

❖

(4) ከዚህ በኋላ ተመለሰና የአብያን ወንዝ ተሻግሮ ምድረ ኰሊሳ ደረሰ:: እዚያ ሰፍሮ አንድ ሳምንት ተቀመጠ:: እዚያ እንዳለ ሰላሳ የሚያህሉ ጋሎች ገቡለት[61]::

(5) *ወእምድኅረ ኀለፈ ክረምት ወኮነ ሀጋይ ሰምዓ ንጉሥ ከመ ከድአ ጋላ ዘውእቱ ወረንሻ፣ ወቀተሎሙ ለሰብአ ወሊቃ ወሰበረ ብዙኃነ አምባ::*

*ዝንቱ ጋላ እኩይ ውእቱ ወጕሕላዊ እምጥንቱ አምሳለ ሰይጣን፣ ኅፁዕ ውእቱ ወምኑነ ዘመድ እምኵሎሙ ነገደ ጋላ እለ ይነብሩ ውስተ ብሔረ በድው:: ቅድመ ነበረ ምስለ ወርዳያ:: ወከድአ ለወርዳያ፣ ወቀተለ ብዙኃ እምኔሁ ወኮነ ምስለ አኽቹ::*

*ለአኽቹኒ ከድአ ወገብረ ላዕሌሁ አምሳለ ወርዳያ ወሖረ ኀበ ሊበን፣ ወነበረ ምስሌሁ::*

*ለሊበንኒ ከድአ ወቀተለ እምኔሁ ብዙኃ ወቦአ ኀበ ወሎ ወነበረ ምስለ ወሎ::*

*ዓዲ ለወሎኒ ከድአ ወገብረ ዕርቀ ምስለ ሊበን::*

*ለሊበንኒ ከድአ ዳግመ ወኀደረ ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ፣ ወንጉሥኒ ወሀቦ ምድረ ዠማ ወአሞናት::*

*ወእንዘ ሀሎ በሀየ ከድአ ለንጉሥ ወቀተሎሙ ለሰብአ ወሊቃ፣ ወአምጽአ ለኢቱ ልኢኮ እምነ አደል ከመ ያጥፍእ ሀገረ ወሊቃ ወጕዣም::*

60. እዚያው ገ. 76 7::
61. እዚያው ገ. 85::



*ወሶበ ሰምዓ ንጉሥ ከመ ገብረ ዘንተ ወረንሻ አዘዘ ክተቻ፣ ወተንሥአ እምድኅና ወሖረ እንተ ፍኖተ በጌምድር:: ወወዐለ በሀየ በዓለ ልደት ወጥምቀት::*

*ወተንሥአ እምሀየ ዓደወ ፈለገ በሽሎ ወወፅአ መንገለ አምኃራ እንተ ፍኖተ እምቢስማን:: ወእምአምኃራኒ ዓደወ መንገለ ወሊቃ፣ ወእምወሊቃኒ ወፅአ መንገለ ደራ ወቤተ ማርያም::*

*ወበይእቲ ዕለት እምቅድመ ይብጽሑ ኀበ እሉ መካናት ደንገፁ ሠራዊተ ንጉሥ ወጐዩ በከንቱ እንዘ አልቦ ዘየደነግፆሙ:: ወቆመ ንጉሥ ባሕቲቱ ወተኀጥአ ሰብእ በቅድሜሁ ወበድኅሬሁ በየማኑ ወበፀጋሙ:: ወሶበ ኀጥኡ ሠራዊተ ንጉሥ ዘይዴግኖሙ ተጋብኡ ሎቱ ወተመይጡ እምጕይይ::*

*ወነሊፎ ንጉሥ እምአንቀጸ ጨረን ነበረ እስከ ይጸብሕ ሎቱ:: ወጸቢሖ ወፅአ ንጉሥ መንገለ ደራ ወሖረ ኀበ አሞናት:: ወበሀየ ረከቦ ለወረንሻ ምስለ ኵሉ ኃእዙ ወአልህምቲሁ:: ወተቀትለ ጋላ ብዙኀ በእደዊሆሙ ለሠራዊተ ንጉሥ:: ወተማህረኩ ደቅ ወአንስት ወአልህምት ዘኢይትኌለቁ::*

*ወበሳኒታ ይእቲ ዕለት ገብረ ንጉሥ ከማሁ፣ ወእምዝ ተመይጠ::*

*ወእንዘ ይትመየጥ ፈነዎ ንጉሥ ለአሐቲ አረጋይት ዘተዴወወት እምወረንሻ እንተ ይእቲ እሙ ለከረዩ ፉጦ ምስለ ንኡስ ወልዳ፣ ወለአካ ኀበ ወረንሻ እንዘ ይብል ሶበ አንትሙ ከዳእክሙ ወፀባእክሙ ሀገረ ወሊቃ ወሰበርክሙ አምባ:: አነኒ በእንተዝ መጻእኩ ለፀቢኦትክሙ:: ባሕቱ ሰረይኩ ለክሙ ዕዳክሙ:: ንዑ ግበሩ ዕርቀ ምስሌየ::*

*ወሰሚያሙ ወረንሻ መልእክተ ንጉሥ እምአፈ ይእቲ አረጊት መጽኡ መጠነ ፴ ጋላ ወገብሩ ዕርቀ ምስለ ንጉሥ::*

*ወተመይጠ ንጉሥ መንገለ አምኃራ፣ ወወዐለ በዓለ ቀበላ ጾም በቤተ አምኃራ:: ወበሀየ ሜሞ ሚመተ ትግሬ መኰንን ወባሕር ነጋሽ ለዮልዮስ:: ወለራስ ሥዕለ ክርስቶስኒ ወሀቦ ጐዣምሃ በምልኡ ከመ ራስ አትናቴዎስ::*

*ወተንሥአ ንጉሥ እምቤተ አምኃራ ወረደ በፍኖተ ደንቆሮ፣ ወበጽሐ ኀበ አኽዮ:: ወእምዝኒ ዓደወ ፈለገ በሽሎ፣ ወእምዝ ወፅአ መንገለ ስማዳ:: ወእንዘ የሐውር በጽሐ ኀበ ምድረ ቅርኛ፣ በሀየ አስተፋነዎ ለዮልዮስ ከመ ይረድ መንገለ ትግሬ:: ወንጉሥኒ አተወ ጕርኅራ ወነበረ በሀየ እስከ ወርኃ ሰኔ::*

*ወወረንሻኒ ከድአ ለኢቱ ወቀተለ ሰብአ ዚአሁ ወነሥአ አልህምቲሁ:: ወሶበኒ መጽአ ለገቢረ ዕርቅ አሰሮ ለአዛዥ ሀካኮ ዓቢይ ጋላ ወማእምረ ኵሉ ነገር:: ወአልቦ ዘከማሁ በውስተ ኵሉ ጋላ::*

*ወመሀቦ ለፊት አውራሪ ወልዶ ዘኮነ በውእቱ መዋዕል ሥዩመ ወሊቃ::*

*ወእምድኅረዝ ለአከ ወረንሻ ኀበ ራስ ሥዕለ ክርስቶስ እንዘ ይብል ተቀበለኒ:: ወዓደወ ራስ ሥዕለ ክርስቶስ መንገለ ወሊቃ ወተቀበሎ ወአዕደዎ ኀበ ምድረ ጐዣም ወከረመ በሀየ::*

*ወእምድኅረ ክረመ ወረንሻ በምድረ ጐዣም ወሀቦ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ምድረ ገንዠ:: ወሀሎ በሀየ እስከ ተጽሕፎተ ዝንቱ ታሪክ::*

❖

(5) ክረምት አልፎ በጋ ሲሆን ወረንሻ ጋላ እንደከዳና የወሊቃን ሰዎች እንደፈጃቸው፥ ብዙ አምባ እንደሰበረም ንጉሡ (ሱስንዮስ) ሰማ::

ይህ ጋላ ከጥንቱ ጀምሮ እንደሰይጣን እኩይና ብልሹ ነው:: በምድረ በዳ ከሚኖሩ ከነገደ ጋላ ሁሉ ጉደሎና ወገኑ የተጠላ ነው:: መጀመሪያ ከወርዳያ (ጎሳ) ጋራ ነበረ፤ ወርዳያን ከዳው፤ ከእሱም ብዙዎች ፈጀበትና ከአኽቹ ጋራ ሆነ::

አኽቹንም ከድቶ በወርዳያ ላይ እንዳደረገው አደረገበትና ወደሊበን ሄዶ ከሱ ጋራ ኖረ::

ሊበንንም ከድቶት ከሱ ብዙ ሰው ፈጅቶበት ለወሎ ገብቶ ከወሎ ጋራ ተቀመጠ::

ደግሞ ወሎን ከድቶት ከሊበን ጋራ ታረቀ::

ሊበንን እንደገና ከድቶት ለንጉሥ ሥልጣን ሰገድ አደረ:: ንጉሡም ምድረ ዠማን እና አሞናትን ሰጠው::

እዚያው ሆኖ (እነሆ) ንጉሡን ከድቶ የወሊቃን ሰዎች ፈጃቸው:: (በዚያ ላይ) ወለቃንና ጐጃምን እንዲያጠፋቸው ኢቱን ተላልኮ ከአደል (ከአዳል) አመጣው::

ንጉሡ ወረንሻ ይኸንን እንዳደረገ ሲሰማ ክትቻ ዐወጀና ከድኻና ተነሥቶ በቤገምድር በኩል ሄደ:: እዚያ የልደትን በዓልና ጥምቀትን አሳለፈ::

ከዚያ ተነሥቶ የበሽሎን ወንዝ ተሻገረና በእምቢስማን በኩል ወደ አምኃራ ወጣ:: አምኃራንም ወደ ወለቃ ተሻገረው:: ከወለቃ ደግሞ ወደ ደራና ወደ ቤተ ማርያም (ወደ ሀገረ ማርያም) ወጣ::

የንጉሡ ሠራዊት በዚያች ዕለት እነዚህ ቦታዎች ገና ሳይደርሱ ምንም የሚያስበረግጋቸው ሳይኖር በርግገው በከንቱ ሸሹ:: ንጉሡ ብቻውን ሆነ፤ በፊቱም በኋላውም፥ በቀኙም በግራውም ሰው ጠፋ:: የንጉሡ ሠራዊት የሚከታተላቸው ሲያጡ ተሰባስበውለት ከሽሽት ተመለሱ::

ንጉሡ ከጨረን በር አልፎ እስኪነጋለት ድረስ ቆየ:: ሲነጋ ንጉሡ ወደ ደራ ወጥቶ ወደ አሞናት ሄደ:: እዚያ ወረንሻን ከጓዙና ከከብቱ ሁሉ ጋራ አገኘው:: ብዙ ጋላ በንጉሡ ሠራዊት እጅ አለቀ፡ ቊጥር የሌላቸው ሕፃናት፥ ሴቶች፡ ከብቶች ተማረኩ::

ንጉሡ በዚያች ዕለት ማግስትም እንደዚሁ አደረገ:: ከዚያ በኋላ ተመለሰ::

ሲመለስ የክረዩ ፋጦ እናት የሆነችውን ከወረንሻ የተማረከችውን እንዲት አረጋዊት ከትንሽ ልጇ ጋራ ላከት:: እንዲህ ሲል ወደወረንሻ ላከት፥ "እናንተ ብትከዱኝና ወሊቃን ብትወጉ፥ አምባም ብትሰብሩ እኔ ደግሞ በዚህ ምክንያት ልወጋችሁ መጣሁ:: ግን እዳችሁን ይቅር ብየላችኋለሁ:: ኑ፥ ከኔ ጋራ ታረቁ::"



ወረንሻ የንጉሡን መልክት ከዚች አረጋዊት ሲሰሙ አርባ የሚሆኑ ጋሎች መጥተው ከንጉሡ ጋራ ታረቁ::

ንጉሡም በአምኃራ በኩል ተመለሰ:: የ(ሀቢይ) ጾም ቅበላን በቤተ አምኃራ አሳለፈ:: እዚያ ሆኖ ዮልዮስን የትግሬ መኰንንና የባሕር ነጋሽ ሹመት ሾመው:: ለራስ ሥዕለ ክርስቶስ ደግሞ ድፍን ጐጃምን ሰጠው -- እንደ ራስ አትናቴዎስ::

ንጉሡ ከቤተ አምኃራ ተነሥቶ በደንቆሮ መንገድ ሄዶ አኻዮ ደረሰ:: ከዚያም የበሽሎን ወንዝ ተሻገረ:: ከዚያም ወደስማዳ ወጣ:: ሲሄድ (በዚያው) ምድረ ቅርኛ ደረሰ:: ከዚያ ዮልዮስን ወደትግሬ እንዲወርድ ሸኘው:: ንጉሡም ጎርጎራ ገባ:: እዚያ እስከሰኔ ወር ድረስ ተቀመጠ::

ወረንሻም (ጎትቶ ያመጣውን) ኢቱን ከድቶት ሰዎቹን ገደለበት፤ ከብቶቹንም ወሰደበት:: አዛዥ ሀካኮን ዕርቅ ለማድረግ ሲመጣ አሰረው:: (ሀካኮ) ሁሉን ነገር ዐዋቂ ትልቅ ጋላ ነው:: እንደሱ ያለ በጋላ ውስጥ የለም:: (አስሮ) በዚያን ጊዜ የወሊቃ ሹም ለነበረው ለፊታውራሪ ወልዶ ሰጠው::

ከዚህ በኋላ ወረንሻ "ተቀበለኝ" ብሎ ወደራስ ሥዕለ ክርስቶስ ላከ:: ራስ ሥዕለ ክርስቶስ ወደወሊቃ ተሻግሮ ተቀበለው:: ወደምድረ ጎጃምም አሻገረውና ክረምቱን እዚያ አሳለፈ::

ወረንሻ በምድረ ጎጃም ከከረመ በኋላ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ምድረ ገንዠን ሰጠው:: ይህ ታሪክ እስከተጻፈበት ጊዜ ድረስ እዚያ አለ[62]::

ይህንን ሁሉ የጻፉልን አዛዥ ተክለ ሥላሴ ጢኖም እንደ አዛዥ ሀካኮ ኦሮሞ ሳይሆኑ አይቀሩም:: ኦሮሞዎችን የሳቸውን ያህል የሚያውቅ የለም::

አፄ ሱስንዮስ በአልጋው ሲደላደል በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያኑን ቅፈፍ (መሬት) እየወሰደ ብዙዎቹን አስፍሯቸው ነበር[63]:: በዚያ ላይ ኦሮሞዎቹ ከአፄ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ከመንግሥት ጋራ እንደዚያ እየተጣሉ በኢትዮጵያዊነት የመንግሥት የጦር ሠራዊት ውስጥ ተመልምለው የዝርፊያ ጥቅማቸውን በዚያ በኩልም ያገኙት ነበረ:: ይኸንን የምናውቀው ታሪክ ጸሐፊዎች አንዳንዶቹን ኦሮሞዎች በስማቸውና የነገዳቸውን ስም ጠርተው ሲያስተዋውቁን ነው:: በክርስትና

62. እዚያው ገ. 141-3::

63. *የጎጃም ታሪክ* EMML 5403, f. 65ab: "አጼ ሱስንዮስም መንግሥቱ በጸና ጊዜ አብረው የመጡትን ጋሎች በጎጃምና በዳሞት በመተከልና በባንጃ ሠራቸው (አስፈራቸው):: የተረፉትን ጋሎች ደግሞ የሚሠራበት (የሚያስፍርበት) ቢአጣ ለየአድባራቱ የገባውን ቅፈፍ (መሬት) ኢየነቀለ ጋላ ሠራበት (አሰፈረበት)::"

ስማቸው የሚጠሯቸውማ "የሰሜንና የማህል ኢትዮጵያ ሰዎች" ወይም እንደ ዶክተር መሐመድ ሐሰን አጠራር "አቢሲኒያውያን" እንጂ ኦሮሞዎች አይደሉም።

ግን ምንጮቹ እንደሚያሳዩት፥ ኦሮሞዎች በጎሳነት አንድ አካባቢ ከያዙ በኋላም ከሰብአ ትካታዊ ዘላንነት ወጥተው በያዙት አካባቢ በግብርናም ሆነ በከብት ርቢ "በግምባር ላብ" ለመኖር ጊዜ ፈጅቶባቸዋል። ባህላቸው ያልዘሩትን ማጨድ የማይከለክል፣ እንዲያውም የሚያበረታታ ይመስላል፤ መንፈሳዊ መሪያቸውን ከሩቅ አገር ድረስ እየመጡ ቡራኬ ሲጠይቁት የሚሰጣቸው ቡራኬ፥ "ውለዱ ክበዱ፣ የሥራችሁን ፍሬ ዋቃ ይባርክላችሁ" የሚል ሳይሆን ለድል አድራጊነትና ለዘረፋ የሚሆን ምረቃና መድኃኒት ነው። አንድ ጊዜማ ማህል ለማህል እየገፉ መጥተው የራሱን የወዳጃቸውን የአፄ ሱስንዮስን ከተማ ዘርፈው ቤቶቹን በእሳት አጋዩዋቸው[64]፤

*ወእንዘ ሀሎ በአይባ ፈነወ ደጅ አዝማች ሀፈ ክርስቶስ መጽሐፈ መልእክት እንዘ ይብል። ናሁ መጽኡ ፫ ቤት ጋላ ዘውእቶሙ አና ዑሩ ወአበጢ ዘበተጋብአቶሙ ይሰመዩ በስመ ፩ ነገድ ዘውእቱ መረዋ። ወምጽአተ ጋላስ ኮነ ለአጥፍኦ በጌምድር።*

*ወሶበ ሰምዓ ንጉሥ ዘንተ ነገረ ተንሥአ እምአይባ ከመ ይሖር ለተፃብአተ ጋላ መንገለ በጌምድር፥ ወተዓየነ በወይና ደጋዓ። ወበህየ ኖለቁ ንጉሥ አፍራሰ ሠራዊቱ ወኮኑ መጠነ ፲ወ፺። ወኢሀሎ መኑሂ ዘእንበለ ጸናሕያነ ዴዴ። ወራስ የማነ ክርስቶስኒ አሜሃ ሀለወ ምስሌሁ መጺአ እምነ አምኃራ። ወእምወይና ደጋዐኒ ወረደ እንተ ፍኖተ ደረጸ፥ ወዓደወ ፈለገ ርብ ወኀለፈ ካዕበ እንተ ፍኖተ ዘንግ ወተዓየነ ኀበ ምድር ዘትሰመይ ቈጠማ። ወእምህየኒ በጽሐ ምድረ ጸምአ አመ ፲ወ፰ ለወርኃ ታኅሣሥ በዕለተ ረቡዕ።*

*እምድኅረ ተዓየነ በውስተ ውእቱ ምድር ለኀዲር ጊዜ ፱ ሰዓት መጽኡ ሰብአ ዓይን ወነገርዎ ለንጉሥ ከመ ሀሎ ጋላ በቅሩብ። ወንጉሥኒ አዘዘ ከመ ያጥፍኡ እሳተ ለእመ ርእየ ጋላ ከመ ኢይገዋይ እንበለ ይግበር ፀብአ። ወተአዘዙ ኵሉ ሠራዊቱ ወአጥፍኡ እሳተ፣ ወኀደሩ በትዕቢት ወበተመክሖ።*

*ወበጽባሕ ተንሥአ ንጉሥ ወሖረ ኀበ ሀሎ ጋላ ወጊዜ ፫ ሰዐት በጽሐ ኀበ አምባ ዘሠርዖ ወልደ ሐይቶኒ። ወአምጽአ ሠርዖ መጠነ ፲ወ፩ ቸብቸቦ ዘጋላ። ወኀሊፎ ንስቲተ እምነ ውእቱ አምባ ተመይጡ ሰብአ ዓይን ዘፈነዎሙ ንጉሥ ከመ ይርአዩ ኀበ ሀሎ ጋላ ወነገርዎ ወይቤልዎ ሀሎ ጋላ በቅሩብ ኀበ ምድር ዘትሰመይ ጡቅሮ። ወባሕቱ ይፈቅድ ሐዊረ ወገቢረ ገዓሮ።*

*ወንጉሥኒ እምቅድመ ይርአይ ሀልዎተ ጋላ አዘዘ ለኵሉ ሠራዊቱ ከመ ኢይቁሙ ምስሌሁ አላ ይሑሩ ወኢይስድድዎ ለጋላ። ወሶቤሃ*

64. Pereira, *Chronica de Susenyos*, pp. 116-19.



*ፈትሐ ወራሪ ኵሉ ሠራዊተ ንጉሥ ከመ ዘይፈትሑ ወትረ ላዕለ ጎንጋ ወሻንቅላ። ወሶበ በጽሑ ተርእየ ጋላ፤ ወሀሎ ሠሪዖ ጭፍራሁ ወተደሊዎ ለፀብእ።*

*ወሀሎ ማእከለ ጋላ ወማእከለ ሠራዊተ ንጉሥ ቍልቍለት ዘኢኮነ ነዊኃ ወኢሐጺረ። በፍጻሜ ቍልቍለትኒ ሀሎ መርኅብ ሠናይ ዘይበቍዕ ለተፃብኦ ወለምርዋጸ አፍራስ። ወኀሊፎ ጋላ ዛተ መርኅበ ሀሎ ንቡረ በጭፍራ ኀበ ምድር ዘትልዕል፥ ወትመጥቅ እምነ ይእቲ መርኅብ።*

*ወሠራዊተ ንጉሥሰ እለ ይበዝኁ ኢቀርቡ ለተፃብኦ ጋላ፣ አላ ቆሙ እምርሑቅ፥ መንፈቆሙ በፍርሀት ወመንፈቆሙ በትምይንት። ወእለሰ ጠብዐት ልቦሙ ወእለ ፈርሁ ኀፍረተ ወረዱ ምስለ ራስ የማነ ክርስቶስ ወአቤተኑን ወልደ ክርስቶስ። ወንጉሥኒ ወረደ እምነ ዓቀብ መንገለ መትሕት ወአትከለ ደበና።*

*ድብ አንበሳኒ ተዘብጠ ለትእምርተ ወጢነ ፀብእ፣ ወንስርቃና ተነፍሐ። ወጋላሰ ሀሎ ፈረሰ ዘጭፍራ በባሕቲቱ ምስለ ኀዳጣን እግር፣ ወጭፍራ ዘእግር በባሕቲቱ ዘአልቦ ኍልቈ። ወአኀዙ ይትቃተሉ ዓቢየ ቀትለ። ወኮኑ ያጕይይዎ ምዕረ ጊዜ ሠራዊተ ንጉሥ ለጭፍራ ዘፈረስ። ወምዕረ ጊዜ ያጕይዮሙ ጋላ። በዘከመዝ ግብረ ተፃብኦ ወሀሉ ሰዓተ እሙረ።*

*ወሶበ ርእየ ጋላ ዘሀሎ ንቡረ በጭፍራ ከመ ብዙኃን ፈራሃን እለ ቆሙ መልዕልተ ዓቀብ ያንጎግው ድኅሬተ ወይትሐወሱ ከመ ብርዕ ይትሐወስ በኀይለ ነፋስ። ተንሥአ ጋላ በምልኡ ወኢክህሉ ሠራዊተ ንጉሥ ተቃውሞቶ። ወቀደሙ ጕይየ እለ ቆሙ በርኁቅ። ወኮነ አሜሃ መዊእ ለጋላ ወተመውአ ለንጉሥ።*

*ወተቀትሉ ብዙኃን መኳንንት በእደ ዝኩ ጋላ ዘውእቶሙ አቤተኑን ወልደ ክርስቶስ፥ ወአሰን ልሳነ ክርስቶስ፥ ወልሳነ ክርስቶስ ወልደ አፄተኑን ሣህሉ፥ እስክንድር ወልደ ተክለ ሥሉስ ዘሲሬ፥ ለባሲ ሥዮም (ሥዩም?) ዘዝፋን ቤት፥ ወንኡስ የማኖ ዘልህቀ ታሕተ እግረ ንጉሥ፥ ሼቶ እምነ አርባብ። ወመለክ ሐራ ዕንቆ፥ ወካልኣን ብዙኃን እምነ ቍርባን። ወእምነ ሰራዊተ ንጉሥ መስተፅዕናነ አፍራስ ወሰብአ እግር እለ ሞቱ በውእቱ ዕለት አልቦሙ ኍልቈ። ወዝንቱ ተመውአ ኮነ አመ ፲ወ፱ ለታኅሣሥ በዕለተ በዐሉ ለቅዱስ ገብርኤል። አልቦ ቤት ውስተ ከተማ ንጉሥ ዘኢሀሎ አሜሃ ሰቆቃው ወላህ በእንተ ብዝኀ ሞቶሙ ለሰብእ።*

*ንጉሥሰ እምድኅረ ኮነ መዊእ ለጋላ ወፅአ እንተ ፍኖተ ዳባት። ወበሳኒታሁ ኀለፈ እምዳባት ወተዓየነ መልዕልተ አሐቲ ወግር ዘትሰመይ ድባና። ወእምዝኒ ኀለፈ መንገለ ማኅደረ ማርያም ወአሰንበተ ባቲ።*

*ወበህየ መጽአ ጕዛዋም ኒጋሽ ክፍሉ ምስለ ጨዋ ዘይሰመዩ ኀይላት ወምስለ ብዙኃን ሰብአ አፍራስ ወእግር። ዓዲ እንዘ ሀሉ ውስተ ይእቲ*

*ማኅደረ ማርያም ፈነወ ንጉሥ ኀበ ዮልዮስ መጽሐፈ መልእክት እንዘ ውእቱ ሀሎ አሜሃ በምድረ ጉማን። ወነገረ መልእክቱሰ ለንጉሥ ይነግር ኩነተ መዊእ ወተመውኦ ወይኤዝዝ ከመ ይብጻሕ ፍጡነ ለረዲኦቱ።*

*ወእምድኅረ ፈነወ ዘንተ መልእክተ ተንሥአ ንጉሥ እማኅደረ ማርያም ወሖረ ጉዕዞ ውኀደረ ኀበ ምድር ዘትሰመይ ኾድ ገበያ። ወእምዝኒ ኀለፈ መንገለ ቃሮዳ። ወእምቃሮዳኒ ተንሢኦ ተዓየነ ማእከለ ቆጋ ወአምባ ማርያም ኀበ ምድር ዘትሰመይ ማሸሉት። ወበሀየ ወዐለ በዐለ ልደት ዘለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘክሮቱ ሰጊድ።*

*እምድኅረ በዐለ ልደት ወፅአ ንጉሥ በፍኖተ ወይና ደጋዓ መንገለ ደንቀዝ። ወኮነ ይጸንሕ በሀየ ተጋብኦተ ሰብእ እምዝርወት ወምጽአተ ሠራዊት እምርኁቅ ወቅሩብ ከመ ይፃባእ ዳግመ ምስለ ጋላ። ወጋላሰ ወረደ አሜሃ እምውቅሮ መንገለ ሐሙስ ወንዝ፡ ወእምዝኒ መጺኦ በጭፍራ አጥፍኦ ወአማሰነ ኵሎ አህጉራተ እንፍራዝ ወማህረከ እስከ ጎረባ ወእስከ ጭኸራ። ወአውዓየ መዲና ንጉሥ ዘቆጋ ወተመይጠ መንገለ ሐሙስ ወንዝ።*

❖

(ሱስንዮስ) በአይባ በነበረበት ጊዜ ደጅ አዝማች ሀፈ ክርስቶስ (ወደ ንጉሡ) እንዲህ ሲል የመልእክት ደብዳቤ ላከ፤ "እነሆ ሶስቱ ቤተ ጋላ፥ እነሱም ሲሰባሰቡ መረዋ በሚል አንድ ነገድ የሚጠሩ፥ እነ አና፥ ሁሩ፥ አበጢ መጡ። የጋሎች አመጣጥ በጌምድርን ለማጥፋት ነው።"

ንጉሡ ይኸንን ነገር ሲሰማ ጋሎችን ለመዋጋት ወደ በጌምድር ሊሄድ ከአይባ ተነሣና ወይና ደጋዓ ላይ ሰፈረ። ንጉሡ እዚያ የሠራዊቱን ፈረሶች ቈጠረ፤ አንድ መቶ አርባ ነበሩ። ከግቢው ጠባቆች በቀር (የቀረ) ሌላ ማንም አልነበረም። ራስ የማነ ክርስቶስም ያን ጊዜ ከአምኃራ መጥቶ አብሮት ነበረ። ከወይና ደጋዐ ወደ ደሪጻ መንገድ ወረደ። የርብ ወንዝን ተሻግሮ ደግሞ በዘንግ መንገድ አልፎ ቈጠማ ከምትባል ቦታ ሰፈረ። ከዚያ በታኅሣሥ ፲፰ቀን ረቡዕ ዕለት ጾምአ ደረሰ።

ለማደር እዚያ በዘጠኝ ሰዓት እንደሰፈረ ሰላዮች መጥተው ጋሎች በቅርብ እንዳሉ ለንጉሡ ነገሩት። ንጉሡም ጋላ እሳት ሲያይ ሳይዋጓ እንዳይሸሽ እሳት እንዲያጠፉ አዘዘ። ሠራዊቱ ሁሉ ታዘው እሳት አጠፉና በትዕቢትና በትምክሕት አደሩ።

ጠዋት ንጉሡ ተነሥቶ ጋሎች ወዳሉበት ሄደ። በሶስት ሰዓት ከሐይቶኝ ልጅ ከሠርያ አምባ ደረሰ። ሠርያ ዓሥራ አንድ ያህል የጋላ ቾብቾቦ አመጣ። ከዚህ አምባ ጥቂት አለፍ እንዳለ ንጉሡ ጋላ ያለበትን እንዲያዩ የላካቸው ሰላዮች ተመልሰው መጡ። "ጋሎች በቅርብ ውቅሮ በምትባል ቦታ አሉ፤ ግን ዓባ እንሥተው ለመሄድ ይፈልጋሉ" ብለው ነገሩት።



ንጉሡም የጋሎችን ሁኔታ ሳያይ ሠራዊቱን እንዳይለቋቸው (ወደነሱ) እንዲሄዱ፥ አብረውት እንዳይቆሙ አዘዛቸው። በዚያን ጊዜ የንጉሡ ሠራዊት በሞላ ዘወትር በጎንጋ እና በሻንቅላ ላይ ወራሪ እንደሚፈቱ ፈቱ፤ ሲደርሱ ጋሎቹ ታዩ። በጭፍራ ሰልፋቸው ሆነው ለጦርነት ተዘጋጅተዋል። በጋሎችና በንጉሡ ሠራዊት መካከል ረጅም ወይም አጭር የማይባል ቊልቊለት አለ። ከቊልቊለቱ ማለቂያ ላይ ለጦርነትና ለፈረስ ሩጫ የሚስማማ ጥሩ ሜዳ አለ።

ጋሎቹ ያችን ሜዳ አልፈው፥ ከሜዳዋ ከፍ ከምትልና ወደላይ ከምትሆን መሬት በጭፍራ (ሰልፍ) አሉ። የንጉሡ ሠራዊት ደግሞ ግማሾቹ በፍርሃት ግማሾቹም በንቀት አብዛኞቹ በሩቁ ቆሙ እንጂ ጋሎቹን ለመውጋት አልቀረቡም። ልባቸው የጨከነና እፍረትን የፈሩ (ሊዋጉ) ከራስ የማነ ክርስቶስና ከአቤተጉን ወልደ ክርስቶስ ጋራ ወረዱ።

ንጉሡም ከአቀበቱ ወደታች ወርዶ ድንኳን አስተከለ። ጦርነት ለመጀመር ድብ አንበሳ (ከበሮ) ተመታ፤ ንስር ቃናም (እምቢልታ) ተነፋ።

ጋሎች ደግሞ የጭፍራ ፈረሰኛ ከጥቂት እግረኞች ጋራ ለብቻው፥ ቊጥር የሌለው የእግር ጭፍራ ለብቻው ሆኖ ትልቅ ተጋድሎ ተጋደሉ። አንድ ጊዜ ፈረሰኛውን ጭፍራ የንጉሡ ሠራዊት ያባርሯቸዋል፤ አንድ ጊዜ ጋሎቹ ያባርሯቸዋል። በዚህ ዓይነት ጦርነት ለታወቀ ሰዓት (ለተወሰነ ጊዜ) ዋሉ።

በጭፍራ ያሉት ጋሎች ከአቀበቱ ላይ ያሉትን ብዙዎቹን ፈሪዎች ወደኋላ ሲያፈገፍጉና በነፋስ ኃይል እንደሚወዛወዝ መቃ ሲርመሰመሱ ሲያዩዋቸው ጋሎቹ በሞላ ተነሡ። የንጉሡ ሠራዊት ሊቋቋማቸው አልቻለም፤ ከሩቅ የቆሙት ቀድመው ሸሹ። በዚያን ጊዜ ድል የጋሎች፥ ሽንፈት የንጉሡ ሆነ።

በእነዚሁ ጋሎች እጅ ብዙ መኳንንት ተገደሉ። እነሱም እኒህ ናቸው፤ አቤተጉን ወልደ ክርስቶስ፥ አስጓ (የሹመት ስም ነው) ልሳነ ክርስቶስ፥ የአቤተጉን ሣህሉ ልጅ ልሳነ ክርስቶስ፥ የሺሬው ተክለ ሥሉስ ልጅ እስክንድር፥ አምባራስ (ባላምባራስ) ፍቅሮ፥ የወገራ ሹም ዘኢየሱስ፥ የዝፋን ቤቱ ሹም ለባሲ፥ በንጉሡ እግር ስር ያደገው ትንሹ የማኖ፥ ከአርባብ (የሠራዊት ስም ነው) ሼቶ፥ መለክ ሐራ (ሹመት ነው) ዕንቆ፥ ከቊርባንም ሌሎችም ብዙዎች። ከንጉሡ ሠራዊት ፈረሰኞችና እግረኞች በዚህ ዕለት የሞቱ ቊጥር የላቸውም።

ይህ ሽንፈት የሆነው በታኅሣሥ 19 ቀን በቅዱስ ገብርኤል ዕለተ በዐል ነው። በዚያን ጊዜ ከሞተው ሰው ብዛት የተነሣ በንጉሡ ሰፈር ሐዘን የሌለበት ቤት አልነበረም።

ንጉሡም ድል የጋሎች ከሆነ በኋላ ወደ ዳባት መንገድ ሄደ። በማግስቱ ከዳባት አልፎ ድባና ከምትባል ኮረብታ ላይ ሰፈረ። ከዚያም ወደ ማኅደረ ማርያም አለፈና ሰንበትን በዚያ ዋለ።

ጐዣም ነጋሽ ክፍሎ ኃይላት ከሚባሉት ወታደሮች፥ ከብዙ ፈረሰኞች እና እግረኞች ጋራ ሆኖ እዚያ መጣ። ንጉሡ ደግሞ እዚች ማኅደረ ማርያም እያለ ለዩልዮስ -- በዚያን ጊዜ በምድረ ጉማን ሳለ -- የመልእክት ደብዳቤ ላከ። የንጉሡ የመልክቱ ይዞታ የማሸነፍንና የመሸነፍን ሁኔታ ይናገርና እንዲረዳው ቶሎ እንዲደርስ ያዛል።

ንጉሡ ይኸንን መልእክት ከላከ በኋላ ከማኅደረ ማርያም ተነሥቶ የጉዞ መንገድ ሄደና ኾድ ገበያ ከምትባል ምድር አደረ። ከዚያም ወደቃሮዳ አለፈ። ከቃሮዳ ተነሥቶ በቆጋ እና በአምባ ማርያም ማህል ማሽሉት ከምትባል ምድር ሰፈረ። እዚያ (ስሙን) ሲያነሡት ስግደት የሚገባውን የጌታችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል አከበረ።

ንጉሡ ከልደት በዐል በኋላ በወይና ደግዓ መንገድ ወደ ደንቀዝ ወጣ። ከጋሎች ጋራ እንደገና ለመዋጋት (አስቦ) የሰዎቹን ከተበተኑበት መሰባሰብና የሠራዊቱን ከሩቅና ከቅርብ መምጣት ይጠብቅ ነበረ።

ጋሎች ደግሞ በዚያን ጊዜ ከዚያ ከውቅሮ ወደ ሐሙስ ወንዝ ወረዱ። ከዚያ በጭፍራ መጥተው የእንፍራዝን አገሮች ሁሉንም አጠፏቸው፥ አበላሿቸው። እስከ ጎረባ እና እስከ ጭኾራ ድረስ ማረኩ። የንጉሡንም የቆጋውን መዲና አቃጠሉትና ወደ ሐሙስ ወንዝ ተመለሱ።

ጸሐፊው አልነገረንም እንጂ የነዚህ መኳንንትና የብዙው ሕዝብ ቸብቸቦ በኦሮሞዎቹ ሰፈር ቦታ ጠቦት ይሆናል።

አፄ ሱስንዮስ አፄ ሠርፀ ድንግል ለእናርያ ሰዎች እንዳደረገው፥ ኦሮሞዎችን ክርስትና አስነሥቶ ከክርስቲያኑ ሕዝብ ጋራ አንድ ሊያደርጋቸው ሞክሯል። በሱ ምክርና ትእዛዝ ወረኛዎች በሞላ "የአባቶቻቸውን የጋላ ልማድ" ትተው እንደ ተጠመቁ አዛዥ ጢኖ እንዲህ ሲሉ ከሌላ ቦታ ነግረውናል[65]፤

*መበውእቱ ወርኃ ክረምት አዘዞሙ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ከመ እግዚእ አዛዚ ወሐዋርያ ሰባኪ ወተናገሮሙ ለጋላ ዘውእቶሙ ወረኛ በአሰፍዎ ሀብት ሰማያዊ ወምድራዊ። ወይቤሎሙ እመኑ በክርስቶስ ወተጠመቁ በስሙ ከመ ትኩኑ ዕሩያን ምስሌነ በክብር አመ ትንሣኤ ሙታን ወኅድጉ ልማደ አበዊክሙ ጋላ*

65. እዚያው ገ. 214-5። ጥቅሱ እንደሚያመለክተው ያልተገዘረ አባት የሚወልደው ልጅ እንደ ጉድ ይታይ ነበር። ባህሉ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ይከበር እንደነበረ ብዙዎች የኦሮሞ ባህል ተመራማሪዎች መዝግበውታል። ናይጄሪያ ውስጥ መንታዎች ሲወለዱ ይጥሏቸው እንደነበረ ማለት ነው። ኦሮሞዎች የሚገዘሩት በእድሜ ከገፉ በኋላ ስለሆነ ጎልማሶቹን ገሳጭ "ጎርሳዎች" ባይኖርባቸው እስኪገዘሩ ድረስ የማይፈለግ ብዙ ልጅ ይወለድ ነበር።



*ዘኢይሰነአው ምስለ አሚን በክርስቶስ እግዚአ ሕያዋን ወሙታን። ወይቤሉ ወረኛ አሆ ለይኩን በከመ አዘዝከነ እግዚእነ ንጉሥ።*

*እስመ ልማዶሙ ለጋላ ኮኑ ይሰምይዎ ለሰማይ እግዚአብሔርሃ አምላኮሙ ወውእቱ ፈጣሪሆሙ ዘፈቀደ ይቀትል ወዘፈቀደ የሐዩ። ወኵሎ ሥልጣናተ ወዕዘዘ ይሁብዎ ሎቱ።*

*ዓዲ ይትአመንዎ ለ፩ ብእሲ እምኔሆሙ ዘስሙ አባ ሙዳ በከመ ይትአምንዎ አይሁድ ለሙሴ ወተንበላት ለመሐመድ ወየሐውሩ ኀቤሁ እምርሑቅ ሀገር ወይትባረኩ እምኔሁ በበረከተ መዊእ ወበበረከተ ሰላም። ወይተፍእ ሎሙ ምራቆ በከርቤ። እሙንቱኒ ቈጺሮሙ ይጸውርዎ በከርቤ ከመ ይኩኖሙ ተስፋ ለዕለተ ፀብእ ምስለ ኵሉ ዘይፃብእዎ።*

*ዓዲ ኵሉ ጋላ በበ ነገዶሙ ፯ አንጋድ እሙንቱ፤ ወይሠየሙ በበ ዕብሬቶሙ በበ ፰ ዓመት። ወእለ ተሠይሙ ወእለ ኮነት ዕብሬቶሙ ይሰመዩ ሉባ። እስከ ይበጽሐሙ ዝንቱ ሢመት ዘውእቱ ሉብነት ኢይትገዘሩ ነፍስቶሙ። ወለእመኒ ወለዱ ተባዕተ አው አንስተ ኢያልሀቅዎሙ ከመ ሥርዓተ ወላድያን አላ ይገድፍዎሙ አፍአ ...።*

*ዓዲ ለእመ ኢቀተሉ ሰብአ በመዋዕለ ሢመቶሙ ኢይትላጸዩ ሥዕርተ ርእሶሙ፤ ወኢያወፅኡ ጕተ ለትእምርተ ቀቲሎቶሙ ሰብአ አላ ይነብሩ ትኩዛኒሆሙ እንዘ ይበክዩ ወትረ ከመ ዘተፈትሐ ቦቱ ፍትሐ ሞቱ።*

*ወዘንተ ኵሎ ልማዳተ ጋላ ... አኅደጎሙ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ። ወአዘዘ ያጥምቅዎሙ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ወተጠምቁ ኵሉ ወረኛ ወተመጠዉ ምሥጢረ ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ወኮኑ አሐደ መርዔተ ለአሐዱ ኖላዊ ምስለ ኵሎሙ ክርስቲያን። ወረኛሰ ፩ ነገድ እሙንቱ እምነ ፯ አንጋደ በርቱማ።*

❖

በነዚያ የክረምት ወራት ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ወረኛ የሚባሉትን ጋሎች እንደ ገገር ጌታና እንደ ሰባኪ ሐዋርያ አዘዛቸው። ሰማያዊና ምድራዊ ሀብት በሚሰጥ ተስፋ አነጋገራቸው። (እንዲህም) አላቸው፤ "ሙታን በሚነሡበት ጊዜ በክብር ከኛ ጋራ እኩል እንድትሆኑ በክርስቶስ እመኑና በስሙ ተጠመቁ። የሕያዋንና የሙታን ጌታ ከሆነው ከክርስቶስ እምነት ጋራ የማይስማማውን የአባቶቻችሁን የጋላ ልማድ ተዉ።" ወረኛዎች "እሺ፡ ንጉሥ ጌታችን እንዳዘዝከን ይሁን" አሉ።

(ይህ የሆነበት) ምክንያት፥ ጋሎች ሰማይን አምላካቸውና ፈጣሪያቸው፥ የፈለገውን የሚገድል፥ የፈለገውን የሚያኖር እግዚአብሔር ይሉታል፤ ሥልጣኖችንና ገዥነትን ይሰጡታል።

ደግሞ፥ ከማህላቸው አባ ሙዳ የሚሉትን አንዱን ወንድ አይሁድ ሙሴን፥ እስላሞች መሐመድን እንደሚተማመኑበት ይተማመኑበታል። ከሩቅ አገር ድረስ ወደእሱ እየሄዱ በእሱ የማሸነፊያ ቡራኬና የመዝረፊያ ቡራኬ ይባረካሉ። ምራቁን በድኝ ላይ ይተፋላቸዋል፤ እነሱም ከሚወጉት ዘንድ ሁሉ የውጊያ ዕለት ተስፋ እንዲሆናቸው (ምራቁን) በድኝ ቋጥረው ይይዙታል።

ደግሞ ጋሎች ሁሉ በየነገዳቸው ሁነው አምስት መደቦች ናቸው። (አምስቱ መደቦች) በየተራቸው በየስምንት ዓመት ይሾማሉ። የተሾሙት ባለተራዎቹ ሉባ ይባላሉ። ይኸ ሹመት፥ ማለት ሉብነት፥ እስኪደርሳቸው ድረስ እስኪታቸውን አይገዘሩም፤ ወንድም ሆነ ሴት (ልጅ) ሲወልዱ (ልጆቹን) ... አደጅ ይጥሏቸዋል እንጂ እንደወላጆች ሥርዓት አያሳድጓቸውም።

ደግሞ በሹመታቸው ዘመን ሰው ካልገደሉ፤ የራሳቸውን ጠጉር አይላጩም። የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት (ሰው) ዘወትር እያለቀሱ በሐዘን ላይ ይኖራሉ እንጂ፥ ሰው ለመግደላቸውም ምልክት (የሚሆነውን) ቁንጮ አያወጡም።

... እነዚህን የጋላ ልማዶች ሁሉ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ አስተዋቸው። በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቋቸው አዘዘ። ወረነሻዎች ሁሉም ተጠመቁ። የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የሥጋውንና የደሙን ምስጢር ተቀበሉ (ቈረቡ)። ከክርስቲያኖቹ ሁሉ ጋራ ያንድ እረኛ አንድ መንጋ ሆኑ። ወረነሻዎች ከሰባቱ የበርቱማ ነገዶች አንዱ ነገድ ናቸው።

ከ1713 እስከ 1723 ዓ. ም. ከገዛው ከአፄ በካፋ ታሪክ የተወሰደውን ስለማስፈር የሚናገረውን እንመልከት፤[66]

*ወአመ ሖረ አቡሁ ኢያሱ ምድረ ጊቤ ወእናርያ አትለዎ ድኅሬሁ እንዘ ያለብሶ ግስላ ወያጸውሮ ረምኅ። ወኢሐወጸ ፍርሃት እንዘ ወልደ ፲ዓመት...።*

*ስምዑኬ አዓቃብያነ መንግሥት ዘእነግረክሙ አነ ጸሐፌ ዝንቱ ታሪክ፤ እስመ ኮንኩ እተልዎ ለንጉሥ አቡሁ በምድረ ጊቤ። ወአመ ግዕዘ ንጉሥ እምነ ብሔር እንተ ትሰመይ ቱሉ ቁባ ሉባ ረከበኒ ፩ጋላ ወተዛውዓኒ ብዙኀ ነገረ፤ ወይቤለኒ አርእየኒ እስኩ*

66. Guidi, *Annales Iohannis I 'Iyasu I et Bakaffa*, part II, p. 272-3.



*ወልደ ንጉሥ ዘይሰመይ በካፋ። ወአርአይክዎ። ወካዕበ በሣልስት ዕለት ረከበኒ ዝኩ ጋላ ወይቤለኒ፥ አእምር አንተ ብእሲ ናሁ ዝንቱ ሕፃን ዘስሙ በካፋ ይነግሥ ዕኑዓ መንግሥተ፤ ወይቀንዮሙ ለሜጫ ወለቱለማ ኅቡረ። ወእቤሎ በምንት ተአምር እንዘ አረማዊ አንተ። ወይቤለኒ በትእምርተ አቡየ አአምር።*

❖

አባቱ ኢያሱ (1674-98) ወደ ጊቤ እና ወደ እናርያ የሄደ ጊዜ (በካፋን) የግስላ (ለምድ) አልብሶት ጦር አሲዞት ከኋላው አስከትሎት ነበረ። የዓሥር ዓመት ልጅ ሆኖ ሳለ ፍርሃት አልጐበኘውም...።

የመንግሥት ጠባቂዎች (ባለሥልጣኖች) ሆይ፥ እኔ የዚህ ታሪክ ጸሐፊ (ሲኖዳ) የምነግራችሁን ስሙ፤ ምክንያቱም አባቱን ንጉሡን በምድረ ጊቤ ተከትየው ነበር። ንጉሡ ቱሉ ቁባ ሉባ በምትባል ሀገር ሲጓዝ አንድ ጋላ አግኝቶኝ ብዙ ነገር አጫወተኝ። "እስቲ በካፋ የሚባለውን የንጉሡን ልጅ አሳየኝ" አለኝ፤ አሳየሁት። ይኸው ጋላ እንደገና በሶስተኛው ቀን አገኘኝና፥ "አንተ ሰው፥ ዕወቅ፤ እነሆ ይኸ ስሙ በካፋ የሆነ ሕፃን በተደላደለ መንግሥት ላይ ይነግሣል፤ ሜጫንና ቱለማንም አስተባብሮ ይገዛቸዋል" አለኝ። "አንተ አረመኔ ሆነህ ሳለ እንዴት ታውቃለህ?" አልኩት። "ካባቴ (በተማርኩት) ምልክት አውቃለሁ" አለኝ።

አባቱ ቀዳማዊ ኢያሱ (አድያም ሰገድ) ከጎንደር ተነሥቶ ጊቤ ድረስ የሄደው ኦሮሞዎቹን ለማስፈርና ሰላም ለመፍጠር ነበረ፤ ግን የሆነውን አሁንም ከዚሁ ንጉሥ ከአፄ በካፋ (1713-1723) ታሪክ ወስደን እንመልከት፤

(1) *እምይእዜሰ እነግረክሙ ብዝኀ መዓቱ ለዝንቱ ንጉሥ በካፋ፡ መፍርህ ወመደንግጽ፡ ወብዝኀ ምሕረቱ ዘኮነ ኅዕለ ጃዊ እስመ በጥቃ መዓቱ ሀሎ ብዝኀ ምሕረቱ።*

*ወአመ ኮነ ዓመተ መንግሥቱ ፩ዓመተ ወ፫ዓውራኀ መጽአ ቦቱ ዜና ለንጉሥ ከመ አጽረረ ጠሊታ ጃዊ ዘአምጽአ አቡሁ እምድረ ጊቤ ወአንበሮ በጽንፈ ዓባዊ።*
*አሜሃ አዘዘ ለቢትወደድ ኤራቅሊስ ከመ ይዕቀብ ትዕይንተ እስመ ሀየ ሀሎ አክሊለ መንግሥቱ፡ ወለበጅሮንድ ማሞ አማዕቀቦ ኵሉ ንዋየ ቤቱ እስመ ምዕመን ውእቱ ወተወከፈ ስደተ በእንቲአሁ ...።*

*ወፈነወ ሎቱ ለደጃዝማች ማሞ ዘዳሞት መጠነ ፶ንፍጥ፥ ወአዘዘ ንጉሥ በቃለ ዓዋዲ ከመ ይትልዎ ኵሉ ሠራዊት እመኒ ዘመድ ወዘመደ ዘመድ።*

*ወአመ ፲ወ፭ለጥር በዕለተ ሐሙስ በዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ ተንሥአ ንጉሥ በካፋ እምነ ጐንደር ወኃደረ በወይና ዓረብ ...።*

*ወነበረ ንጉሥ በአሪንጎ ፲ወ፮ዕለተ። ወፈነወ ላእከ ኀቤሁ ደጅ አዝማች ማሞ ዘዳሞት ከመ ፀብዖ ወአሕለቆ ለጠለታ ጃዊ ...።*

❖

(1) አሁን ግን በዚህ በጃዊ ላይ የተፈጸመውን የዚህን አስፈሪና አስደንጋጭ ንጉሥ የበካፋን የቁጣውን ብዛት እነግራችኋለሁ፤ ምክንያቱም በቁጣው አጠገብ የምሕረቱ ብዛት አለና።

አባቱ ከምድረ ጊቤ አምጥቶ በዓባይ ዳር ያስፈረው ጃዊ ጠለታ በጠላትነት እንደተነሣ በመንግሥቱ ዘመን በ፩ ዓመት ከ፰ ወር ዜና ደረሰው።

በዚያን ጊዜ ቢትወደድ ኤራቅሊስን ከተማ እንዲጠብቅ አዘዘው፤ ምክንያቱም የመንግሥቱ ዘውድ እዚያ ነው። በጅሮንድ ማሞን የቤቱን ንብረት በሞላ አስጠበቀው። ምክንያቱም (በጅሮንድ ማሞ) ታማኝ ነው፤ ለሱ ሲልም ስደት ደርሶበታል።

ለዳሞቱ ደጃዝማች ማሞ አምሳ ያህል ነፍጥ ላከለት። ሠራዊቱ ሁሉ ዘመድም ሆነ የዘመድ ዘመድም እንዲከተለው ንጉሡ በዐዋጅ ትእዛዝ ሰጠ።

ጥር 15 ቀን ሐሙስ ዕለት በወንጌላዊው ሉቃስ ዘመን ንጉሥ በካፋ (ለዘመቻ) ጐንደርን ለቅቆ ወይና ዓረብ አደረ።

ንጉሡ አሪንጎ ላይ ዓሥራ ስድስት ቀን ተቀመጠ። (እዚያ ሳለ) የዳሞቱ ደጃዝማች ማሞ ጃዊ ጠለታን እንደወጋውና እንደፈጀው ወደሱ መላክተኛ ላከ[67]።

(2) *ወበቀዳሚት ሰንበት በጽሐ ዋንካ። ወሀየ መጽኡ ኅዳጣን እምነ ጃዊ እለ ይብልዎሙ ቍዕር፤ ወይቤልዎ ለንጉሥ በቃለ ጃዊ፥ መሐረነ አንጉሥ እስመ ንሕነ አግብርቲከ ወአግብርተ አቡከ። እመኒ አበስነ እግዚእ እስመ ለነ አበሳ ወለከ ምሕረት።*

*ወይቤሎሙ ንጉሥ ሑሩኬ መሐርኩክሙ። ባሕቱ አምጽእዎሙ ለሮጌ ወለነፌ እምዬ። እመሰ ኢያምጻእክሙ ትበልዑ ኵስሐክሙ ወትሰትዩ ስንተክሙ። ወኢያመስጠኒ ዕእስከ*

67. እዚያው ገ. 275 6።



*ዘያስተዓዝብ ዲበ አረፍት፤ ወእሁብ ሥጋክሙ ለአዕዋፈ ሰማይ ለእመ ኢመጻእክሙ እስከ ዕለተ ረቡዕ ሀበ ሀሎኩ አነ።*

❖

(2) ቅዳሜ ዋንካ ደረሰ። እዚያ (እያለ) ከጃዊ ውስጥ ቍዕር የሚሏቸው ጥቂቶች መጡና ለንጉሡ በጃዊ ቋንቋ (በጃዊኛ እንዲህ) አሉት፥ "ንጉሥ ሆይ፥ ማረን፤ ምክንያቱም እኛ አሽከሮችህ የአባትህም አሽከሮች ነን። ጌታ ሆይ፥ ብናጠፋ ጥፋት የኛ፥ ምሕረት ያንተ ነው።"

ንጉሡ (እንዲህ) አላቸው፥ "በሉ ሂዱ ምሬያችኋለሁ። ግን ሮጌን እና ነጮን ከእምዬ አምጧቸው። ካላመጣችሁ ኩሳችሁን ትበላላችሁ፥ ሽንታችሁን ትጠጣላችሁ። እዚህ አለሁበት ድረስ እስከ ረቡዕ ዕለት ድረስ ያልመጣችሁ እንደሆነ ግድግዳ ተጠግቶ የሚሸና (ወንድ) ሁሉ አያመልጠኝም። ሥጋውን ለሰማይ ወፎች እሰጠዋለሁ[68]።

## (10) በአንድ ሀገር ሶስት መንግሥት

*ኦሮሞዎች በኢትዮጵያ ታሪክ እስኪታወቁ ድረስ በኢትዮጵያ ላይ ሁለት መንግሥት ተቋቁሞ ነበረ--አንዱ የሐዜጌ ሌላው የእጨጌ። ይኸ ታሪክ በይፋ የተቋቋመው ይኩኖ አምላክና ካህናቱ ተባብረው የዛጔዎችን መንግሥት በገለበጡ ጊዜ በ1263 ዓ. ም. ነው ቢባልም፥ ክርስትና ኢትዮጵያ ውስጥ ስር ከሰደደበት ጊዜ ጀምሮ የሐዜጌው ቤተ መንግሥትና የእጨጌው የሆነው ቤተ ክህነት እንደ ሥጋና እንደ ነፍስ አንድ አካል አንድ አምሳል ሁነው ይገዙ ነበር። በሁለቱ መንግሥታት መካከል ኅብረት እንጂ አልፎ አልፎ ካልሆነ የጎላ ግጭት አለመኖሩ ለሕዝቡ ትልቅ እፎይታ ነበር።*

ኦሮሞዎች ሲመጡ ባሉት ሁለቱ (የተባበሩት) መንግሥቶች ላይ "ሕዝባዊ የሉባጌ" መንግሥት አቋቋሙ።

እንደሚመስለው፥ ኦሮሞዎች ያሰቡት እንደጻጻሱ ከሥነ ልቡናዊ የማያልፍ ሥልጣን ባለው አባ ሙዳ እና በሉባ ትውልድ አዝማች ስር ሆነው እያንዳንዱ ጎሳ በያዘው መሬት ላይ በዘላንነት (ወደኋላ ላይ በግብርናም) በራሱ ንዑስ መሪ የራሱን አስተዳደር ዘርግቶ ለመኖር ነበረ። ታሪክ ጸሐፊዎቹም ይኸንን ዐውቀውና ተቀብለው፥ የታሪክ ድርጊቶችን ዘመን ሲያመለክቱ በዚያን ጊዜ በሚገዛው አፄ ዘመን እንደሚቈጥሩ

68. እዚያው ገ. 278 9።

በኦሮሞዎቹ ሉባ ዘመንም ይቈጥሩ ነበረ። ለምሳሌ ከጸሐፊዎቹ አንዱ ስለ ግራኝ ፀመፅ አጀማመር መጻፍ ሲጀምር እንዲህ ይላል[69]፤

*እምአመ ሢመቱ ላሜልባሕ በ፱ ዓመት ተፃብኡ ሐፄ ወናግ ሰገድ ምስለ ግራኝ በሽምብራ ኩሬ።*

❖

በሜልባሕ በ9ነኛው የሹመት (ዘመን) አፄ ወናግ ሰገድ ከግራኝ ጋራ ሽምብራ ኩሬ ላይ ተዋጉ።

ስለአፄ ሠርፀ ድንግል የተጻፈ አንድ የዜና መዋዕል ቅጂ እንዲህ ይላል[70]፤

*ወበ፻ወ፪ አመት ወረደ እናርያ። ወሞተ ኩስትሮ። ወረሰዮሙ ንጉሥ ለሰብአ እናርያ ክርስቲያነ።*

*ወበ፻ወ፫ አመት ወጽአ ቤገምድር ለተፃብዖተ ጋላ በዘመነ ሢመቱ ለፊዳታ ዘሰመይዎ ቡራቃ።*

❖

(ሠርፀ ድንግል በነገሠ) በ፻ወ፪ ዓመት ወደ እናርያ ወረደ። ኩስትሮ ሞተ። ንጉሡ የእናርያን ሰዎች ክርስቲያን አደረጋቸው።

በ፻ወ፫ ዓመት፥ ቡራቃ በሚሉት በፊዳታ የሹመት ዘመን፥ ጋላን ለመውጋት ወደ ቤገምድር ወጣ።

ብዙ ርቀን ሳንሄድ ራሱን *ዜናሁ ለጋላ*ን በጥሞና ብንመለከተው ደራሲው ዘመኑን በሉባዎቹ የግዛት ዘመን እንደሚቈጥሩ በቂ ምልክት እናገኝበታለን። ለምሳሌ፥ እነዚህን እንመልከት፦

ከወንድሞቻቸው ተለዩና ቦረን "አምቢሳ" በሚለው -- በርቱማ "ሮባሌ" በሚለው -- ሉባ ዘመን ኀብረት ፈጥረው "አፍሬ" ተባሉ (ክፍል ፩)።

ቢርመጂ በሚባለው ሉባ ዘመን ኀብረት ፈጥረው "ሰደቻ" ተባሉ (ክፍል ፩)።

69. ዜና መዋዕል፤ EMML 7109, f. 58a. እርግጥ በኋላ የመጣ ቀጂ አሳስቷል፣ "ለ" መስተዋድድ መሆኗን ልብ ባለማለቱ ሹሙ "ላሜልባሕ" መስሎት "ለሜልባሕ" ("የሜልባሕ") ሊል የሚገባውን "ላሜልባሕ" ብሎ አበላሽቶታል። ሁለተኛም፣ አንድ ሉባ ከስምንት ዓመት በላይ አያስተዳድርም። ስለዚህ ደራሲው ያለው እንዲህ ይመስለኛል፡ "አፄ ወናግ ሰገድ በነገሠ በ19ነኛው ዓመቱ፡ በሜልባሕ የሹመት ዘመን፡ ከግራኝ ጋራ ሽምብራ ኩሬ ላይ ተዋጋ።"

70. Ignazio Guidi, "Di due frammenti relativi alla storia di Abissinia", pp. 590-1.



ይህ መጽሐፍ በተጻፈበት ጊዜ የቢፎሌ ልጅ የሙልኢታ ሹመት ሰባት ዓመት ሆኖታል (ክፍል ፲፰)።

ቤኪንግሃምና ሃንቲንግፎርድ የሚባሉ ሁለት እንግሊዛውያን ምንጮቹን መርምረው የሉባዎቹን የግዛት ዘመን በዓመተ እግዚእ እንደሚቀጥለው ገምተውታል[71]፤

1522-1530፡ ሜልባሕ፥ ገላን ወንዝን ተሻገረ። (ግራኝ በዚህ ዘመን ወረረ።)
1530-1538፡ ሙደና፥ ዋቢ ሸበሊን ተሻግሮ ባሌ ገባ። (የግራኝ ወረራ ቀጠለ።)
1538-1546፡ ኪሎሌ፥ የደዋሮን ቆላዎች ወረረ። (የግራኝ ወረራ አከተመ።)
1546-1554፡ ቢፎሌ፥ ደዋሮን አጠፋ።
1554-1562፡ ምስሌ፥ ጊቤን መቈጣጠር ጀመረ።
1562-1570፡ ሐርሙፋ፥ በጥረ አሞራን አጠፋ።
1570-1578፡ ሮባሌ፥ ሸዋን አጠፋ።
1578-1586፡ ቢርመጂ፥ ከጣና ባሕር እስከ ዳሞት መጣ።
1586-1594፡ ሙልኢታ፥ ጎጃምን ወረረ።

የዘመኑ ነገሥታት ያልወደዱት ኦሮሞዎች ለራሳቸው በማሾሙት የሉባ ትውልድና አባ ሙዳ የመንፈሳዊ በላይነት መተዳደራቸውን አይደለም፤ ኢትዮጵያ ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ ነገዶችና የእስላም ግዛቶችም አገር ነበረች። ከነገሥታቱ ጋራ ግጭት የሚፈጠረው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ ሌሎች ነገዶች ሲያመቻቸው አንገብርም እንደሚሉት አንገብርም ሲሉ፥ ሁለተኛም መንግሥት የራሱ አድርጎ የሚጠብቀውን "ሀገረ መንግሥት" የሚባለውን ክፍለ ኢትዮጵያና ሌላውን (መንግሥት የሚዘርፈውን) ሁለቱንም እኛ እንዝረፍ ሲሉ ነበረ።

በዚያ ላይ አንድ የከፋው ባለሥልጣን ከመንግሥት ሲጣላ ኦሮሞዎችን "የከፋው ዋሻ፥ ያመፀኛ መሸሻ" ያደርጋቸዋል። ከብዙ ማስረጃዎች ውስጥ ይህንን ከአድያም ሰገድ ኢያሱ (1674-1698) ታሪክ የምጠቅሰውን እንመልከት[72]፤

*ወእምድኅረ በዓለ ፋሲካ ዓመፀ ወሌ ዘእምነገደ መጫ፥ ወቦአ ውስተ ብሔረ ጋላ ኃዲጎ ስመ ክርስትናሁ ጊዜ ርስእናሁ እስመ ከረዮ ጸጋብ እመንገለ ብዝኃ ጕልት። ወኮነ ዕፁብ ዝንቱ ነገር ውስተ ኵሉ ዓለም።*

71. Beckingham and Huntingford, *Some Records of Ethiopia*, pp. lxxiv-lxxv and 205-212.

72. Guidi, *Annales Iohannis I 'Iyasu I et Bakaffa*, II p. 96.

*ወዓዲ ዘየዓቢ እምዝ ዕፁብሰ ዕፁብ ውእቱ ወመንክር በዊአቶሙ ውስተ ሀገረ ጋላ ለመምህረ ጐንጅ ወመምህረ እንጭላላ እንዘ ቆሞሳት ውእቶሙ ወመምህራነ ቤተ ክርስቲያን ወእንዘ አልቦሙ ምክንያተ ነገር ለበዊእ ውስተ ጋላ።*

❖

ከፋሲካ በዓል በኋላ ከመጫ ነገድ የሆነው ወሌ አመፀና ጋላ ሀገር ገባ -- ከጉልቱ ብዛት የተነሣ ጥጋብ ነፍቶታልና በእርጅናው ዘመን የክርስትና ስሙን ትቶ። ይኸ ነገር በዓለም ውስጥ ሁሉ ጉድ ሆነ።

ደግሞ ከዚህ ጉድስ የሚበልጥ ጉድና አስገራሚ ነገር፥ የጐንጅ መምህርና የእንጭላላ መምህር እጋላ አገር መግባት ነው -- ቆሞሶችና የቤተ ክርስቲያን መምህራን ሆነው ሳለና እጋላ አገር ለመግባት ምክንያት ሳይኖራቸው።


ይኸም ሁሉ ሆኖ፥ እንዳየነው እነዚህ ስፍር ቍጥር የሌላቸው ጎሳዎች ዛሬ ለኛ እንደሚመስለን አንድነት ኖሯቸው እንደሆነ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት ይሆናል እንጂ ከገቡ በኋላስ አንድነት አይታይባቸውም። ሌሎቹን አሮሞ ያልሆኑትን ጎሳዎች እንደሚዘርፏቸው አንዱ የኦሮሞ ጎሳ ሌላውን ይዘርፈዋል። "ሁላችሁም ያው ጋላ ናችሁ" የሚሏቸው ሌሎች ናቸው እንጂ እነሱ ራሳቸውን እንዳንድ ሕዝብ አያዩም ነበር። እርግጥ አንዳንድ ጊዜ የመንግሥቱን ግዛትም ሆነ ሌላውን የኦሮሞ/ጋላ ጎሳ ለመውጋት ሲፈልጉ ይረዳዳሉ፤ ግን ዘላቂ አንድነት አይፈጥሩም፤ አንድነቱን የሚፈልጉትም አይመስልም።

"ሉባጌው" የኦሮሞውንም ሆነ የሌሎቹን ነገዶች እንደተለያዩ የኦሮሞ ጎሳዎች እየቈጠረ ኢትዮጵያን በእኩልነት ባህላቸው ቢያስተዳድር ኖሮ ሀገሪቱ ከብዙ ውዝግብ ከመዳን አልፋ ሕዝቡ በውስጥ ነፃነት ብዙ ይራመድ፥ ዴሞክራሲውም ኢትዮጵያዊ ይሆን ነበር። ግን ይህ በሰብአ ትካትነት የሚኖር ሕዝብ ሥልጣኔዋ ከፍተኛ ደረጃ ለደረሰ ሀገር "ይኸንን ባደረገላት" ብሎ መቆጨት አይታሰብም። እንኳን ይህን ሊያደርጉ ራሳቸው ተበታትነው የሀገሪቷን መንግሥት ብትንትኑን አወጡት። ያ እንኳ ባይሆን፥ ዛሬ ንጉሣዊ አገዛዝ ከቀረ፥ መሪው "ፕሬዚዳንት" ከሚባል **አባ ሙዳ** ቢባል እንዴት ባማረብን።

ስለ መንግሥቱ አንድነት ከሆነ ግን ከግራኝ ይልቅ አሮሞዎች ጐድተውታል፤ ግራኝ አጢቃሎ በአንድ ሃይማኖት (በእስልምና) ሊገዛት ያሰባትን ሀገር እነሱ በስፍር ቍጥር አልባ ጎሳቸው ልክ ከተፏት። በነሱ ምክንያት "ሀገረ መንግሥት" የሚባለው ክፍል ሳይቀር በአንድ ማእከላዊ መንግሥት ስር መተዳደር አልቻለም። ለራሳቸው አንድነትን፣ ለሀገራቱም



አንድ መንግሥትን ለማምጣት የልጅ ልጆቻቸው ጎንደር ላይ መሠረቱን መጣል፥ ሸዋ ላይ ቤቱን መሥራት ነበረባቸው። ባጭሩም ቢሆን ታሪኩን እንቃኘው።



ወጠንኩ፡ እጽሐፍ፡ ዜናሆ፡ ለ
ጋላ፡ ከመ፡ አእምር፡ ኍልቈ፡
ነገዶ፡ ወግብረ፡ ትጋሁ፡ ለ
ቀቲለ፡ ነፍሳት፡ ወተአንሶ
ሶቱ፡ ግዕዙ። ወለእመሰ፡ ዘ
ይብለኒ፡ ለምንት፡ ጸሐፈ፡ ዜ
ናሁ፡ ለእኩይ፡ ከመ፡ ዜና፡ ሠ
ናያን። አተብእሶቱ፡ ተወ
ጥዎ፡ ወእብሶ፡ ኅሥሥ፡ ው
ስተ፡ መጽሐፍ፡ ወትርአይ፡
ከመ፡ ተጽሕፈ፡ ዜናሁ፡ ለመ
ሐመድ፡ ወዜና፡ ነገሥቶሙ፡
ለተ●ንበሳት፡ እንዘ፡ ፀር፡ ለነ
ስሙንቱ፡ በሃይማኖት።
ወጊዮርጊስኒ፡ ወልደ፡ አሚድ፡

Codex vindobonensis Palatinus, Aeth. 4, f. 1b.

እስካሁን ከተገኙት የዜናሁ ለጋላ ቅጅዎች አንዱ፡፡

(ገጽ 63 ላይ ተቀድቷል፡፡)

# ምዕራፍ ፩

## ትንሣኤ መንግሥት

ምኒልክ ተወልዶ እልም ባያልም፥
ጎበና ፎክሮ ያን ባይተረጉም፥
ኢትዮጵያ እምትባል የሰው ልጅ እናት፡
በዛሬው ዓለም ውስጥ ቦታም ባልኖራት፡፡




የኦሮሞችን ታሪክ የጻፉ አቶ ዓፅመ ጊዮርጊስ (ዓፅሜ/ዓጥሜ)::

*... del Caffa. Viaggi di Antonio Cecchi, 188*




**የኦሮሞችን ታሪክ የጻፉ አቶ ዓፅመ ጊዮርጊስ (ዓፅሜ/ዓጥሜ)።**

(ከ *Da Zeila alle Frontiere del Caffa, Viaggi di Antonio Cecchi*, 1886)

ለኦሮሞዎቹ አንድነትን ለሀገሪቱም አንድ መንግሥትን ለማምጣት የኦሮሞዎችና የሌሎች ኢትዮጵያውያን የልጅ ልጆች ጎንደር ላይ መሠረቱን መጣል፥ ሸዋ ላይ ቤቱን መሥራት ነበረባቸው።

ኢትዮጵያን እነዚህ ኀብረት አልባ ኦሮሞዎች ሲቆጣጠሯት የማእከላዊ መንግሥት ባለሥልጣኖች መላወስ አልቻሉም ነበረ፤ "*ወሊ ንኩ ኮርማ ታኢ፥ ቡአፌ ያቢ ደወዱ*" ("ወንዶ ኮርች ሁን፥ ወጪና ወራጁን ከልክል") የሚለውን የሸማግሌዎች ምርቃት እንደ ዓሠርቱ ቃላት ትእዛዝ የሚያከብሩት ይመስል ነበረ። አቤቶ ነጋሢ ማህል ሸዋን ሰባት ዓመት ከገዛና ሥልጣኑን በሕዝብ ዘንድ ካረጋገጠ በኋላ የማዕርግ ስም ለማስፈቀድ ጎንደር ሄዶ መመለሻውን ኦሮሞዎች ስለዘጉት እዚያው ሞቶ እዚያው ተቀበረ[1]።

ኢትዮጵያን እንደዱሮው ከዳር እስከዳር የሚያስተዳድር መንግሥት ጠፋ። ሁሉም፥ ኦሮሞዎቹም፥ ክርስቲያኖቹም እስላሞቹም በያዙት ቦታ ኀበዝ እየወጣባቸው ሀገሪቷ የትናንሽ መንግሥታት መጠራቀሚያ ሆነች። "ሀገረ መንግሥት" የሚባለውም ለስሙ ዘውድና አልጋ ጠባቂ ንጉሥ ጎንደር ላይ ይኑረው እንጂ ባለ ዘውዱ እንኳን ሥልጣን ኖሮት ሊሾም ሊሽር የሚበላው አጥቶ "ለንጉሡ መጽውቱት" የሚባል ለማኝ ሆኖ፥ ጉልበተኞች በጎጃም፥ በጎንደር (በስሜን)፥ በትግሬ፥ በሸዋ ራሳቸውን የቻሉ መንግሥቶች አቋቋሙ። ኦሮሞዎችም በጊቤ ወንዝ አገሮች የሉባው ዴሞክራሲ ቀርቶ የቈራጭ ፈላጭ መንግሥት ማቋቋም ጀምረው ነበረ።[2]

በዚህ ጊዜ ነው "ብቅል የገደለውን ብቅል ያነሣዋል" እንደሚባለው የጋሎቹና የሲዳማዎቹ (የኦሮሞዎቹና የአማሮቹ) ልጆች ተቀባይነትን ለማግኘት በአቤቶ ያዕቆብ ዐፅም ተንጠላጥለው የኢትዮጵያን መንግሥት "ነበ ዘቀዳሚ መንበሩ" (ከቀድሞው መንበሩ) የመለሱት። ታሪኩን በአማርኛ ብዙዎች ስለጻፉት እዚህ መድገም አያስፈልግም[3]።

---

1. ኀሩይ ወልደ ሥላሴ (Asfa-Wossen Asserate, *Die Geschichte von Šawā*), p. 38.
2. Huntingford, *The Galla of Ethiopia The Kingdoms of Kafa and Janjero*, London 1955.
3. በዚህ ርእስ ላይ ብዙ ተጽፏል። ከዚህ በታች ያሉትን በማንበብ መጀመር ይቻላል፤ የብላቴን ጌታ ኀሩይ ወልደ ሥላሴ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ* (የፋሺስቶች ወረራ

ለማገናኘት ያህል፥ አፄ ልብነ ድንግል (1500-1537) በግራኝ ጦርነት ከመላ ቤተ ሰቡ ጋራ በሸሽት በነበረበት ጊዜ አንዱ ልጁ አቤቶ ያዕቆብ እዚያው እሸዋ ካንድ ቦታ ተደብቆ ቀርቶ ነበረ። የአቤቶ ያዕቆብ አንዱ ልጁ ገራም ፋሲል የሱስንዮስ አባት ነው፥ ሁለተኛው ዘሮቹ ከኦሮሞዎች ጋራ በጦር ሜዳና በጋብቻ ተገናኝተው ሸዋ ላይ መንግሥት ያቋቋሙት ሥግወ ቃል ነው። (ሶስተኛው፥ ተዝካረ ድንግል የአጐቱን የአፄ ሚናስን መንግሥት ሲቀናቀን ተሸንፎ የእቴጌይቱ ዘመዶች ገደል ወረወሩት።)

ከኦሮሞውም ከአማራውም እየተጋቡ፥ ሥግወ ቃል ወይዘሮ ሰንበልትን፥ ወይዘሮ ሰንበልት አቤቶ ነጋሢን፥ ነጋሢ ስብስቴን፥ ስብስቴ አብዬን፥ አብዬ አምኃ ኢየሱስን፥ አምኃ ኢየሱስ አስፋ ወሰንን፥ አስፋ ወሰን ወሰን ሰገድን፥ ወሰን ሰገድ ሣህለ ሥላሴን፥ ሣህለ ሥላሴ ኀይለ መለኮትን፥ ኀይለ መለኮት ዳግማዊ ምኒልክን ይወልዳሉ[4]።

የዛሬይቱ የኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግሥት ተመልሶ የተቋቋመው አፄ ዮሐንስና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በሀገሪቱ ድንበር ላይ ከጠላት ጋር ሲዋደቁ በነዚህ ልጆችና በመጨረሻም ምኒልክ ኀይለ መለኮትና ጎበና ዳጨ ነፍጠኞች ትግል ነው።

ትዝታቸው፥

ምኒልክ ተወልዶ እልም ባያልም፥
ጎበና ፎክሮ ያን ባይተረጉም፥
ኢትዮጵያ እምትባል የሰው ልጅ እናት፥
በዛሬው ዓለም ውስጥ ቦታም ባልኖራት።

የሚያሰኝ ነው።

ከአፄ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ የጠፋን መፈለግ፥ የተናደን መገንባት ተጀመረ። ስለትንሣኤው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ሲተርኩ እንዲህ ይላሉ[5]፤

---

ኅትመቱን ያጨናገፈው)፤ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፥ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፥ በከፊል፥ Asfa-Wossen Assrate, *Die Geschichte von Šawā*፤ የጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*፤ የተክለ ጻድቅ መኩሪያ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፤ እና የባሕሩ ዘውዴ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1884 እስከ 1966*።

4. ለምሳሌ፥ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ እኅት ወይዘሮ ቀለመ ወርቅ "የአድአውን ባላባት ልጅ አቶ ደሞ ቡኔን አግብተው" እንደነበረ አቶ ገብረ ሥላሴ አጳ ያስታውሳሉ፤ *ትዝታ ለመታሰቢያ*፤ ገ. 6-7።
5. ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፤ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ*፤ ገ. 100።



ከዚህ በኋላ በ፲፰፻፷፬ ዓመተ ምሕረት በዲርማ ደብረ ነጐድጓድን፥ በለገሒዳ አትሮንሰ ማርያምንና ታዕካ ነገሥትን፥ በለገኈራ መካነ ሥላሴን፥ ጥንት በኖራ የተሠሩ አብያተ ክርስቲያናት በግራኝ ጊዜ የተቃጠሉትን እያስቆፈሩ ግምቡን አስወጡት። የግምቡም ቁመት ሰባትም ስምንትም ክንድ ሆነ። ነገር ግን ከቀን ብዛት የተነሣ መሬቱ አጥብቆ ውጦታልና እስከ መሠረቱ ለመቆፈር አልተቻለም። ሥራውም ድንጋዩ አራት ማዕዘን የተጸረበ የተቀረጸ እጅግ የሚያስደንቅ ነው። ከዚያውም ብዙ ንዋየ ቅድሳት ወጣ። የወሎም ሰው ይህን ሁሉ ባየ ጊዜ እውነትም የክርስቲያን አገር መሆኑን ተረዳው።

ከዚህ ጥቅስ አራት ነገር እንረዳለን፤ (1) እነዚህ የታወቁ የአማራው አገር ታላላቅ አድባራት በግራኝ ወረራ ጊዜ መቃጠላቸውን (በታሪክም አንብበናል)፥ (2) በኦሮሞዎች ወረራ የቦታዎቹ ስሞች መለወጣቸውን (ዲርማ፥ ለገሒዳ፥ ለገኈራ)፥ (3) "አዲሱ" ትውልድ አዲሶቹን የቦታ ስሞች መቀበሉን፥ (4) ቅርሶች ከመቃብር ለመነሣት ዕድል ማግኘታቸውን።

በሀገርና በመንግሥት መካከል ያለው ልዩነት እንዳይማታ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ምኒልክና ጎበና ዳጨ መልሰው ያቋቋሙት ማእከላዊውን መንግሥት እንጂ ሀገሪቷማ ሁል ጊዜም በልጆቿ እጅ ነበረች። የቦታ ስሞችን የለወጡት ራሳቸው ኢትዮጵያውያን ስለሆኑ ወደኋላ ወደዱሮው እንመልስ ያለ የለም።

የማእከላዊው መንግሥት ትንሣኤ ሸዋ ላይ ይወለድ እንጂ፥ የተፀነሰው ቀደም ብሎ እዚያው እጎንደር ነው። እንደምናየው፥ በጎንደር ዘመነ መንግሥት በኦሮሞዎችና በመንግሥት መካከል ብዙ ጊዜ በጥቅም ምክንያት የረጅም ጊዜ ግጭት ተካሂዷል። ሆኖም ላይ ላዩን "ጋላና ክርስቲያን" ወይም "ኦሮሞና ሲዳማ" የማይገናኙና የማይጣጣሙ ይምሰሉ እንጂ፥ የነፃነቱ አብሮ ኑሮ በማህል ያለውን የዘርና የባህል ልዩነት የሁለት ኩሬን ውሐ የሚገድበውን ግድብ እንደሚያፈርስ ኃይል ቦርቡሮት ውስጥ ውስጡን በባህልም በዘርም ተደበላልቀዋል። አምቻና ጋብቻነቱ እስከ ቤተ መንግሥት ዘልቋል። ኦሮሞዎች እንደነ አዛዥ ሀካኮ በሥርዓቱ ውስጥ ገብተው ሥልጣን ተካፍለዋል። ተጨማሪ ምሳሌ ካስፈለገ እነዚህን ከአፄ ኢያሱ (1676-1698) ታሪክ የቀዳኋቸውን ሁለት ጥቅሶች እንመልከት፤

(1) *ወዳግመ ሜጽአ ጨዋሂ ዘይብል ወጽአ ጋላ ወፀብአ ለድን። ወሶበ ሰምዓ ንጉሥ ዘንተ ነገረ አዘዞ ለጸሐፌ ላሕም ቱሉ ወይቤሎ ሑር ትልዎ ወኢያምስጥከ። ወውእቱኒ ሖረ በሌሊት ወተለዎ ወረከቦ ለጋላ በምድረ ጨ።*

❖

(1) "ጋላ መጥቶ ድንን ወጋው" የሚሉ ትክለኛ ወታደሮች እንደገና መጡ:: ይህንን ነገር ንጉሡ ሲሰማ ጸሐፌ ላሕም ቱሉን፥ "ሂድ (ጋሎችን) ተከተላቸው፥ እንዳያመልጡህ" ብሎ አዘዘው:: እሱም በሌሊት ሄደና ተከተላቸው፤ ጋሎቹን በምድረ ጨ አገኛቸው[6]::

(2) *ወበውእቱ ወርኀ ሤሞ ለዮሐንስ ሢመተ ጸሐፌ ላህም ዘዳሞት:: ወሤሞ ሢመተ ብላቴኖች ጌታ ለጠቢብ ወማዕምር ወለባዌ ፍትሕ ወክቡረ ዘመድ ወነገድ ዘእምነገደ ጋላ ወአድያ ዘውእቱ ባስልዮስ ወልደ ቡናያ ወወልደ እኅቱ ለደጃዝማች ሎሬንስ::*

❖

(2) በዚህ ወር ዮሐንስን የዳሞት ጸሐፌ ላህም ሹመትን ሾመው:: ከጋላ ነገድና ከአድያ የሆነውን ጥበበኛውን፥ ዐዋቂውን፥ ፍርድ አስተዋዩን፥ ባለ ተከበሩ ዘመዶች የሆነውን የቡናያን ልጅና የደጃዝማች ሎሬንስ እኅት ልጅ ባስልዮስን የብላቴኖች ጌታ ሹመትን ሾመው[7]::

በዚያን ዘመን የብላቴኖች ጌታ ማዕርግ ከቢትወደድነት ቀጥሎ ነበረ:: ግን ጸሐፊው የባስልዮስን ነገድ ባይነግረን የማን ነገድ ይመስለን ነበረ? በስማቸው ምክንያት ኦሮሞዎች መሆናቸውን ሳናውቅ የቀረን ስንቶች ናቸው? የክርስቲያኑ መንግሥት ስንል የኦሮሞዎችና የሌሎቹ ሁሉ ክርስቲያኖች መሆኑን ማስታወስ አለብን::

በደም የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን ከተራው ሕዝብ ቤት እስከ ቤተ መንግሥት የጎሳዎችና የነገዶች ግንኙነት ውጤት መሆናችንን የሚያሳየው ያያቶቻችን የጋብቻቸው ታሪክ ያልተጻፈው በኢትዮጵያውያን መካከል ጋብቻ ጉድ ወይም ብርቅ ስላይደለ ነው:: የአፄ ምኒልክ ልጅ ወይዘሮ ሸዋረገድ የራስ ጎበና ልጅ የአቶ ወዳጆ ባለቤት እንደነበሩ የተጻፈው የገዥዎች ታሪክ ስለሆነ ነው እንጂ አፄ ምኒልክ አማራ (!) ራስ ጎበና ዳጩ ኦሮሞ ስለሆኑ ያንን እንደ ታሪክ ለመመዝገብ አይደለም:: ክቡር ልጅ ሚካኤል እምሩ ራስ ጎበና ዳጩ አያታቸው መሆናቸውን የነገሩን ***ለንድነት*** ጋዜጣ ስለጠየቃቸው ነው:: ያውም ቢሆን ዘራቸውን ለመቍጠር ሳይሆን ቤተ ሰባቸው ለኢትዮጵያ መንግሥት ትንሣኤ ስላደረገው አስተዋጽኦ ታሪክ ሲያስተምሩን ነው::

በባህልም ረገድ ኦሮሞዎች ኢትዮጵያ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በነሱና በወረሩት ሕዝብ መካከል ከፍተኛ መደባለቅ ነበረ:: ለምሳሌ፡ ክርስቲያኖቹ ስማቸውን "ዘጸ"፡ "ዐስቦ"፡ "ዐምዶ"፡ "መንገዶ"፡ "ተዝካሮ"፡ "ዘሦ"፡ ወዘተ እያሉ በሳብዕ ሲያሳጥሩ እናያለን:: የሆነው፡

6. Guidi, *Annales Iohannis I 'Iyasu I et Bakaffa*, part II, p. 206-7.

7. እዚያው ገ. 170::



ኦሮሞዎች "ጢኖ"፥ "ጥሂቶ"፥ "ሐለብዶ"፥ "በርባዶ"፥ ወዘተ እያሉ ስም የሚያወጡበትን ዘዴ በመውሰድና የራሳቸው በማድረግ ነበረ:: በአማርኛ ላይ የሚታየውን የባህላቸውን ጉልሕ ተጽእኖ ትተን ግዕዝን ብንመረምረው የኦሮሞ ባህል ተጠቃሚ ሆኗል:: ይሄ የሆነው ኦሮሞዎች የግዕዝ ዓለም ጎረቤቶች ስለሆኑ ሳይሆን፥ እንደ ኦሮሞዎቹ እንደ አዛዥ ጢኖ እና የጎጃምን ታሪክ እንደጻፉልን እንደሠዓሊው እንደ አለቃ ተክሌ የግዕዙ ሥነ ጽሑፍ ባለቤት ስለሆኑ ነው::

የሀገሪቱ ባህል በአዲስ ደም እንደፋፋ ግልጽ ነው:: አባ ባሕርይም ቢሆኑ ይኸንን ያህል ዝርዝር የጻፉት ስለባለቤት እንጂ ስለ ጐረቤት ወይም "እጋላ አገር" ሄደው ያገኙት "የመስክ ጥናት" አይደለም::

የየጎሳው ልጆች ያስመሰለን ታሪካዊ አጋጣሚና በቦታ መወሰን ምክንያት ግማሾቻችን ያንዱን ነገድ ቋንቋ፥ ግማሾቻችን ደግሞ የሌላውን ነገድ ቋንቋ ስለምንነጋገር ነው:: ለምሳሌ፥ ደምቢያን (ጎንደርን) እና ጎጃምን የወሰዱ ኦሮሞዎች ልጆች ቋንቋ አማርኛ ሆኗል፤ አማራ መስ-ለዋል:: የአርሲ ሕዝብ ከግማሽ በላይ የሐድያ ትውልድ ሆኖ ሳለ ቋንቋው ኦሮሞ ሆኗል፤ ኦሮሞ መስሏል:: ይህ መስሎ መገኘት ለጠላት መግቢያ ትልቅ ቀዳዳ ሆኖ እነሆ ሊያተራምሰን ይመላለስበታል::

የምንነጋገረውን ቋንቋ ተከትለን ኢትዮጵያ ውስጥ ከተፈጸሙት ታሪካዊ ድርጊቶች አንዱን ክፍል የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ አንዱን የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ ታሪክ እናድርግ ብንል እውነት አትፈቅድልንም:: የአያቶቻችን ልጆች መሆናችንን በማያጠራጥር ግምት የምንደርስበትን ያህል የቅድምአያቶቻችን ቋንቋ ምን እንደነበረ አንደርስበትም:: ዛሬ የትኛውንም ቋንቋ ወርሰን ብንገኝ ሁላችንም፥ በዚያን ዘመን አነጋገር የጋሎቹና የሲዳሞቹ፥ ወይም በዛሬው አነጋገር፥ የኦሮሞዎቹና የአማሮቹ ልጆች ነን::

በምንናገረው ቋንቋ እየተመራን ከጥንት ዘራችን ልንደርስ የማንችልበት ምክንያት ቋንቋዎቹን ጥምዝምዙ የታሪክ መንገድ ስላሳወራቸው ነው፤ ዕውር ደግሞ መምራት አይችልም፤ ቋንቋዎችን ታሪክ አካፋይ ብናደርጋቸው ሲደናበሩ ለነሱ (ለቋንቋዎቹ) እንደሚመች አድርገው፥ ግማሾቻችንን ከናታችን ግማሾቻችንን ከአባታችን ዘርና ታሪክ ያለያዩናል:: በ16ተኛው ምእት ዓመት ኢትዮጵያን የወረሩ ኦሮሞዎችና ሊከለክሏቸው የሞከሩ የቀድሞዎቹ ነባሮች ሁሉም ከሞላ ጐደል እኩል አያቶቻችን ሆነዋል፤ እኛም እንደዚያው ከሞላ ጐደል እኩል ልጆቻቸው ነን::

የምንናገርበትን ቋንቋ ማስረጃ አድርገን ከተፈጸመው ረጅም ታሪክ ውስጥ ኦሮሞዎቹ የፈጸሙትን ዛሬ ኦሮምኛ ለሚናገሩ ሌላውን ለሌሎች ማካፈሉን የምንገፋበት ከሆነ መጀመሪያ ታሪኩን ከአያቶቻችን ነጥቀን ለወረስናቸው ቋንቋቻቸው መስጠት ይኖርብናል:: ይህ ደግሞ

“ባለታሪኩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም፤ እኛ ታሪክ የለንም” ማለት ይሆናል።

እርግጥ ኦሮምኛ የሚናገሩ ኦሮሞ የሚባሉ ኢትዮጵያውያንና ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ የግል መጠሪያ ያላቸው ሌሎች ኢትዮጵያውያን አሉ፤ እነዚህ ሰዎች ታሪክ አንድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጋቸውን ረስተው ልዩነታቸውን ለማጠንከር ከፈለጉ ከአሁን ይጀምሩት እንጂ ወደ ታሪክ አይሂዱ፤ ታሪክ ያሳቅቃቸዋል፤ ፍላጎታቸውንም ውድቅ ያደርግባቸዋል።

# አባሪ

# Appendix



በኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፋቸው ውስጥ ስለ ኦሮሞች በሰፊው የጻፉ አለቃ ታዩ።

(ከ Gustav Arén, *Envoys of the Gospel in Ethiopia,* 1999)

# አባሪ ፩ - Appendix I

## ከአለቃ ታየ ትልቁ መጽሐፍ የተቀዳ

(JE692E, ገ. 548-561, 586-7, 595-600)

"ሌም" ሌሎች ምንጮች፥ "መ" የኢየሩሳሌሙ ቅጂ የአለቃ ታየ መጽሐፍ፡ (JE692E)።
(በጎዳግ ካልገለጽኩ በቅንፍ ያለው የጸሐፊው ነው)

### 17. ስለ ነገደ ጋላ

ስለ ነገደ ጋላ የሚነገር ቁም ነገርና እውነት፥ እውነትና ተረት የሆነ በየአይነቱ ብዙ ልዩ ልዩ ታሪክ አለ። አቶ ዓጽሜ በጻፉት የታሪክ መጽሐፍ ስለ ጋላ ሲናገር እንዲህ ይላል። ጋላ የሚሉት ሕዝብ ካገሩ የወጣበት ምክንያት እጅግ አይታወቅም። ባለታሪኮች እኒህ የጋላ[1] ሕዝብ ከእስያ ፈልሰው ወደ ማዳጋስካር እንደ ተሻገሩ፥ ከዚያም ፈልሰው ቦባሳ አጠገብ ከባሕር ወደብ ተቀመጡ። ቦባሳ ማለት ለክብትም ቢሆን መሠማሪያ ማለት ነው፥ በጋልኛ። ከዚያም ገናሌ የሚባለውን ጅረት ተከትለው ኢትዮጵያ ወጡ ይላሉ።

ካገራቸው ሲወጡ ግን ሁሉ ባንድ ጊዜ አልወጡም፤ የወደደ ወጣ ያልወደደ ቀረ እንጅ[2]፤ ይህ ጋላ የተባለ ሕዝብ ከዚያ ተነስቶ መጣና በባሌ ዳር ገላና በሚሉት ጅረት (ወንዝ)[3] ዳርቻ ተቀመጠ። ላሙንና[4] ፍየሉን በጉን እያረባ እንደ ዘላን ሁኖ ኖረ።

ከመጣም ካፄ ልብነ ድንግል ስመ መንግሥታቸው[5] ወናግ ሰገድ ከሳቸው መንግሥት በፊት 102 ዓመት[6] ሁኖት ነበር። ይህም አፄ ይስሐቅ በነገሡ በ፳ ዓመት በ፮ ሺህ ፱፻፬ዓመተ ዓለም፥ በ፲፬፻፬ ዓመተ ምሕረት

1. መ የገላ።
2. Bairu Tafla, *Aṣma Giyorgis and His Work,* pp. 56-57 and 138.
3. መ።
4. "ላሙን" የሚሉት ግስዙን ተከትለው ነው፡ በሬም ይጨምራል። ከብቱን ማለታቸው ነው።
5. መ "ሥታቸው።
6. መ ዓመ።



በኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፋቸው ውስጥ ስለ ኦሮሞች በሰፊው የጻፉ
አለቃ ታየ::

ነው፤ የሚሉ አሉ። እውነተኛው ግን የጋሎች ወደ ኢትዮጵያ መውጣት በዛጌ (መራ ተክለ ሃይማኖት ስመ መንግሥቱ ዛጔ[7]) መንግሥት ፲ዓመት በ፱፻፴ ዓመተ ምሕረት ነው።

ፈረንጆች ስለ ጋላ የጻፉት ታሪክ በራስ ዕውቀትና በመመርመር ነው። እኛ ግን አዛዥ ጢኖ የጻፈውን ታሪክ አይተን ነው።[8]

ጋሎች ሲመጡ በጋላኔ ወንዝ (ጅረት)[9] ወጥተው ሐሮ ውላቦ በሚባል አገር ገቡ። በሐሮ ውላቦ ዋናተኛ በዋና የሚቆርጣትና የሚሻገራት ትንሽ ኵሬ ባሕር አለች። ጋሎች አባታችንና ፍጥረታችን ከዚህ ውሀ ወጣን ይላሉ። ስለዚህም፥ ዑማን ውላቦ ባቲ ይላሉ። ይህም ከውላቦ ውሀ ፍጥረት ወጣ ማለት ነው። ስለዚህ ጋሎች ለውሀ ይሰግዳሉ። ሰውም እንስሳም ከዚያች ውሀ አይጠጣም። ክልክል ነው። ጋላ ሁሉ ከዚያ ለውሀይቱ ይሰግዳል። ከዚያም ሰንጋና ብዙ ፍሪዳ በግም ፍየልም ያርዳሉ።

በሐሮ ውላቡ ልዩ ልዩ ቋንቋ ያላቸው ጥቂት ሕዝቦች አሉ። ዶራስ ይባላሉ። የጋላን ሕዝብ ይመስላሉ። ከሲዳሞ እስከ ውላቡ ፬ቀን፥ ከውላቡ እስከ ቦረን ፭ቀን ያስኬዳል።

ጋሎች ፪ ነገድ ናቸው፤ በርቱማና[10] ቦረና[11] ይባላሉ።
በርቱማ ፮ ልጆችን ወለደ። እነርሳቸውም እኒህ ናቸው፤

፩፥ ከረዩ
፪፥ መረዋ
፫፥ ኢቱ
፬፥ አክቱ[12]
፭፥ ወረንሸ[13]
፮፥ ሁበና[14]

የበርቱማ የበኵር ልጁ፥ ከረዩ ፮ ልጆች ኃይለኞች ወለደ። እነርሳቸውም፤

፩፥ ሊበን

7. ቅንፍ የመ።
8. አዛዥ ጢኖ የጻፉት የሚሉት የትኛውን ድርሰት እንደሆነ አይታወቅም፣ ዜናሁ ለጋላን አስፋፍተው የጻፉት ይመስላል።
9. መ።
10. ሌም "በርቱማ"ን እና "በረይቱማ"ን ያፈራርቋቸዋል።
11. "ቦረን" እና "ቦረና" የአንድ ነገድ ስም ይመስላሉ።
12. መ "አከቱ"ን እና "አክቴ"ን ደጋግሞ ለየብቻቸው ስለሚጽፋቸው የስሕተት ጉዳይ አይመስልም።
13. ሌም "ወረንሻ"ን እና "ወረንጥሻ"ን ያፈራርቋቸዋል፥ አሁን ደግሞ መ "ወረንሸ"።
14. ሌም ሁምበና።



፪፥ ትሉማ። ወሉ[15]
፫፥ ጆሌ
፬፥ አቦ
፭፥ ሉባ
፮፥ ዐለስ ናቸው።

ወሉ ከ፮ ሴቶች ፯ ወለደ።

፩፥ ሂበኖ
፪፥ ዐበይ
፫፥ አሊ
፬፥ ቃሉ
፭፥ አምቦ
፮፥ ሂዳ
፯፥ ጎራ ናቸው።

ከኒህ ሌላ ደግሞ ለወሉ በኩ፥ ኖሊኢኑ የሚባሉ ፪ልጆች አሉ የሚሉ አሉ።

ቦረና ፲፩ልጆች ወለደ።

፩፥ ዳጬ
፪፥ ጆሌ
፫፥ ኮኖ — እኒህ
፬፥ ቦች — ትሉማ ይባላሉ[16]።
፭፥ አካኮ
፮፥ ወቦ — እኒህ
፯፥ ሉባ — ሰደቻ ይባላሉ።
፰፥ ጭሌ
፱፥ ሊቦን
፲፥ ጕድሩ
፲፩፥ ሆኮ ናቸው።

እኒህ ሆኮ ይባላሉ።
ከወሉ ልጆች ፫ቱ ፌተኞች በወሉ ስም ይጠራሉ፤ ፬ቱ በወረሰደቻ ስም ይጠራሉ ይባላል።

መረዋ የበርቱማ ሁለተኛ ልጁ ወርድያንን[17] ወለደ።

15. ሌም "ቱለማ"፡ "ቱላማ" ። "ወሉ" የተጨመረው ለእርማት ይሁን አይሁን አይታወቅም።
16. ቍ. 15ን ተመልከት።
17. እንዲ "ን" በስሕተት የገባ መሆን አለበት፥ ቍ. 19ን ተመልከት።

ወርድያን ፫ልጆችን ወለደ፡፡ እነርሳቸውም፤

፩፥ አና
፪፥ ዑር[18]
፫፥ አበጢን[19] ናቸው፡፡

እኒህ የመረዋ ልጆች በኃይልና በብዛት ከሁሉ ይበልጣሉ፡፡

ይህም የጋላ ሕዝብ አረማዊ ሕዝብ ነውና እግዚአብሔርን አያውቅም፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ ጽፎ ከሰጠው ካ፲ቱ ቃላት ለጋላ የጐደለው መጀመሪያ ትእዛዝ ያንተ አምላክ እኔ ነኝ፤ ከኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ ያለው ብቻ ዋና ነገሩ ነውር[20] ከባህርይ ሕግ ጎዶሎነት የሚያስተምረው ሐዋርያ ስላጣ ሁሉን ይፈራልና ዛፉንም ወንዙንም ባሕሩንም ደንጊያውንም ገደሉንም ያመልካሉና ይሰግዳሉም፡፡

ሁለተኛ እሁድን ሰንበተ ጉዳ ቅዳሜን ሰንበተ ጢና እያለ እንደ ክርስቲያን ያከብራል፡፡

ሶስተኛ ምንም ቢሆን በሐሰት አይምልም፡፡

አራተኛ አባት እናቱን አክብሮ በዕድሜ የበለጠውንም ባልንጀራውን ያከብራል፡፡ አለዚያ በጨፌ ማለት በሸንጎ ጉባኤ ይፈረድበታል፡፡

አምስተኛ ነፍስ የገደለ በጉማ የነፍስ ዋጋ በመክፈል በእጅግ ብዙ ገንዘብ ይቀጣል፡፡ ደግሞ ነገሩ ታይቶ በአዩ በሉባ ተፈርዶበትም የሚሞትም አለ፡፡

ስድስተኛ ምንዝር[21] በጨፌያቸው ወይም በችሎታቸው ከክርስቲያኖች ይልቅ እነሱ መልካም ይፈርዳሉ፡፡

እነዚህም የበርቱማና የቦረን ልጆች የጋላ ነገድ ሁሉ ከሕፃንነት ጀምሮ እስከሽምግልና እንደ ክህነት ያለ መዓርግ አላቸው፡፡ ይህ መዓርጋቸው ገዳ ይባላል፡፡ ገዳ ማለት እንደ ክህነት ያለ ሹመት ሥልጣንም ነው፡፡ ይኸውም ሥልጣናቸው እንደ ዘመናቸው ቍጥር ለ፰ ለ፰ ዓመት ነው፡፡ ዘመናቸው በ፰ በ፰ ዓመት ይከፈላል፡፡ ገዳ ይሉታል፡፡

በ፰ በ፰ ዓመት የሚከፍሉትም ባ፭ ሉቦች ስም እንደ ተጠራ ፭ ናቸው፡፡ በ፰ በ፰ ዓመት አንድ ሉባ ተሽሮ ሌላው ሉባ ሲሾም እንደ ሌላው ሕዝብ ንጉሥ ባላባትም[22] ጌታም የለባቸውም፡፡ እስከ ፰ዓመት ለሉባ ይታዘዛሉ፡፡ ከ፰ ዓመት በኋላ ሌላ ሉባ ይሾማል፡፡ የዚያ ጊዜ ለየነገዳቸው ስም ያወጣሉና ይገዛራሉ፡፡

18. ሌም ኡሩ፡፡
19. መ፡፡
20. መ፡፡
21. ዐዕሜ "አመንዝራ"፡፡
22. መ ባለበትም፡፡



ነገሩ እንደኛ ይመስላል፡፡ እኛ ዓመት በእየ ወንጌላዊ ስም እንደምንጠራቸው[23]፥ ፩ ማቴዎስ፥ ፪ ማርቆስ፥ ፫ ሉቃስ፥ ፬ ዮሐንስ ብለን ለ፬ ዓመታት ስም እንደምንሰጣቸው[24]፥ እነሱም በ፰ ዓመት አንድ ስም ይሰጣሉ፡፡ ፵ውን ዘመን ባ፭ አርበኞች ስም ይጠራሉ፡፡ ፵ውን ዘመን ሲጨርስ ተገዝሮ ሉባ ይሆናል፡፡

ይህም ፵ው ዘመን ካ፭ የሚከፍል ያ፭ አርበኞች[25] ስም የሚጠራበት እኒህ ናቸው፡፡

መጀመሪያው፥ ገዳ ቢርመርጂ ነው፡፡[26] ሁለተኛው፥ ሆረታ[27] ወይም ሚልባህ፤ ሶስተኛው፥ ምንችሌ[28] ወይም ሙደና፤ አራተኛው፥ ዱሎ፤ አምስተኛው፥ ሮበሊ ይባላሉ፡፡ እነዚህ የጋላ ሕዝብ ሥራት አባ ዱሎች በ፰ በ፰ ዘመን ይመላለሳሉ፡፡ የጋላ ታላቁ[29] ሕግ ይህ ነው፡፡

ደግሞ ከዚህ ሌላ ሞጋሳ ኮሉ የሚባል ሥራትና ሕግ አላቸው፡፡ ሞጋሳ ለባዕድ ነው፡፡ እሱም የጡት ልጅ እንደማለት ያለ ነው፡፡ ኮሉ ከጎሳ ወገን ነው፡፡ ይህም ረዳት ወይም አዛዥ እንደማለት ነው፡፡

የሕጋቸውም ሥርዓት እንዲህ ነው፡፡ ጋላ ከተወለደ ጀምሮ እስከ ሞቱ ድረስ ሕግና ሥርዓት አለው፡፡ አባቱ ተገዝሮ ሉባ ሲሆን፥ ልጁ ለ፰ ዓመት ኢትሚኮ ይሆናል፡፡

ቀጥሎ ለ፰ ዓመት ደበሌ ይሆናል፡፡ የሕግን ሥርዓት ካባቱ ከሽማግሌችም ይማራል፡፡

ሶስተኛ፥ ጢፎሊ ይባላል፤ ነጻ የወጣ ነው፡፡ ይዘፍናል፥ ይጨፍራል፥ የፈቀደውንም ይሠራል፡፡ ተው ይህ ከፉ ይህ በጀ የሚለው የለም፡፡ በዘፈን በጭፈራ ይጣላሉ ይጋደላሉ፡፡ የነጻ ዘመን ነውና ነገር የለበትም[30]፡፡

፬ተኛ ቍንዳላ ይሆናል፤ በዕርጋታ በመደመም ይኖራል፡፡ ወደ ጨፌ ይሄዳል፥ በሸንጎም ይቀመጣል፡፡

፭ተኛ የቍንዳላነቱን ዘመን ከጨረሰ በኋላ ያሮማይ ይባላል፡፡ ወደ ጨፌ አይሄድም ወደ ሸንጎም አይወጣም፡፡ የቀሩት ወደ ጨፌ ሲሔዱ እሱ በመንደር ይቀራል፡፡ ሌባ ቀማኛ[31] ወንበዴ ይሆናል፡፡ የማንንም በግና ፍየል

23. መ እንደምጠራቸው፡፡
24. መ እንደምሰጣቸው፡፡
25. መ "ኞች፡፡
26. ጸሐፊዎቹ ገዳን እና ሉባን፥ የሉባውን የተጸውዖ ስምና የሹመት ስም፥ የሉባዎቹን ቅደም ተከተል የሚሰጡት በተለያየ መልክ ነው፡፡ ለዚህ ድርሰት መነሻውን የአባ ባሕርይን ድርሰት ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ገዳ ሥርዓቱ ነው፤ ሉባ ባንድ ዘመን ተገዝሮ 8 ዓመት የሚገዛ ትውልድ ነው፡፡ "ቢርመርጂ" ቢርመጂ ነው፡፡
27. አባ ባሕርይ አያውቁትም፡፡
28. ሊም ምስሌ፡፡
29. መ ታሉቁ፡፡
30. መ የለበም፡፡
31. መ ቀመኛ፡፡

እያረደ ይበላል። ብቻ ካንድ በረት ፩ በግ ፩ ፍየል ፩ ሰንጋ እንጂ ፪ አይወስድም።

እንዲሁም እኒህን ፭ መዓርጋት ሲፈጽም ፵ ዘመን ይሆነዋል። ከዚህ በኋላ ይገዘራልና ሉባ ይሆናል።

አዩ ግን ከወገኑ ተመርጦ ወገኑ የወደደውን ይሾማል። ገዳውን የጨረሰ[32] ሉባ ይሾሙታል። አዩም ቦኩን አስመርቆ በጨፌ ይቀበላል። ቦኩ ማለት የወይራ ዱላ ነው። እሱም ቅቤ የጠገበ የተወለወለ እንደ በትረ መንግሥት የከበረ ነው። በሱ ተሹሞ ይመረቅበታል። ፰ ዓመት ተሹሞ ይፈርዳል። ከ፰ ዓመት በኋላ ይሻራል። አይፈርድም፤ ከጨፌም አይደርስም። ሉባ ዱለቻ ይባላል። አዩ በደጁ ከብዙ ሉቦች ጋራ ይፈርዳል።

በ፰ በ፰ ዓመት ጋላ ሁሉ ተሰብስቦ የሚፈርድበት ያለፈውም የ፰ ዓመት ታሪክና ፍርድ የሚነገርበት የተነቀፈው ተነቅፎ አዲስ ሕግ የሚሠራበት ለሚመጣውም የጋላ ሕግና ሥርዓት የሚሰበክበት ቦታውና ጨፌው በቀድሞ ዘመን ቦረና ነበር። ከዚያም የሚፈርደው አባ ሙዳና ይባላል። አባ ሙዳና ማለት መሢሐዊ ወይም የተቀባ ማለት ነው።

ከቦረናም ከወጡ በኋላ እስከዛሬ ከየጎሳው ወደርሱ ስብከቱና ትእዛዙን ሰምተው የሚመለሱ ፪ ፪ ሰው ይልኩ ነበሩ። እነሱም በተመለሱ ጊዜ በእየጨፌው አዩ በክብር ይቀበላቸዋል። እነዚህም ጅላ ይባላሉ። በልብሳቸው ወይም በምልክታቸው የታወቁ ናቸውና በሰልፍ መሀከል ቢሄዱ የሚነካቸው የለም።

ከቦረና ከወጡ ወዲህ የሁሉም ጨፌ መልካ ቦሎ አዋሽ ነበረ። አዩም የሚፈርደው ከጋላን[33] ነበረ። በኋላ ዘመን ጋሎች እስበሳቸው ሲጣሉ ቦታም ሲጠባቸው በሚጥጫም[34] ሲለያዩ በጨፌም ተለያዩ።

32. መ "ሻ።
33. መ።
34. የ"ሚጥጫ"፡ "ሜጥቻ" ትክክለኛ ትርጉም ምን እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም። ቃሉም አንዳንድ ቦታ "መጥቻ" ተብሎ ተጽፎ ይገኛል። ግን የከብት መንጋ መሆን አለበት። "ከግራኝ ወዲህ ሸዋን የተሎማ ጋላ ሜጥቻ አሰረበት።"፥ (EMML 1515 p. 160)። ከዘመቻ በፊት የሚደረግ የከብት ደም ማፍሰስና መቀባት ያለበት አምልኮ በዚሁ ስም ይጠራል። አንድ ምንጭ ክርስቲያኖቹን ሲወቅስ፡ "እንደ ጋላም ደመ መጥቻ ለፈረስ ይቀቡ ያደርጉ ዠመሩ" ይላል (EMML 144, f. 113a)። አምልኮው ወደ ጦርነት ሲወጡ የሚያደርጉት መሆኑን የልማዱ ታሪክ ያስረዳል። ኦሮሞዎች በንጉሡ ሹምና በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያምፁ ድል የሚያደርጉበትን ዘዴ እንዴት ጋኔን እንደነገራቸው ጸሐፊዎቹ ሲተርኩ እንዲህ ይላሉ፡ "ይህ ላሎ የሚባል ሰው ቡላ ፍየል ጥቁር በግ ነጭ ላም ቅቤ ይዞ (ከጠንቋይ ዘንድ) መጣ፡ ምን ላድርግ አለው። ከዚህ በኋላ ... እንዲህ አለው፤ በጉን ፍየሉን ላሚን አርደህ ደማቸውን በቅቤ አመድ ለውሰህ ቀድመህ አንተ ግምባርህን ተቀባ፡ ለፈረስህም ቀባው፤ ልጆችህም እንዳንተ ይቀቡ። ሥጋውንም አንተ በፊት



ስለዚህ አዋሽ መልካ ቦሎ የቱለማ[35] ጨፌ ሆነ። የአዩም ያው ገላን[33] ነው። የመጫም ጡሌ ሆነ። እኩሌታ መጫ ነገሥታት አሉበት።

የይቱ ጨፌ ካራ ቁርቁራ ሆነ።

ከቡርቃ[36] በታች የሐረርጌ ጋላ ጨፌ በሉሎ ነበረ።

እንደዚህም ወሎ አሩሴም በየደጃቸው ጨፌ አደረጉ።

ይኸውም ጨፍያቸው በመሰብሰባቸው ሁከት እንዳይነሳ በዳግማዊ ምኒልክ አዋጅ ተከለከሉ[37]። እንዲህ ስለሆነ ጋሎች በጨፊያቸው የሚፈርዱበት ባጠገባቸው ካለነው ክርስቲያን ነን ከምንለው ይልቅ የነርሳቸው የተሻለ የጸናም ነው።

በጋላ ሥርዓት በሉባ በአዩ በጨፍያቸው ጋላ ያባቱንና የናቱን ልጅ አያገባም። ያጎቱን የእኅቱን ልጅ አያገባም። ሕግ ተላልፎ ቢያገባም እስከሞት የሚያደርስ ብርቱ ቅጣት አለበት። ከወገኑ ከዘመዱ ማግባት በነርሳቸው ዘንድ እርም ነው።

ጥንቱንም አልተጀመረም እንጅ በጨፌ አፍርሰውትም ቢሆን ከሕግ ወጡ ማለት ነው፤ በሕጋቸውም ይፈረድባቸዋል። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል። እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ አያደላምና ሕግ ሳይሰራላቸው የበደሉ ሁሉ ያለ ሕግ ይጠፋሉና። ሕግ ተሠርቶላቸውም የበደሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል። ሕግን የሚሰሙ በእግዚአብሔር ዘንድ ጻድቃን አይደሉምና ሕግን የሚሰሩ እነርሳቸው ይጸድቃሉ እንጅ። ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባህርያቸው ሕግ ቢያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው ለራሳቸው ሕግ ናቸው። ሕግንም በማድረግ በልባቸው የተጻፈውን ይገልጣሉ እርስበርሳቸውም ልባቸው ይመሰክርባቸዋል። አሳባቸውም ይገሥጻቸዋል። እግዚአብሔርም በሰው ምሥጢር በሚፈርድበት ቀን በኢየሱስ ክርስቶስ እኔ በወንጌል እንዳስተማርሁ ፍርዳቸው ይሆናል እንዳለው የሚሆንበት ጊዜ አለ። ሮሜ 2:11-17። 1:42።[38]

ጋሎች በሃይማኖት አረማውያን ናቸው። ብቻ የሐዋርያ ማጣት ነው እንጂ፥ ፩ አምላክ እንዳለ ያውቃሉ፤ ዋቃ ጉራቻ ይሉታል። በተቸገሩና በተጨነቁ ጊዜ ወደ ሰማይ ያያሉ፤ ወደዚያውም ይለምናሉ።

በልተህ አብላቸው አለው። ... ላሎም ይህን ነገር ሰምቶ የነገረውን ሁሉ አድርጎ ... አልመጣም ብሎ ካዝማች እንድርያስ ላከ። ከዚህ በኋላ አዝማች እንድርያስ ስማ ሠራዊት ክተት በጕራት ብሎ ሰውን ሁሉ ሰብስቦ ተዋጉ። (ላሎ) ድል ነስቶ ላሙን ነድቶ ልጆቹን አስከትሎ ጋላ ከሚባል ዱር ገብቶ ጫት ቡን እየበላ ወተት እየጠጣ ጎጆ ሰርቶ ተቀመጠ" (EMML 144, ff. 107b-108a)።
35. መ "ሉማ።
36. መ ከቡርታ።
37. በሳቢያው ለዐመፅ እንዳይዶልቱ ይሆናል።
38. መ ።

ከጋላ ሁሉ አስቀድሞ የወሎ ጋላ አሰለመ:: ቀጥሎ የሜጫ ጋሎች፥ ነገሥታት ነን የሚሉ: ከጊቤ ማዶ ያሉ አሰለሙ:: ቀጥለው በሐረርጌ ከተማ ዙሪያ ያሉ ጋሎች ምስሮች በገዙዋቸው ጊዜ በግድ ሰለሙ፤ በኋላም ባጼ ምኒልክ ዘመን እስከ ኢቱ[39] ሰለመ::

አሁንም የቀረው ጋላ ያማራ ወታደርን ስለጠላ[40] ክርስቲያን ከመሆን እስላም መሆንን ይመርጣል:: ጋላ አማራን መጥላቱ ገንዘብን በመውደዱና በክፋቱ በመጨከኑ እንቅፋት ሆኖበት ነው እንጂ የእስላም ቢሆን ወይም የክርስቲያን የሃይማኖትን ክፋትና በጐነት ለይቶ ስላወቀ አይደለም::

### ጋሎች በሴት ቅናትና መጋደል ይቅር ብለው ሕግ የሰሩበት ምክንያት::

(ገ. 555-561)

በወሎ፥ በፊት ገና ሳያሰልሙ፥ አንድ ጅግና ጎበዝ ባገራቸው ነበረ፤ መልካም ቆንጆ ምሽት ነበረችው:: አንድ የጨዋ ልጅ መልከ መልካም ገና ከሴት ያልደረሰ ጐበዝ በጎረቤት ነበረ:: የዚህ ጅግና ምሽት በዚህ ጐበዝ ፍቅር ተነድፋ ነፍስ አልቀረባትም:: ዘወትርም ለምኝታ ትመኘው ነበረች:: ከዕለታት አንድ ቀን በተመቸ ቦታ አገኘችው፤ ፈቃድዋንም ለመፈጸም ያዘችው:: በጋላ ሥርዓት ያልገደለ ሰው ከሴት አይደርስም ነበረ፤ ይልቁንም ከጉልማሳ ምሽት ምንም አይቀርብ ነበረ::

ስለዚህ እንዲህ አላት፤ የተደረገ ነገር ሳይሰማ[41] አይቀርምና እኔም ገና መራየን አላወጣሁምና ይህ ነገር ቢሰማ አንች ትነወሪያለሽ፤ ባልሽንም ታስነውሪያለሽ፤ ስለዚህ[42]:: አሁን አይሆንም:: በኋላ ግን ከዘመቻ ገድዬ በተመለስሁ ጊዜ በግልጥ ወዳጅ አደርግሻለሁ:: የጅግና የእገሌ ምሽት ሆነሽ አሁን ከኔ መራዬን ካላወጣሁ ልጅ ጋራ ብትገኝ በኋላ ላንች ታላቅ ኃፍረትና ነውር ይሆንብሻል አላት::

እሱዋ ግን አንድ ጊዜ በክፉ ፍትወት ተነድፋ፥ በሱ ፍቅር እሳት ልብዋ ተቃጥሏልና፥ ይህማ ምን ቸግሮህ፤ እኔ አንዱን ልጄን በምሥጢር በንዲህ ያለ ስፍራ እሰድልሀለሁ እሱን ግደልና ሰልበህ እያዘፈንህ ና አለችው::

እሱ ግን አዬ ብትጠይኝ ነው እንጂ ይህስ መውደድም አይደለ፤ የዚያን ጅግና ጐበዝ ልጅ ገድዬ በኋላ የተደረገ ነገር ሳይሰማ አይቀርምና ቢሰማ ይገለኛል:: እንኳን እኔን ከነዘር አዛነርቴ ያጠፋኛል አላት::

39. መ ኤቱ::
40. መ ስጠላ::
41. መ ሳይማ::
42. መ ስዚህ::



እሷም ግድ የለህም ይህን ነገር ከኔና ካንተ በቀር ሌላ ሰው ማን ያውቀዋልና ይሰማል ብለህ ትጠራጠራለህና ትፈራለህ አለችው::

እሱም በይ እንግዲያስ ነገርሽ እንዲህ ከሆነ፥ በኋላ ስለ ልጅሽ እንዳይጠጥትሽ ይህነንም ምሥጢር ለሰው እንዳታወጭ ብሎ በጽኑ መሐላ እንደ ሥራታቸው አማላት:: ከዚህ በኋላ በሩካቤ ሳይገናኙ ሁለቱም በየቤታቸው ሄዱ::

ማታ በጨለማ በቀጠሮው ስፍራ ሂዶ ከዱር ተሸሽጎ ተቀመጠ፤ እሷም ልጅዋን ባንድ ምክንያት ልካ ወደዚያ ስፍራ ሰደደችው:: ልጁም በደረሰ ጊዜ ያዘውና ወደ ሩቅ ስፍራ ወሰደው:: ከዚያም ይህ ልጅ የወንድሜ ልጅ ነውና አደራ ደኅና አድርጋችሁ[43] ተጠንቅቃችሁ[44] ጠብቁልኝና አኑሩልኝ ብሎ ከወዳጅ ዘመድ ቤት አኖረው::
ጊዜው የሽብርና የስርቆት የመግደል ጊዜ ነበርና፥ አባት እናት ቤተ ዘመድም ሁሉ ተሰርቆ ተሸጦ ይሆናል (ወይም ጋዱ ገድሎት ይሆናል)[45] ብለው አልቅሰው ዝም አሉ::

ይህ ጐበዝም ጥቂት ሰንብቶ አንድ ልብስ የፍየል ደም ቀብቶ አንድ ጨቤ ይዞ ወደ ሩቅ አገር ሂጄ ገደልሁኝ፤ ሰለባውን[46] አስጣሉኝ፤ የደም ሽማውን ጨቤውን ግን አመጣሁኝ ብሎ አሳያቸው:: በቤቱ ይዘፈን ጀመረ::

ይህች ሴትም ምንስ ልጃችን ጠፍቶ አዘንተኞች ብንሆን ለርሱም ለጐረቤታችን ሞቱ (ነውና) እንደሰው ሁሉ ሂደን እንኳን ደኅና መጣህ፥ እንኳ ቀናህ እንበለው ብላ ከነ ባልዋ ወደ ቤቱ ሄዱና እንኳ ደኅና ገባህ፥ እንኳ ቀናህ አሉት::

እሱም እንኳ ደኅና ቆያችሁኝ ብሎ እንደ ሥራቱ ስለ ልጃችሁ ሞት *ሐሞቱ ኢሲኒቲ ኢንዴቢይን ከንጉደቱ ኢሲኒ ያሌኙ* ብሎ አጸናናቸው::[47] ይህም ክፉ አይመልስባችሁ የሚያድገውን ይስጣችሁ ማለት ነው::

ከዚህ በኋላ ተነስታ ከሚዘፍነው ሰው ጋራ ተነስታ[48] ዘፈነች::

ዘፈን ከተፈጸመ ሰው ሁሉ በየቤቱ ተበተነ::

ይህ ጐበዝና ይች ሴት የሚመቻቸውን ጊዜ ሲጠባበቁ ፩ቀን በሩካቤ ተገናኙ፥ ክፉ ፍትወታቸውንም ፈጸሙ:: ከፊተኛው የሚበልጥ እጅግ አጥብቃ ወደደችው::

43. መ "ጋቸው:: ይህ በጸሐፊው አማርኛ ልክ ሊሆን ይችላል::
44. መ "ቃቸው:: እንደ ቍጥር 43::
45. በኋላ በቅንፍ ኅዳግ ላይ የተጨመረ::
46. መ ሰላ"::
47. መ::
48. መ::

እሱም አንድ ጊዜ ልቧን መዝኖ ታልና ጥቂት ሰነባብቶ እንቢ አላት:: ምነው ምን ሆንህ አለችው::

ባልንጀሮቹ ይህ አንድ የገደለ ሁለተኛ ያልደገመ[49] እያሉ ሰደቡኝና አሳፈሩኝ አላት::

ይህማ ምን ችግርህ ደግሞ ሁለተኛውን ልጄን ግደለው ብላ ሰጠችው:: ወስዶም ከወንድሙ ጋራ ጨምሮ (አኑሮት)[50] መጣና እንደ ፊተኛው ገባ፤ ምኞቷንም ፈጸመ::

እንደልማዱ ደግሞ እንቢ አላት:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ እሷም ፫ኛውን ልጅዋን ደግሞ ግደለው ብላ ሰጠችው:: ወስዶም ከወንድሞቹ ጋራ አኖረው:: እንደልማዱም ገደልሁ ብሎ ገባ:: እስዋንም ምሽት አከል አድርጎ ያዘ::

በደረጀም ጊዜ ይህ ጐበዝ ገዳይና ጅግና ሆነ:: እነዚያንም ልጆች እየተመላለሰ እያያቸው በምግብ እያስመቻቸው አደጉ::

ከ፳ ከ፴ ዓመት በኋላ ብርቱ ጉዳይ አለኝና ፯ ቤት ወሎ ይሰብሰብልኝ ብሎ ለሹሙ ለሐዩ ነገረው:: በሁሉም በሐዩ ትእዛዝ ተሰበሰቡ:: ያዒ የሚባል ታላቅ ጉባዔ አደረጉ::
በጉባዔውም መሀከል ይህ ጐበዝ ተነስቶ ቆመ:: ስሙኝ ዘመዶቹ፥ ዋቃ እግዚአብሔር ይስማችሁ[51]::

ጉባዔውም ዝም ብሎ ነገሩን ለመስማት አደመጠ:: *አንዱ ሥራታቸው[52] ጉባዔውንና አገሩን ቆሌውንና አድባሩን ከመረቀ በኋላ፥ ነገሩን እንዲህ ነው ሲል ጀመረ::

የምነግራችሁ ነገር እገሌን የሚያስቆጣ ነውና አስቀድማችሁ እሱን እንዳይገለኝ እሡሩልኝ አለ:: ያ ሰውም ተያዘና ታሠረ::

ነገሩንም ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው፥ የዚህ ሰው ምሽት እሱን በመመኘት በክፉ ፍትወት ተነድፋ በልጆችዋ ያደረገችውን ጭከናና[53] ጉድ ነገር ሁሉ ነገራቸው::

እኔ ግን ልጆቹን አልገደልኩም፤ በመልካም ቦታ እየመገብሁ አሳደግሁ እንጂ፥ ብሎ ሸልሞ አስጊጦ ባጠገቡ አኑሯቸው ነበርና ተነሱ ብሎ በጉባዔው መሀከል አቁሞ፥ እነሆ ልጆችህ ብሎ ላባታቸው አስረከበ::

ልጆቼ ሞቱ ብሎ ተስፋ የቆረጠና በኀዘን ተደቁሶ የነበረ አባትም ድንገት ሳያስበው የልጆቹን መገኘት[54] በጆሮው በሰማ ባይኑም ባያቸው ጊዜ የደስታ ድንጋጤ ደንግጦ እንደ ድንጋይ ሆነ::

49. መ ያለ"::
50. መ::
51. "አለ" መጨመር ነበረበት::
52. "እንደ ሥርዓታቸው" ለማለት::
53. መ ጭከ"::
54. መ "ች::



ሰውም ሁሉ በዚህ ሰው ደግነት በዚያች ሴት ጭከናና ክፋት ተደነቀና ተገረመ::

ከዚህ በኋላ ደግሞ ይህ ሰው በጉባዔው መሀከል ተነስቶ ቆመ፥ እንዲህ ሲል፡ ወዳጆቹና ዘመዶቹ ሆይ፥ ደግሞ እስቲ ስሙኝ አንድ ጊዜ ለኛ የሚጠቅመውን ነገር እንድናስብና ሥራት እንድናወጣ እንድናቀናም ልንገራችሁ::

ዕውቀት የሌላቸው እንስሶችና አራዊቶች እንኳ ለልጆቻቸው ይራራሉ:: ስለ ልጆቻቸውም ራሳቸውን ለሞት አሳልፈው ይሰጣሉ:: ሰዎች የሚባሉ ፍጥረቶች የኛ ሴቶች ግን ከእንስሳና ከአራዊት እጅግ ይከፋሉ:: ይህም ክፋታቸው የሥጋ ፍትወታቸውን ለመፈጸም ልጆቻቸውን ለሞት አሳልፈው እስኪሰጡ የልባቸው መሸፈንና መደንደን ይታያል::

እንዲህ ከሆነ እንግዴህ በንዲህ ያሉ ፍጥረቶች ሴቶች በሚባሉ መቃናትና መጣላት መጋደልም ይቅር:: ወንድም ወንድሙን፥ ባልንጀራም ባልንጀራውን፥ ቢቸገር የሚረዳውን፥ ቢጮህ አብሮት የሚወጣውን፥ ቢቆስል የሚያነሳውን፥ ቢሞት የሚቀብረውን በኒህ ጥፎች ምክንያት እንዳይጣላውና እንዳይገድለው እናንት[55] ሽማግሎች ለዚህ ነገር የውል ሥራት አድርጉ:: እናቶቻችን ናቸውና ነው እንጂ ሴቶች ከሰው ሊቆጠሩ አይገባቸው ነበረ:: እንግዴህ በሴት መቀናናትና መጣላት ይቅር አለ::

ነገሩም በጉባዔው ሁሉ ፊት የተወደደና ያማረ ሆነ:: ከዚህ በኋላ ሽማግሎች በሴቶቻቸው ላይ ይህን ሥራት ሠሩ::
አንደኛ ነገር፥ ሴት ልጅ ባባትዋ ቤት ከወንድሞችዋ ጋራ ርስት አትካፈል::

ሁለተኛ፥ በሰው ብትሞት የነፍስ ዋጋዋ የወንድ ነፍስ ዋጋ እኩሌታ ፱ ቁም ከብት ይሁን፤ የወንድ ግን ፲ ቁም ከብት::

ሶስተኛው፥ አባት ሴት ልጁን ሲድር ልጄን ሽጪለሁ[56] ይበል፤ ባልዋም እንደባርያ ቀጥቅጦ ይግዛት:: ኮብልላ ሂዳም ከሌላ ሰው ብትወልድ ልጆቿን ጨምሮ መልሶ ወስዶ የግድ ይግዛት::

አራተኛ፥ ከወንድ ባይናፋ[57] ብትያዝ የቅናት ዋጋ ውሽማዋ ለባልዋ አንድ ወይፈን ይስጥ:: ለሷም ፩ ሽማና መስታዎት[58] ይስጥ:: ይህንን ይዞ ወደ ቤትዋ የሚሄድበት[59] ቀን አራራ ይባላል:: ይህም የዕርቅ ቀን ማለት ነው:: ለዚህ ላንዱ ወይፈን መናጆ ፳ትም ፲ርም ቁም ከብት አብሮ ወስዶ ከባልዋ በረት ያገባል::

55. መ እናት::
56. መ ስ"::
57. "ባይናፋ"? ትርጉሙ ግልጽ ነው፤ ቃሉ ግን የተለመደ አይደለም::
58. ታሪኩ እውነት ቢሆን ድርጊቱ የተፈጸመው በቅርብ ጊዜ ነው ለማለት ይቻላል::
59. መ የምትሄድበት::

እሱም ከጥቂት ባልንጀሮቹ ጋራ ሁኖ አጊጦ ተሸልሞ ይሄዳል። ባለቤቱም ጨዋታና ወግ የሚያውቁትን ሽማግሎች ጠርቶ ጐረቤቶቹንም ሰብስቦ መብልና መጠጥ አቅርቦ እሱም ከምሽቱ ጋራ አጊጦና ተሸልሞ ይቆያል።

ያም እንደደረሰ የውሽማውን ራስ ይስማል። ያመጣውንም አስረክቦ አልፎ ይቀመጣል።

ሽማግሎችም እንግዴህ እናንተ[60] በሁሉ ልትረዳዱ የሚገባችሁ ወንድማማች ናችሁ ይሏቸዋል።

ከዚህ በኋላ ከመልካም ጨዋታ ጋራ መብልና መጠጥ ይቀርባል። እነርሳቸውም በደስታ ሲበሉ ሲጠጡ ሲጫወቱ ውለው ያመጡትን ወይፈን አስረክበው ለመናጆ ያመጡትን ከብቶቻቸውን መልሰው ይዘው ወደቤታቸው ይሄዳሉ።

ከዚህ በኋላ ወደ ውሽማው በግልጥ እየተመላለሰ እንደ ባለቤት ይሆናል። ጦሩን በደጁ አቁሞ ይገባል። ባለቤቱ በሜዳ ኑሮ ሲመጣ የምሽቱን ውሽማ ጦር በደጁ ቁሞ ባየ ጊዜ ወደኋላው ተመልሶ እስኪወጣለት ከጐረቤት ሲጫወት ይቆያል። ወደሩቅ አገር የሄደ እንደሆነም ና ቤቱን ጠብቅ ብሎ ይጠራዋል። የምሽቱ ውሽማ ከቤቱ መጥቶ እንደ ባለ ቤት ሁኖ ባለቤቱ ሲሰራው የነበረውን እየሠራ እስኪመለስ ይቆየዋል[61]።

ጋሎች ይህን ሥራት የሡሩ መቸም ሴትን ጠብቆ ማዳን የለምና ላንዲት ሴት ሁለት ወንድ ቢጠብቃት ይሻላል፤ መቃናትና መጋደል ይቀራል ብለው ነው።

## ስለ ጋላ ትውልድ

(ገ. 586-7)

የጋላ ትውልድ እንዲህ ነው፣ ፊት የጠራናቸው በርቱማ[62] ፯ ቦረን ፲፩ ሁለቱ ወንድማማች ፲፰ ልጆች ወልዱ።

የበርቱማ ልጆች

፩፥ ከረዩ
፪፥ መረዋ
፫፥ ኢቱ
፬፥ አክቱ[63]

60. መ እናተ።
61. መ የ"።
62. ቍ. 10ን ተመልከት።
63. ቍ. 12ን ተመልከት።



፭፡ ወረነሻ
፮፡ ሁብና[64] ናቸው

የከረዩ ልጆች

፩፥ ሊበን
፪፥ ሜጫ
፫፥ ትሉማ[65]
፬፥ ወሎ
፭፥ ጆሌ
፮፥ አቦ
፯፥ ሉባ
፰፥ በላዕ ናቸው

የመረዋ ልጆች

፩፥ ወርድያን
፪፥ አሩሲ
፫፥ ኢቱ
፬፥ ጥሙጋ

ወርድያን ፫ ይወልዳል

፩፥ አና
፪፥ ዑር[66]
፫፥ አበጢ

እኒህ ሁሉ የመረዋ ልጆች ናቸው። እኒህ የመረዋ ልጆች በኃይልና በብዛት ከሁሉ ይበልጣሉ። ስለዚህም በሁሉ ይገኛሉ።

የኢቱ ልጆች

፩፥ ጆሌ
፪፥ ሉባ

የአክቱ[63] ልጆች

፩፥ ጅንጉር
፪፥ ጨፉ

64. "ም" ተውጣ ነው እንጂ "ሁምበና" ነው።
65. ሌም ቱለማ፤ ቍ. 15ንና 16ን ተመልከት።
66. ቍ. 18ን ተመልከት።

የወረነኛ ልጆች

፩፥ ሰዩ
፪፥ አቡ
፫፥ ጫቡ
፬፥ ይሉ
፭፥ ጉድሩ
፮፥ ኩታይ
፯፥ አሞሩ
፰፥ ሆሮ ናቸው

የሁበና[64] ልጆች

፩፥ ራያ
፪፥ አዘቦ
፫፥ አሸንጌ ናቸው።

እነዚህ ወሎች ያማራ ጕረቤት ስለሆኑ ጋልኛን አጥፍተው ባማርኛ ይናገራሉ። አሸንጌዎች የትግሬ ጎረቤት ስለሆኑ ጋልኛን አጥፍተው በትግርኛ ይናገራሉ።

የቦረን[67] ልጆች፥

፩፥ ዳጨ
፪፥ ጅሌ
፫፥ ኮኖ።

እነዚህ ትሉማ[65] ይባላሉ።

፬፥ ቦች
፭፥ አካኮ
፮፥ ወቦ
፯፥ ሉባ።

እኒህ ሰደቻ ይባላሉ።

፰፥ ጭሌ
፱፥ ሊበን
፲፥ ጉድሩ።

እኒህ ሆኮ ይባላሉ።

፲፩፥ ሆኮ።

67. ቍ. 11ን ተመልከት።



የዳጨ ልጆች፥

፩፥ ሌቃ
፪፥ ጨለባ።

የጅሌ ልጆች፥

፩፥ ወለጋ
፪፥ ጉማ።

የኮኖ ልጆች፥

፩፥ ሊሙ
፪፥ ጅማ
፫፥ ጌራ።

የቦች ልጆች፥

፩፥ አብቹ
፪፥ ግምብቹ።

የአካኮ ልጆች፥

፩፥ ወበሪ
፪፥ ገላን።

የወቦ ልጆች፥

፩፥ ሉሜ
፪፥ ሊበን።

የሉባ ልጆች፥

፩፥ ሜታ
፪፥ ዋዩ ይባላሉ።

የጭሌ ልጆች፥

፩፥ ጉለሌ
፪፥ ሰላሌ፡[68]

68. ፪ ተረስቶ በኋላ ከ"ሰላሌ" ቀጥሎ ተጽፏል።

የሊበን ልጅ፥

፩፥ አበተ[69]።

የጉድሩ ልጅ፥

፩፥ ደራ።

የሆኮ ልጅ፥

፩፥ በረና[67]።

እኒህ ሁሉ የጋላ አባቶች ናቸው።

## የወሎ እስልምና እውነተኛው ታሪክስ እንዲህ ነው።
(ገ. 592-594)

የእስላሞች መጀመሪያ ነቢይና ንጉሥ የመሐመድን የልጁን የፋጢማ ባል አሊን አብደርህማን[70] የሚባል ገደለው። ያሊ ልጅ ከፋጢማ የተወለደው ሐሰን ነግሦ ነበርና በኋላም የሚነግሡ የመሐመድ የፋጢማ የዓሊ ልጆች ናቸውና የአብድ ረህማን[70] ልጆችና ወገኖች ሁሉ የዓሊን ደም ተበቅለው ይፈጁናል ሲሉ ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከሸዋ በይፋት ተቀመጡ። ይህም የሆነ በንጉሥ ድግና ሚካኤል ዘመን ነው።

ድግና ሚካኤል ከ፲፻፶፮ (እስከ) ፲፻፹፪ ዓመተ ምሕረተ ፳፮ ዓመት ነገሠ። በሱ ዘመን ውስጥ እኒህ እስላሞች በይፋት ገቡ። በዚያ ዘመን የነበሩ ተከታትለው የነገሡ ነገሥታትና መኳንንት ካህናትም በስንፍናቸው ዝም ብለዋቸዋልና ብዙ ገንዘብ እየሰጡ በማታለል የነገሥታቱን የመኳንንቱን ልብ አብርደው እኒህ እስላሞች ቀስ ቀስ እያሉ በሸዋ ዳር ለዳር ባልዩ አምባ ባርጎባ እስከ ወሎ አገር እያስተማሩ ሰው ሰራሽ ሃይማኖታቸውን ዘረጉና አሰፉ። ብዙ ያልተማረ ሕዝብን አሰለሙ።

ወሎም በነበረበት ከኒህ እስላሞች ጋራ ተገናኝቶ የእስላምን ሃይማኖት መስማት ጀመረ። ከዚህም በኋላ ከኒህ እስላሞች ከሉ የሚባል ሽህ መጥቶ አስተማረውና ከወንድሞቹ ተለይቶ፡ እሱ ካሰለመም የእስላም ወገን እየበረታ ሄደ።

69. "አበጢ" ይሆን?
70. መ።



ባጼ ዓምደ ጽዮን ደከሞ የነበረ[71] እንደ ገና እየተነሳ አሸቸገረ። ስለ ዚህም በዚያ ዘመን በውድማ አስፈሬ ጊዜ በነገሠ በሁለተኛው (ዓመት)[72] ባንድ ወገን ጋላ ባንድ ወገን እስላም እየተነሳ ቢያስቸግራቸው ጋላን ብቻ ለማጥቃት እኒህ ከይፋትና ከወሎ እስላሞች ለመታረቅ ንጉሡና መኳንንቱ ካህናቱም ተሰብስበው ባንድ ሁነው መከሩ። መክረውም አልቀሩ ከእስላሞች ጋራ ታረቁ[73]።

ዕርቃቸውም ለንጉሥ ሊታዘዙና ሊገብሩ፥ በሃይማኖታቸው ሊኖሩ፥ በየሕዝባቸው በእያገራቸው ሊሾሙ[74]፥ ባገራቸው ውስጥ ያለ ክርስቲያንን እንዳይበድሉ፥ ቤተ ክርስቲያንም ሊጠብቁ እንጂ ላያቃጥሉ፥ በዚህ ውል ክርስቲያኖች በወንጌል እስላሞች በቍርዓን ተማምለው ውል ሳያፈርሱ በፍቅር ሊኖሩ ታረቁ።

ስለዚህ በይፋት ባርጎባ ባሉ እስላሞች አለቃ ወይም ገዥ ተብሎ ወላስማ ተብሎ ከወገናቸው ተሾመ። የወልሰማን ትርጓሜ በኋላ ከእስላሞች ታሪክ ላይ እናመጣዋለን።

ለወሎም ንጉሥ ሰጥቶት ከዋየት ወዲህ ያለን አገር ያዘና ግዛቱ ርስቱም አደረገ። የዚያ አገር ስም ጥንት ላኮ መልዛ ይባል ነበር፤ ወሎ ከያዘው ወዲህ በስሙ ወሎ ተብሎ ተጠራ። ይህ የሆነ በሺ ፫፻፷፫ ዓመተ ምሕረት ነው።

ወሎም ገና በሕይወቱ ሳለ አገሩን ለ፯ቱ ልጆቹ አካፍሎ ሰጣቸው።
አገራቸውም በየስማቸው ተጠራ።
የሂበኖ ወረሂማኖ ተባለ፤
የቃሉ ወረቃሉ ተባለ። ወረ ማለት አገር ወይም መንደር ማለት ነው።
የዐበይ ዐበይ ቤት፥
የዓሊ ዓሊ ቤት፥
የአምቦ ለገ አቦ[75]፥
የሂዳ ለገ ሂዳ፥
የጎራ ለገ ጎራ ተባለ። ለገ ወይም ለጋ ማለት መልካ ማለት ነው።
ስለዚህም አገሩ በጥቅሉ ወሎ ፯ ቤት ወሎ ይባላል።

71. ዓፄ ዓምደ ጽዮን ሲነግሥ በኢትዮጵያ ግዛት ስር የነበሩ የእስላም ሀገሮች አድመው ዐምፀውበት ነበር፤ ይህ ዐመፅ ሳጥናኤል የአምላኩን መንበር ለመቀማት እንደሞከረ ዓይነት ነው ብሎ መታቸው፤ Peruchon, "Histoire des Guerres d' 'Amda Şyon, pp. 271-363, 361-493.
72. ውድማ አስፈሬ ያነገሠው በ1292-1306 ዓ. ም. ነው።
73. የግብጾችን ታሪክ ይመስላል። መለካውያን (ካቶሊኮች) ቢያስቸግሯቸው ክርስቲያኖቹ ከእስላሞቹ ጋራ ተስማሙ ይባላል።
74. መሾም መሻር የሙሉ ሥልጣን ምልክት ነው።
75. "ም" ተውጣ ነው እንጅ ቃሉ "አምቦ" ነው።

የወሎ እውነተኛ ታሪክ ይህ ነው:: የጋኔን ክታብ ተቀበለ፡ አረርጌ ወርዶ የእስላም ክታብ ተማረ፡ ግራኝ ሲመጣ አብሮ መጣ ማለት ግን ፍጹም ሐሰት እንደሆነ በታሪኩ አለመስማማትና በነገሩ ሁሉ ይታያል::

## ስለ ጋላ ተጨማሪ ያፍ ታሪክ

(ገ. 568-9 572-3)

*(አለቃ ታየ መጽሐፋቸው ውስጥ ስለኦሮሞ ከሚነገረው ያፍ ታሪክ ብዙ ሰብስበዋል:: አንዳንዶቹ እንዲህ ሲሉ ይጀምራሉ፤ ጋሎች አባታቸው አራት ወንዶች (ከረዩን፥ ቱለማን፥ መጫን፥ ወሎን) ሶስት ሴቶች (አልኮን፥ ዱረቲን፥ አያንቱን) ወልደ:: ወንዶቹ የውጭ ሴቶች ቢታጡ(!) እንቶቻቸውን አገቡ ይሉና ልጆቻቸውን ይዘረዝራሉ:: ታሪኩ ከአጀማመሩ ላይ ባይታመንም፥ ስለኦሮሞዎች የሚጽፍ ሰው የልጅ ልጆቹን ዝርዝርና ማን የት እንደሰፈረ የሚሰጥን ምንጭ ሳያጠናው አያልፍም:: ስለዚህ ከአለቃ ታየ መጽሐፍ በቀዳሁት ላይ ከዚህ በታች ያሉትን ሁለቱን እጨምራለሁ::*

**<u>አንዱ ታሪክ</u>** (ገ. 568-9)፤

**ከረዩ አያንቱን አግብቶ፥ አሩሲን፥ አያን፥ ቤቶን፥ ይቱን[76] ወለደ::**

**ዳግመኛም የእስላም መሐመድን[77] የየሱፍን[78] ልጅ አግብቶ ትጉሪን[79]፥ ኑሪን ወለደ::**

አያም አሩሲ ቢሞት እንደ እስላም ሕግ የወንድሙን ምሽት ወርሶ ሱባን፥ ድንጉርጉራን ወለደ:: ከንብ ገደል አይመለል ድረስ፥ ከአደል እስከ ጥልጣል[80] ድረስ፥ ከትግሬ በመለስ ይፋትን፥ ምሥራቁን አገር ሁሉ ይዘውታል:: ወገግን[81]፥ አሰቦትን፥ ጥቁር ምድርን፥ ጨርጨርንም ሁሉ ይዘውታል::

---

76. ይቱ "ኢቱ" ነው::
77. "ን" በስሕተት የገባች ይመስላል::
78. "የ" በስሕተት የገባች ይመስላል::
79. ትጉሪ ለታጁራ (ጅቡቲ) ስም የሰጠው የኦሮሞ ነገድ መሆኑ ነው::
80. የአፋሮች ሌላ ስም::
81. ወገግ የአቡነ ሳሙኤል ሀገረ ስብከት ነበረ:: ገድላቸውን ስታሊስናስ ኩር አሳትሞታል፤ Kur, *Actes de Samuel de Wagag.* አሰቦት ገዳማቸውን ያቋቋሙበት ደብር ነው:: ብዙዎቹን መነኩሳት አሁን በትግሬ ነፃ አውጪ ዘመነ መንግሥት የአነግ አባላት አረዷቸው::



**ትሎማ አልኮን አግብቶ የሜጫ አብቹን[82]፥ ዳጨን፥ ሰዶን[83] ወለደ::**

*ዳግመኛም* ከረዩ ቢሞት **የመሐመድን[77] የሱፍን ልጅ ምሽቱን ወርሶ ራያ ያሉትን ጋሎች ወለደ፤ ትሎማ ይባላሉ:: ጅሌም የትሎማ ልጅ ነው ይላሉ:: ጥንት የዛር ልጅ ነው ይሉት ነበር:: በበረት ውስጥ አግኝቶ አሳደገው፤ ስለዚህ የትሎማ ልጅ ተባለ::**

**ወሎ ያደል ሴት አግብቶ ካሉን ወለደና ሞተ::**

*ዳግመኛም* **ትሎማ የወሎን ምሽት ወርሶ** ባቡን፥ ጉራን፥ ኢሉን፥ ቃሉን፥ ካሎን፥ ሂዳን፥ ኩታይን (ወለደ)[84]:: እነዚህ ፯ቱ ትሎማ ናቸው:: በውርስ ልጅነት ወሎ ይባላሉ::

**ዳጨ የትሎማ ልጅ[85] ነው::** ፬ ቤት አብቹን፥ ፰ ቤት ግምብቹን፥ ፯ ቤት ጋላንን ይወልዳል::

*ዳግመኛም* **ያብቹ ሜጫን[86] (ምሽት)[87] ወርሶ** ሜታን፥ ቦረናን፥ ሀገረ ደዋሮ ያለውን ሰዶን[88] ይወልዳል:: እነዚህም አጨብር፥ ወረዶሮ፥ ኖኖ ይባላሉ::

**ሜጫም ዱረቲን አግብቶ** ጅፋርን፥ ወጌዱን፥ ሊበንን ወለደ::

ኩታይም[89] በሪያን በውርስ ካብቹ ሜጫ ምሽት ወለደችው:: እናታቸው ጥቁር ሻንቅላ አይጠ በላ ናት[90]:: እነዚህ ሁሉ እስከ ዓጼ ልብነ ድንግል ዘመን ድረስ ፯ ፯ ሁነው በኢትዮጵያ ሁሉ መልተው ከክርስቲያን ጋራ እኩል በኮል ሁነው ኖሩ::

---

82. አነጋገሩ ሌሎች አብቹዎች ወይም ሌሎች ሜጫዎች ያሉ ያስመስላል::
83. "ሶዶን" ማለቱ ሳይሆን አይቀርም::
84. "ወለደ" አልተቀዳም፤ ተረስቶ ይሆናል::
85. መ ልድ::
86. ቍ. 80ን ተመልከት::
87. ያልተቀዳ::
88. በዚህ አነጋገር ደዋሮ ይባል የነበረው ሶዶ መሆኑ ነው፤ የአቶ ዐፅሜም እምነት እንደዚሁ ነው:: ትክክሉን ግን በእርግጠኛነት ማወቅ ያስቸግራል:: በየጊዜው ኢትዮጵያን የጐበኙ ምዕራባውያን የነደፏቸው ካርታዎችም እርስ በርሳቸው አይስማሙም:: ደዋሮ ግራኝ መጀመሪያ የወጋው የክርስቲያን ግዛት ስለሆነ አዳል አጠገብ መሆን አለበት፤ ወይም ሁለት ሶዶዎች ነበሩ፤ ወይም ሶዶ ከአዳል የሚዋሰን ሰፊ አገር ነበረ:: መጠሪያነታቸው ስለቀረው የቦታ ስሞች ሁኔታ ለማወቅ የሚፈልግ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ሰብስቦ ያሳተመውን ማንበብ ይችላል፤ Richard Pankhurst, *The Ethiopian Borderlands*, Lawrenceville (New Jersey) 1997.
89. መ ኩታሪን::
90. ጸሐፊው ሌሎች ሕዝቦች ቀንዳውጣ፥ ውሻ፥ እንቍራሪት፡ አንበጣ እንደሚበሉ የሰሙ አይመስሉም::

<u>ሌላው ታሪክ</u> (ገ. 572-3)፤

**ከረዩ አያንቱን አገባና ፲ ወለደ፤ እነሳቸውም እኒህ ናቸው::**

፩፡ አሩሴ
፪፡ ኢቱ
፫፡ ጥሙጋ
፬፡ ጂሌ
፭፡ ሱባ
፮፡ ጅጉርገር
፯፡ ጫፋ
፰፡ ራያ
፱፡ አዘቦ
፲፡ አሸንጌ

**ሜጫ አልኮን አግብቶ አስራ አምስት ወለደ:-**

፩፡ ሰዶ
፪፡ አቡ
፫፡ ጫቡ
፬፡ ይሉ
፭፡ ጉድሩ
፮፡ ኩታይ
፯፡ አሞሩ
፰፡ ሆሩ
፱፡ ሊቃ
፲፡ ጩለባ
፲፩፡ ወለጋ
፲፪፡ ጉማ
፲፫፡ ሌሙ
፲፬፡ ጅማ
፲፭፡ ጌራ ናቸው::

**ትሎማ ዱረቲን[91] አግብቶ አስራ አምስት ወለደ:-**

፩፡ አብቹ
፪፡ ግንብቹ
፫፡ ወበሪ
፬፡ ገላን

91. መ ዱረቱን::



፭፡ አዳ
፮፡ ሉሜ
፯፡ ሊበን
፰፡ ሜታ
፱፡ ዋዩ
፲፡ ጉለሌ
፲፩፡ ሰላሌ
፲፪፡ ዋጁ
፲፫፡ አቦቴ
፲፬፡ ደራ
፲፭፡ ቦረና

**ወሎ ፯ ምስቶች አግብቶ ከ፯ ላይ ቤት ሠርቶ ፯ ልጆች ወለደ፤ ስማቸውም እኒህ ናቸው:-**

፩፡ ሂበኖ
፪፡ ዐበይ
፫፡ አሊ
፬፡ ቃሉ
፭፡ አምቦ
፮፡ ሒዳ
፯፡ ኅራ ይባላሉ::

**የጋላ ሕዝብ በየነገዳቸው እኒህ ናቸው፤ የከረዩ ልጆች ፲፡ የሜጫ ልጆች ፲፭፡ የትሎማ ልጆች ፲፭፡ የወሎ ልጆች ፯ በድምሩ በድሙሩ[92] ፵፭[93] ነገድ ናቸው::**

## የጋላ ሥራትና ሕግ
(ገ. 597-600)

**በኢትዮጵያ ክርስቲያን፡ ክርስቲያን በሚባል ሕዝብ ሕግና ሥራት እየተደነገገ በየጊዜው አይፈጸምም፤ የመንግሥት አዋጅም አያቆመውም:: እግዚአብሔር በፈጠረው ዓለም በያገሩ በየደምቡ አረማዊ ቢሆን፡ ክርስቲያንም ቢሆን፡ እስላምም ቢሆን፡ አይሁዳዊም ቢሆን፡ ሁሉ በየወገኑ ጸንቶ የቆመ ሕግ አለው:: ከቶ ምንም ቢሆን በጥቂት ነገር በታናሽ ምክንያት ባል ምሽቱን አይፈታም፤ የሚያፋታም[94] የለም::**

92. መ::
93. መ:: "፵፯" መሆን ነበረበት::
94. መ የሚፋታም፤ ዐፅሜ የሚያፋታም::

ጋላ ግን ምንም በምክንያት ቢሆን በረኮ ያገባት ምሽቱን ከቶ አይፈታም:: ጋላ በታላቅ ጭንቅ ከምሽቱ ቢለይ እሷም ሂዳ ከሌላ ብትወልድ በኋላ ወደ ረኮ ባልዋ ብትመለስ ልጆችዋን ይዛ ትመለሳለች:: ባትመለስም በዚያም ብትሞት ልጆችዋ ለረኮ ባልዋ ሁነው ይሄዳሉ እንጂ ለወለዳቸው አባታቸው አይሆኑም::

ስለዚህም የመጀመሪያ ባልዋ የፈታት ሴት ብትወልድልኝ ልጆቼ ላይሆኑ እያለ አንዳንድ ከጨነቀው በቀር የሚያገባት የለም:: ይህም የረኮ ባልዋ የነበረ ቢሞት እኒህ ከውጭ የመጡ ልጆች ዘሩ ያይደሉ እንዲወርሱት ያውቃልና የብርቱ ጭንቅ ነገር ካልሆነ በዋዛ ነገር ክርስቲያን እንደሚባሉ ጕረቤቶቹ የረኮ ምሽቱን አይፈታም:: ማኅተም አልጠፋምና እነዚያ የውጭ ልጅ እንደ ልጆቹ ትክክል ናቸውና ርስትን ይወርሳሉ:: እሱም ከሌሎች ምሽቶች ቢወልድ ዋና ልጁ በኵሩ በጋልኛ አንጋፋ የሚባለው የረኮ ምሽቱ የተወለደው ነው::

ረኮ ማለትም የሕግ የኪዳን የመጀመሪያ ምሽት ማለት ነው:: ደግሞ በጋልኛ ጭንቅ ማለት ነው:: ከቁባቶቹ ወይም ከሁለተኛይቱ ከረኮ ምንም ታላላቆች ኃይለኞች ልጆች ቢወልድ ዋና ወራሹ የመጀመሪያይቱ የረኮ ምሽቱ ልጁ ነው:: ሴት ልጅ ቢወልድ ፈጽማ ወደ ባልዋ ትሄዳለች፤ እንደ እስላም ሥራት በባሏ ወገን ትጠራለች::

ጋላ ከሌላ ጎሳ እንጂ ምንም ቢሆን ከዘመዱ አይጋባም:: እንደ ጋላ ዘሩን ቆጥሮ የሚያውቅ የለም:: ታላቁ ዕውቀታቸው ዘራቸውን መቍጠር ነው:: አባት ለልጁ ትውልዱን ያስተምረዋል:: ስለዚህ እስከ ፲ ትውልድ ቢሆን አይጋቡም::

በኢትዮጵያ ፍትሐ[95] ነገሥት እስከ ፬ ትውልድ ሊጋቡ በይነዋል:: ዓጼ ዘርአ ያዕቆብ ብቻ በ፯ ትውልድ ሊጋቡ በመንግሥታቸው ሕዝብ ሁሉ አዋጅ ነግረው ነበሩ:: ይህም አዋጅ እስከ ዛሬ ከሸዋ በተጕለትና[96] በመንዝ፥ በጐንደር፥ በቤገምድርና በጎጃም፥ ከትግሬ በሐማሴን፥ በሌላም አገር ብዞች ሥራት ይጠብቃሉ፤ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሁሉ ያስቡታል::

በጋላ መጻሕፍት ከተሰጧቸው ከማይጠብቁት ክርስቲያን ነን ከሚሉት ጕረቤቶቻቸው ይልቅ የሚሻል ብዙ መልካካም ነገር አለበት:: ጻሩ አንድ ትልቅ ትልቅ[97] ሁሉን ብላሽ የሚያደርግባቸው ነገር አለ:: እሱም እግዚአብሔርን አለማወቅ ነው፤ ማለት ሕጉንና ትእዛዙን በሁሉ ስፍራ መኖሩንም አያውቁም:: ሰማዩን እግዚአብሔር ይሉታል:: ማን ፈጠረህ ቢሉት ዑመም ይላል:: በተቆጡ ባዘኑም ጊዜ ወደ ሰማይ ያያሉና በልባቸው እንዳለ ያስታውቃሉ::

95. መ ፍታ::
96. መ ከተ"::
97. መ::



ጋላ ጥንት ከምሽቱ ወንድ ቢያገኝ ይገል ነበር፡ በፊት እንዳሳየነ:: ስንጋ ካሰረለት[98] ካስታወቀው በኋላ ግን ከምሽቱ ገብቶ ቢያገኘው አንዳች አይለውም:: የምሽቱን ውሽማ ጦር ከደጃፉ ቁሞ ባየ ጊዜ እንደ ገባ[99] ያውቃልና ተመልሶ ወደኋላ ይሄዳል::

## በጋላ ሕግ የደም ሥራት

የጋላ የደም ሥራት ባራት ክፍል ይከፈላል::

መጀመሪያ ጨዋ ቢሞት ገዳዩ ፻ ቁም ከብት ይከፍላል::

ሁለተኛ ሴት ብትሞት ፶ ቁም ከብት፤

ሶስተኛ ጠቢብ፥ አንጥረኛ፥ ሸማኔ፥ ፋቂ ባለ እጅ፥ ሁሉ ቢሞት ፵ ቁም ከብት ይከፍላል::

አራተኛ ልጅ አባቱን ቢገል፥ ልጁ የረኮ ምሽቱ ልጅ ቢሆን ያባቱ ወገኖች ድንጊያ ከወገቡ አስረው ከባሕር ይጥሉታል እንጂ እርማቸው ነውና በደም ማፍሰስ አይደበድቡትም:: እናቱ ረኮ የሌላት እንደሆነች ግን የናቱ ወገኖች ተቀብለው ወስደው ፻ ቁም ከብት ይከፈሉ እንጂ የሕግ ልጅ አይደለምና አይደብደብ ይላሉ:: አባት ልጁን ቢገድልሳ ቢሉ አይገልም ይላሉ::

ስለ ጋላ ከሚነገር ታሪክ ከረጅም ባጭሩ፥ ከብዙ በጥቂቱ ይህ ይበቃናል:: ከዚህ ቀጥለን የእናሪያን (ነገር) ታሪክ አንጽፋለን::


## 18. ስለ ነገደ እናርያ[100]

(ገ. 600)

የእናሪያ ሕዝብ ሁሉ የካም ዘር ነው:: ነገደ ዮቅጣን መጥተው የነገደ ኵሳን መንግሥት በወሰዱ ጊዜ፥ ሕዝቡንም በጦር አጥፍተው የተረፈውን ባሳደዱ ጊዜ በኢትዮጲያ ደቡብ ዳር ለዳር በወላሞ፥ በሲዳሞ፥ በኵሎ፥ በኮንታ፥ በአሞሮ በዝንጅሮ የሚኖር ሕዝብ ነው:: እሱም ከጦር በኋላ ከነገደ ዮቅጣን ነገሥታት ገብቶ ለነሳቸው ተገዝቶ ገብሮ የሚኖር ነው::

ቀድሞ ጋሎች ሳይዙት ሉቅማ፥ ጅማ፥ ሌቃ፥ ትቤ፥ ጉማ፥ ከፋ፥ ይህ ሁሉ ያእናሪያ ሕዝብ አገር ነበር:: በኋላ ጋሎች እያስለቀቁት የጋላ አገር ሆነ:: ይህ ሁሉ ከቀድሞ ጀምሮ እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ከዚያም በኋላ እስከ ዘመነ ክርስትና ተያይዞ እንደ መጣ አንድ እናሪያ ተብሎ ከንጉሠ ነገሥት በታች አንድ ንጉሥ ይሾምበት ነበር::

98. መ ከ"::
99. በኋላ የተጨመረ::
100. ይህ ክፍል ስለነገደ እናርያ ነው፤ እዚህ የቀዳሁት ስለ ኦሮሞ ስላለበት ነው::



ዜናሁ ለጋሣን ወደ እንግሊዝኛ ከተረጐሙት አንዱ ቻርልስ ቤኪንግሃም።